# ላንዳፍታ

የአማርኛ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት

መስከረም ፲፱፻፹፮

፫ኛ ዓመት ቁጥር ፫

$2.50

እንቁጣጣሽ




የሳንፍራንሲስኮው ውድድር

(ገጽ 41)


**LANDAFTA** AN AMHARIC ENTERTAINMENT MAGAZINE

VOLUME 3 - NO. 3 SEPTEMBER 1993




# የኢትዮጵያ መንደር



## ETHIO VILLAGE

CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

# ማ ው ጫ


2 ከአዘጋጁ

4 ደብዳቤዎች

9 ልዩ አምድ
የአልማዝ ደምሰው አሟሟት ሊጣራ ነው።

10 እናስተዋውቃችሁ
የሲያትሏ ኤልሳቤጥ ገበየሁ

13 ልብ ወለድ
"እህያና ጠላ ቤት" (ውሂብ ጥሩነህ)
"የወጣትነት ጊዜ" (ዘውዲቱ ግርማ)
"ጨብጨባ" (ዘላለም መስፍን)
"የዴብራ ጦስ" (ገረሱ)

20 ኑሮ በአሜሪካ
"ሥራ ማግኘት. . እንዴት?"
"እኔ አላማረኝም" (ዳዊት አስፋው)
"እውነት ከልብዎ ነው?" (ዮናስ አሸኔ)
"ምን ትመክሩኛላችሁ?" (አዛለች)
"ሁሉም ሲርቁ ነው" (አያሌው ታደሰ)

30 አዳምና ሔዋን
"የመጀመሪያው አቀራረብ" (አንዱዓለም)
ጓደኛ ለሚፈልጉ

34 የአበው ቅርስ
ውስጠ ወይራ/ቅኔ/ተረትና ምሳሌ

"ግጥም ከተባለ" (ግርማ ዘገየ)
"የትኛው ነው ጀግና" (ግርማ ዘገየ)


41 እስፖርት
"ከሳንፍራንሲስኮው ውድድር የምንማረው"
(አበራ ሲሳይ)

46 ቢስቁም ባይስቁም

47 ጨዋታና ሰንጠረዥ




ደራርቱ ቱሉ በሳንፍራንሲስኮ



የሳንፍራንሲስኮው ዋሊያ ቡድን
ገጽ - 42



ኤልሣቤጥ ገበየሁ
ገጽ - 10

---

የሽፋን ፎቶ - ሟቿ እህታችን የኦርላንዶዋ አልማዝ ደምሰው አንዳርጌ

---

"ላንዳፍታ" የግል መጽሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።
©COPYRIGHT LANDAFTA 1993

የሽፋን ርዕስ
ጎጆ ማተሚያ

ላንዳፍታ
መስከረም ፲፱፻፹፮
፪ኛ ዓመት ቁጥር ፫
LANDAFTA
September, 1993 V. 2 - No. 3

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Contributing Editors**
*Girma Zegeye*
*Abera Sisay*

**Editorial Advisors**
*Dr. Abera Molla*
*Haile Demissew*
*Solomon Melesse*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Dawit Deres*
*Zelleke Nigatu*

**Editorial Assistant**
Woinishet Bekele

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Taste of Ethioipia
Sweet Auburn Grocery
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
E.C.A.C.
Tesfaye B. (Hoddo)
Yeshi Gessesse
Dallas, TX
ET. Beauty Supply
Hartford, CT
Dr. Tilahun G. Hiwot
L.A., CA
K RAH Market
New York
Gion Ethiopian Rest.
Oak Land, CA
Albo-African Shop
Seatle, WA
Amy's Merkato
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Bayibih Medlu
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone: (404)728-9122

*Landafta is an independent magazine published in Amharic bi-monthly. Views expressed do not necessarily represent that of its editors.*

# ከአዘጋጁ

እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላምና በጤና አደረሳችሁ። አዲሱ ዓመት ተስፋችሁ ለምልሞ በጐ ዓላማችሁ ግብ የሚመታበት ዓመት እንዲሆንላችሁ ምኞታችንን እንገልጽላችኋለን።

በጋራ ተባብረን በመረዳዳት የምናደርገው ሁሉ ጥሩ ውጤት እንዳለው እንዲያስታውሰን የውድ እህታችንን የአልማዝ ደምሰውን ፎቶ በሽፋናችን ላይ አውጥተነዋል። ዛሬ "እነሱ ተበታትነዋል፤ ምን አቅምና ዶሞጽ አላቸው?" በሚል የንቀት ስሜት በሚመስል "አልማዝን ራሷን ገድላ ነው፤" በማለት ገዳይዋ እንዳይገኝ ተሸፋፍኖ ሊያልፍ የነበረው ጉዳይ ሁላችንም ከያቅጣጫው ባደረግነው የአቤቱታ ግፊት ምርመራው እንደገና እንዲካሄድ መወሰኑ የኅብረትን ጥቅም ያስታውሰናል። አሁንም በጋራ የምናደርገው ግፊት የአልማዝ ጉዳይ በትክክል እንዲጣራ ከማድረግ ባሻገር ወደፊት የምንደጋገፍና የምንተሳሰብ መሆናችንን በመረዳት የሚንቁን እንዲያከብሩን፣ ሊያጠቁን ያሰቡ እንዲጠነቀቁ ያደርጋቸዋል።

---

በችግርም ሆነ በደስታ ጊዜ መገናኛና መረዳጃ ሁኔታዎች ባልተደራጁበት ቦታዎች በአንዱ ወገናችን ላይ አደጋ ቢደርስ ሊፈጠር የሚችለውን ሁኔታ አጢነን መሰባሰብና መገናኘት አለብን። በሲያትል ዋሽንግተን ተገድሎ አስከሬኑ ወሳጅ በመጥፋቱ ሊቃጠል የነበረው የወንድማችን የመስፍን መንገሻ ታሪክ ብዙ ትምህርት ይሰጠናል። አስክሬኑን ወደ ዘመዶቹ ለመላክ የሚያስችል ገንዘብ እስኪሰበሰብ አንድ ወር ሙሉ መቆየቱ ምን ያህል ይሰማን ይሆን? ለዚህ ጉዳይ በራሷ ጥረት ተነሳስታ በየቦታው በመዞር ዕርዳታ ጠይቃ አስከሬኑ ለዘመድ እንዲደርስ ያደረገችው፤ ከመጣች አራት ዓመት ብቻ የሆናት የ24 ዓመቷ ወጣት ኤልሣቤጥ ገበየሁን በ"እናስተዋውቃችሁ" አምዳችን አቅርበናታል። የመረዳጃ ማህበራት ወይም የኮሚኒቲ ማህበራት ቢኖሩ ይህ ችግር ባልተፈጠረ፤ ኤልሣቤጥም ሥራዋን ትታ በየቦታው በመዘዋወር ባልተቸገረች ነበር። የኮሚኒቲ ማህበራት በሥርዓቱ ተደራጅተው ካሉባቸው ከተሞች እንማርና እንሰባሰብ፤ እንደራጅ። አንድ የሚያደርጉን ብዙ ነገሮች አሉ። መጠነኛ ልዩነቶቻችንን እናጉላ። ከstate ደረጃ አልፈው በregion ደረጃ በመደራጀት ላይ ያሉ ምናልባትም የወደፊቱ "የአህጉራዊ ኢትዮጵያውያን ማህበር" እስኪል የሚሆነውን ማህበር የፈጠሩት የመካከለኛው ምዕራብ አሜሪካ ኢትዮጵያውያን ትልቅ ትምህርት ይሰጡናል። እዚህ የሚደርስብንን ችግር በጋራ ለመወጣት ከመተጋገዝ ባሻገር፤ በአገር ቤት የሚደርሰውንም ችግር የምንረዳበት፤ የሚፈጠሩትንም የሰብዓዊ መብት ረገጣዎች አጋልጠን የምናሰማት አህጉራዊ የብዙሃን ማህበር መኖር ትልቅ አስተዋጽዖ አለው እንላለን።

የ"ላንዳፍታ" መጽሔት ይህንን የመሰባሰብ የመደራጀት አስፈላጊነትን ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የእንደዚህ ዓይነት ማኅበራት አስፈላጊነትን በመጥቀስ የምንወያይበት፤ ከተደራጁት ልምድ የምንካፈልበት "ትኩረት" የሚል አምድ ከሚቀጥለው እትም ጀምሮ ትከፍታለች። እንግዲህ እንጠቀምበት።

---

በዚህኛው እትም የ"እስፖርት አምድ" ጀምረናል። በየአካባቢያችሁ ስላለው የእስፖርት እንቅስቃሴ ዘገባችሁ ከፎቶግራፎች ጋር ላኩልን፣

---

ማሳሰቢያ – በ"ላንዳፍታ" ላይ የሚቀርቡ የግል አስተያየቶችና ቅሬታዎች፣ የሚቀርቡ ሃሳቦች (ከዝግጅት ክፍሉ ቅንብሮች በስተቀር) የመጽሔቱን አዘጋጆች አስተያየትና ሃሳብ ላይወክሉ ይችላሉ። ቅሬታ የተጻፈባቸው ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች መልሳቸውን ለመስጠት መድረካችን ክፍት ነው።

እንኳን
ከዘመን ወደ ዘመን
በሰላምና በጤና
አሸጋገራችሁ !!



## እስቲ አንቺ መስከረም !

እፈራለሁ እንዳትሆኚ
        እንዳለፉት መስከረሞች፣
ዘመን ከፍተው ወራት መርተው
ልብ አድምተው ህዝብ አጥፍተው
        እንደሄዱት ያንቺ ዓይነቶች።
ዘንድሮ እንኳን ቀና ብለሽ
ህዝባችንን ቀና አድርጊው፤
        የሠላም ወር መጣሁልህ
        እንባህ ይድረቅ በቃህ በይው።
እንደአበባሽ ትኩስ ሽታ
        ዘመኑንም ደግ አድርጊው፤
ስቃይ የለም ሞትም ሞቷል
        . . . ጠፍቷል በይው።
በቄጤማሽ በለምለሙ
        መራርቂና ቸብ አድርጊው፤
እንዳለፉት ሃያ ዓመታት
        ምስኪኑን ህዝብ አታሣቂው።
ከፊት ሆነሽ ወራት መርተሽ
ሰላም ደስታ እንዲታደል
        የኖህ እርግብ ገድ ወፍ ሁኚው።
        ውብ መስከረም ቀደምት ወራት
የአበቦች መፈንጠቂያ፣
የወራቶች በር መግቢያ።
        ፍሬዎች ልጆችሽን፣
        ቀሪ ወራት ያጀቡሽን፤
ገድ ፍኖት ሁኚላቸው
አንቺ ቀንተሽ ቀኝ አርጊያቸው።

እንቁጣጣሽ

በያመቱ


ያምጣሽ !




አዲሱ ዓመት
የሰላምና የጤና
የብልጽግና ይሁንላችሁ !

፲፱፻፹፮

ግጥም – ግርማ ዘገዬ



# ደ ብ ዳ ቤ ዎ ች



ለላንዳፍታ የመጽሔት አዘጋጆች ሰላም ለናንተ ይሁን፣ እንደምን አላችሁ? መጽሔታችሁን ሳይ ደስ አለኝ ገልበጥበጥ አድርጌም ተመለከትኳት የተደሰትኩት በመጽሔቱ ውስጣዊ ይዞታ አልነበረም ታድያ በምንድን ነው? ትሉኝ ይሆናል የሐገሬ ብሔራዊ ቋንቋ በሌላውም አለም እትመት ላይ በመዋሉ ነው። ይህንን መፅሔት አቀናብራችሁ ለእትመት ያቀረባችሁት ባልላሳት ኢትዮጲያዊያን ናችሁ ብዬ ገምቻለሁ። ታዲያ ኢትዮጲያዊ የሆነ ሁሉ የኢትዮጲያ ጉዳይ ያገባዋልና ምነው? እናንተም ሆናችሁ የመጽሔት ደንበኞቻችሁ አገራችሁን ኢትዮጲያን ችላ ያላችኋት ትመስላላችሁ። ነው? ወይስ የኢትዮጲያ ችግር ሁሉ ተሟጦ አልቋል? ስለኢትዮጲያ የሚጻፍ ነገር የለም ብላችሁ ነው? ኸረ ችግር ሞልቷል። ለልጅ ልጅ ይተርፋል። ከዛው ከችግሩ ጉራ አካባቢ በቅርቡ ነውና የመጣሁ እኔ ላውራላችሁ። የኢትዮጲያ ተሟጦ ያለቀው ሐብቷና ንብረቷ እንዲሁም ውድና ሃሳቢ ልጆቿ ናቸው እንጂ ችግሩ ከድረው በግምት በ10 እጥፍ ጨምሯል። ጦርነቱ፣ ረሐቡ፣ እራናው፣ ጫናው፣ ዘረኝነቱ፣ ጐጠኝነቱ፣ መለያየቱ፣ መበታተኑ፣ መራራቁ፣ እምነት መጥፋቱ፣ ዘወትር በስጋት መኖሩ፣ የአገሪቱ ሉአላዊነት መጥፋቱ፤ ውድ አርበኞች ልጆቿ በደማቸውና በአጥንታቸው ነፃ ካወጧት በኋላና ከነፃነትም ማግስት በልማቱ ጉዳና ተሰልፈው የሰበሰቡላትንና ያከማቹላትን አንጡራ ሐብቷን ሲያመችም በግልጽ ሳያመችም እንደተራ ሌባ ጨለማን ተገን በማድረግ ወዳልታወቀ ቦታ ተጉዞ አልቆ አገሪቱ እርቃኗን መቅረቷ ይህ ሁሉ ችግር ነው። ውድ አዘጋጆች ብዙ በሃገር ውስጥ ያሉ የመጽሔት አዘጋጆች ካለው ችግር በመነሳት በፖለቲካ ውስጥ Involve ማድረግ አንፈልግም ይላሉ። ይሁን እንጂ ያ ሁሉ ችግርና ጫና እያለባቸው እንኳን ስለሃገር ጉዳይ ያልጠቃቀሱበት አንድም እትም የለም ሐገር ናትና። እናንተ ግን በነፃውና ዲሞክራሲ ሰፍኖበታል በምትሉት ትልቅ አገር ውስጥ እየኖራችሁ በመጽሔታችሁ ላይ በመጠኑም ቢሆን የሃገርን ጉዳይ መጠቃቀስ ሲገባችሁ በሁለተኛ ደረጃ መታየት በሚችለው የማህበራዊ ችግር ላይ እጅጉን ማትኮራችሁ እናንትን አዘጋጆችንም ሆነ በአሜሪካ ውስጥ የሚኖሩትን ኢትዮጲያዊያን በትዝብት ዓይን እንድመለከት አድርጎኛል። ይህን ስል የሃገራችን ችግር በኛ መጽሔት ተገለፀ አልተገለፀ ምን ለውጥ ያመጣል ልትሉ ትችላላችሁ። ግን መጽሔት ለዜና ማሠራጫ መሣሪያዎች አንዱ እንደመሆኑ መጠን ሌላ ነገር ማድረግ ባይቻል እንኳ ኢትዮጲያ ውስጥ ከዕለት ዕለት የሚፈጠሩትን ችግሮች እየተከታተላችሁ ለህዝብ እይታ ብታበቁት ሕዝቡ ደግሞ እግዚአብሔር ኢትዮጲያን በምህረት ዓይኑ እንዲመለከታት ቢያንስ በፀሎት ይማፀናል። በወደፊቱ እትማችሁ ላይ ምክሬን ተቀብላችሁ ይህን ካደረጋችሁ ቅመም ወጥን የሚያጣፍጠውን ያህል ዝግጅታችሁን ፍሬያማ ያደርገዋል። የመጽሔታችሁ አፍቃሪዎችም ቁጥራቸው እየተበራከተ ይሄዳል። ይህን ካላደረጋችሁ ግን ሁሌ አልጫ መብላት ለኢትዮጲያዊያን ይሰለቻልና እናንተም አስቡበት። ይህን ለእትመት ካበቃችሁት ለወደፊት በደንበኝነቴ የምቀጥል መሆኔን ቃል እገባለሁ።

ዶክተር ታሪክ ታደሰ (ኒውዮርክ)

---

ለምወዳት ለላንዳፍታ መጽሔት አዘጋጅ፤ ለመጽሔቷ ያለኝ የፍቅርና የጉጉት ሰላምታዬ ካለሁበት በተዳርቦ ይድረሳችሁ። በላንዳፍታ 2ኛ ዓመት ቁጥር 2 July '93 ላይ የሠፈረውን ወቀሳና ዘለፋ ተመልክቼ ለተወሰኑ ቀናት አሳርረውኛል። ያለማወላዳት የጽሑፉ አንጡራ ባለቤት የዛሬው ወንጀለኛ ዘውዱ እሸቱ ነኝ። ወንድሜ ከሁለቱ አቆጣጠር አንዱን እንኳን ሳይለዩ 1980ን በመጥቀስ ግራ አጋብተውኝ ነበር። እኔ የጻፍኳት በአገራችን አቆጣጠር 1977ዓ.ም በኢትዮጲያ ማለትም በጋሞ ጎፋ ክ/ሀገር አርባ ምንጭ (ሴቻ) ከተባለው ከተማ ፊንጠር ብሎ ከሚገኘው የኢትዮጲያ ትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን (ኢ.ት.ኮ.ባ.), (E.T.C.A.) መ/ቤት ውስጥ የክ/ሀገሩ የጥገና ክፍል Clerk I. ሆኜ በምሠራበት ወቅት ነው። በጊዜው በመስክ ሠራተኞች እጥረት መንስዔ የክፍል አለቃዬ የነበሩት አቶ ዮሴፍ ግርማ በአርባ ምንጭና በኰንሶ መካከል መንገዶችና ፎርዶችን በበላይ ተቆጣጣሪነት እስጠግን ዘንድ ከተገቢው የመስክ ማቴሪያሎች ጋር ልከውኝ ከተከልኳት ድንኳኔ ፊት ለፊት የበረሃ ሀሩር እየጠበሠኝ ሣለ ነበር። ጽሑፍን ዛሬ ከሞላ ጐደል በውል ለማላስታውሳቸው የአገር ቤት ባልንጀሮቼ አስቀድቻለሁ። ኬኒያም በስደት ላይ ሳለሁ እንደዚሁ እዚህም ያነበብኩላቸው ይገኛሉ። በሌላ እስቴቶችም ጽሑፍ ዛሬም አለችኝ። ያኔ በመጽሔት እንዳላሳትማት፤- 1. ጋሞ ጎፋ ጽሑፍ በመጽሔትና ጋዜጣ ከዚያው አካባቢ ያልጎለበተባትና ኋላ ቀርም በመሆኗ። 2. በጊዜው የነበረው መንግሥት ከሚያሳድረው ተፅዕኖ ሌላ ቢወጣ እንኳን የሚያስቀጣ ስለመሠለኝ ለማስታወስ ሻለቃ ዓሊ ሙሣ፣ አቶ አማረ ገ/ ኪዳን፣ አቶ እንዳለ ተሠማ፣ (የሃገር አስተዳደር ሚ/ር የነበሩት) አቶ ስምዖን ጋሎሬ፣ ሌሎችም በደርግ ፖለቲካ የተጫወቱበት ክ/ሀገር ስለነበርኩ ነው።

ጽሑፎን ለመጻፍ የበቃሁት በጊዜው የሥራ አጥነት መስፋፋት የአገሬን ወጣት ለመጠጥ፣ ለዕፅ፣ ለዝሙት ለስርቆትና ለጸብ ወንጀል ስለዳረገውና ሥራ የሚገኝ የነበረው 1. ወይ እናት ወይ እህት በሩካቤ ስጋ ግንኙነት፣ 2. በባለሥልጣን ዘመድ ተገንነት 3. በገንዘብ 4 በሆነ ነገር ታዋቂነት ያለው ሰው ዘመድ ወይም ባልንጀራ ውለታ በመስራት ከተሆነ ስለነበርና በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ለመግለጽ መሞከሬ ስለነበር ነው። እኔ የዋህነቴና ለግጥሟ ክብደት ባለመስጠቴ እንጂ ለብዙ ሰዎች አሳልፌ ሰጥቼ ሌላው ግምት ቀርቶ ለዛሬው ቅሌትም ባልበቃሁ ነበር። ወንድሜ ፀጋዬ አደፍርስን የምለምናቸው የሁለታችንም የሥነ ፅሑፍ ችሎታ ስሜን ባጠፉባት የላንዳፍታ መድረክ ይለካ ዘንድ አዘጋጆች ብታሳስቡልኝ ከልብ አመሰግናለሁ። ለእንግሊዘኛቸውም ምስጋናዬ አይለያቸው።

ውድ አዘጋጆች አሁንም አንድ ፅሑፍ ልኬላችኋለሁ። ዋናው አዘጋጅ እዚህ ያሉ መስሎኝ Mail Box ውስጥ ያስገባሁ ዕለት በሥራ ጉዳይ ወደ አሁን አድራሻቸው እንደተዛወሩ ሰማሁ። የቅርብ ቤተሰቦቻቸውንም አነጋግሬ አልደረሰንም ተባልኩኝ። ለማንኛውም አሁን ልኬያታለሁና መልካም ፈቃዳችሁ ከሆነ ብታወጡልኝ።

## ተመንደጊልኝ !

ክልብ የመነጨ ይድረስሽ ሠላምታ፣
እጅግ ለምወድሽ ብርቅዬ ላንዳፍታ።
ካልገባሽ ላስረዳሽ እንዴት እንደሆነ?
ነጥብሽ ከፖለቲክስ ነፃ ስለሆነ!
ለዚህ ነው በሁሉም ስምሽ የገነነ፣
ሁሉም ያነብሻል ጊዜ እያባከነ።
በሥራ በትምህርት የደከመ አዕምሮ፣
ይበረታል ባንቺ ይዝናናል ጠንክሮ።
ቁም ነገሮችሽን አዝለሽ ስትመጪ፣
ታደርጊያለሽ ሠውን አዳዲስ አመንጪ።
የቃላት ሰንጠረዥ ቅኔና ተረቶች፣
በጉ አስተያየቶች ቀልዶችና ግጥሞች፣
ገጠመኞችና እናውንስመንቶች፣
መቼ ይኼ ብቻ እንዲሁም ሌሎች ሌሎች።
ስለምታመርቺ ልዩ ልዩ ቃሎች፣
ልዩ ሆነሽብኛል "ላንዳፍታ" ከሌሎች።
እያበጠርሽልኝ ዕውነቱን ከውሸት፣
የምርተ- ቃልሽም ጨምሮ ጥራቱ፣
እያሣሠብኩ ካሁን እስከ ወደፊቱ፣
ላይሽ እወዳለሁ ጎልብተሽ በዕውቀቱ።
በዚህች አጭር ፅሑፌ ደህና ሁኚ ስልሽ፣
እስክትመጪልኝ ነው ደግሞ እንደልማድሽ።
እንግዲ በርቺልኝ እያልኩኝ "ላንዳፍቱ"፣
የምሠናበትሽ ዘውድዬ እሽቱ።
ዘውዱ እሸቱ (ቺካጉ/ኢሊኖይ)

---

ውድ የላንዳፍታ መጽሔት አዘጋጆች፤ ከሁሉም አስቀድሜ የማክበር ሰላምታዬን ለእናንተ ተስፋዬን ላለመለመችው መጽሔታችሁ ደግሞ ያለኝን አድናቆት በዚች ደብዳቤዬ አማካይነት አቀርባለሁ። ባጋጣሚ ሆኖ 2ኛ ዓመት ቁጥር አንድ መጽሔታችሁን በእጄ ትገባለች። መጽሔቱን ሳገላብጥ "ሁለት ያጣ ዕውነተኛ የፍቅር ታሪክ" የሚል ርዕስ ትኩረቴን ሳበውና ሳላመነታ ማንበቡን ተያያዝኩት። እንብቤ ስጨርስ ከበስተግርጌው ያለውን የጸሐፊውን ስም (ደምሌ እያሌው) ሳይ ሰማይ ምድሩ ዞረብኝ። ወድጄ አልነበረም። ደምሴ እያሌው የሚባል ወንድም አለኝ። ከ4 ዓመት በፊት እናንተው ጋ አሜሪካን ነበር። ሆኖም ደብዳቤው እኔም ሆንኩኝ ቤተሰቦቼ በማናውቀው ምክንያት ከተቋረጠ ድፍን 4 ዓመት ሆኖታል። በመሆኑም ወንድሜ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ ስላልቻልን ጭንቀታችን ወሰን አልነበረውም። ስለዚህ ውድ አዘጋጆች የደምሌ እያሌው አድራሻ በመጽሔታችሁ አማካይነት እንደሚደርሰኝና የእኔም አድራሻ እንደሚደርሰው ሙሉ እምነቴ ነው። ለምታረጉልኝ ትብብር በእኔና በቤተሰቦቼ ሥም አስቀድሜ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ሕይወት መንግሥቱ ለማ

ከአዘጋጁ፤- ለደምሌ ተነግሯቸዋል።

---

ለላንዳፍታዎች የከበረ ሰላምታዬ ካለሁበት ይድረሳችሁ እላለሁ። በመቀጠልም ስለእናንተ ያለኝን አስተያየት እንደሚከተለው አቀርባለሁ። መጽሔታችሁ ጥሩ ጅምር ስለሆነች ሳትሰለቹ በርቱ፣ ግፉበት። መጽሔታችሁ ትምህርት ሰጪና አዝናኝ ነች። ነገር ግን አንድ ቅር ያለኝ ነገር ቢኖር መቼም እንደምታውቁት አሜሪካንን ብናውቃት በየዕለቱ የተለያዩ አዳዲስ የሳይንስ ግኝቶች ከሚገኙባት አገሮች መሃከል አንዷ መሆኗ ይታወቃል። ስለዚህ እባካችሁ ላንዳፍታዎች በአሜሪካም ሆነ በሌላው አገር የሚከሰተውን የተለያዩ አዳዲስ ግኝቶችንና ፈጠራዎችን በመጽሔታችሁ ብታሳውቁን ጥሩ ነው። በአጭሩ ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ የምታገኙትን መረጃዎች በመጽሔታችሁ ጨልፋችሁ እንድታወጡልን አደራዬ የጠበቀ ነው።
ከበደ ገብረ ማርያም (ገብረ ጉራቻ-ሰሜን ሸዋ)

---

ይድረስ ለ"ላንዳፍታ" አዘጋጅ:-በጉጉት የምጠብቃት ላንዳፍታ ብትዘገይም ትዕግሥቴን አስጨርሳ ደርሳኛለች። በሰኔ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር 2 እትማችሁ ልዩ ክፍል ስለእህታችን አልማዝ ደምሰውና ስለወንድማችን ሉልሰገድ ገ/ሕይወት አሰቃቂ አሟሟት የአቀረባችሁት በወገን ተቆርቋሪነቴ እጅግ በጣም ተሰምቶኛል። ከዚሁ ጋር አያይዤ እኔም በበኩሌ የምኮራበት ላንዳፍታ ምናልባት ትረዳኝ ይሆናል በማለት ችግሬን በይፋ ለማውጣት ተገድጃለሁ።

በአሜሪካ አገር በካሊፎርኒያ እስቴት በ"Venice" ከተማ ኗሪ የነበረ ጓደኛ ነበረኝ። በመጨረሻ የደብዳቤ ልውውጥ የአደረግነው በJanuary 01/1990 ሲሆን አሜሪካ ከመጣሁበት ከDecember 18/1990 ጀምሮ በሰጠኝ አድራሻና ስልክ ቁጥር ለመገናኘት ሙከራ ባደርግ ደብዳቤው ተመላሽም አልሆነም፣ መልስም ማግኘት አልቻልኩም። ስልኩም አልሠራልኝም። በመጨረሻ ተስፋ በመቁረጥ ጉዳዩን ለማጣራት ወደአዲስ አበባ ግንኙነቴን በመቀጠል ሞከርኩ። ወንድሙ እንደገለፀልኝ ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን ሰምቻለሁ። መቼ፣ የትና በምን ምክንያት እንደሞተ አብራርቶ የሚነግረኝ ስለአጣሁ ተስፋ ቆርጬ ተቀምጫለሁ። በሀበሻ አጠራሩ ጋሻው አበጋዝ፣ በአሜሪካ አጠራሩ Tarek Abegaz ሲሆን እኔ በመጨረሻ የማውቀው አድራሻ:- Tarek Abegaz 1002 5th Ave.#4 Venice, CA. 90291 U.S.A (001213) 399-5127 ስለዚህ ይህን አቤቱታ ተቀብላችሁ ግለሰቡን የሚያውቁት የወገን ተቆርቋሪዎች ለእኔም ሆነ ለወላጅ ዘመዶቹ ቢያሳውቁን የዘወትር ምኞቴ ሲሆን ለላንዳፍታ አዘጋጅም ለትብብሩ በቅድሚያ አመሰግናለሁ። ቸር ይግጠመን ደህና ሁኑ!!
ደንበኛችሁ ጫኔ ቢሆነኝ (ዋሽንግተን ዲ.ሲ)

ከአዘጋጁ፤- ፎቶው በጣም ጉልህ ስላልሆነ አላወጣነውም።

---

ለላንዳፍታ መጽሔት ዋና አዘጋጅ በመጀመሪያ የከበረ ኢትዮጲያዊ ሰላምታዬን ለእርሶና ለመጽሔቱ ዝግጅት ተባባሪዎች እንዲሁም በመላው አሜሪካ ለሚገኙ ኢትዮጲያዊያን አባቶቼ፣ እናቶቼ፣ ወንድሞቼና እህቶቼ አቀርባለሁ። ላንዳፍታ መጽሔት ቁጥር 4 እና ቁ.5 (2ኛ ዓመት ቁ.1) በጓደኞቼና በምሠራበት መ/ቤት ላይብረሪ አነበብኳት። በእውነቱ በጣም የሚረዳና ጠቃሚ፣ ትምህርት ሰጪ ሆና አግኝቼአታለሁ። ከእንግዲህ ቋሚ ደንበኛችሁ መሆኔን በደስታ እገልፃለሁ።ላንዳፍታ ላይ የቀረበው የሬጀንት ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ታሪክ በእውነቱ ሀገራችን በዚህ አሳዛኝና አስቸጋሪ ጊዜ እውነትም የምትኮራባት እሳቸውን የመሳሰሉ ታላቅና ክብር ኢትዮጲያዊ በመኖራቸው እኛ ልጆቻቸው ከልብ እንኮራለን። የእርሳቸውንም አርአያነት ተከትለን አባቶቻችን ያስረከቡንን ኢትዮጲያን ታሪኳን፣ ባህሏን፣ ቅርሷን በተለይም ዛሬ በከሃዲዎች በመካሄድ ላይ ያለውን የተንኮል ሤራ አክሽፈን አንድነቷን አስጠብቀን ለማኖር ዝግጁ ነን።ውድ አዘጋጅ በዚህ አጋጣሚ ለእኚህ ውድ የኢትዮጲያ ልጅ የአፍሪካ ምሁሮች በተለይ አሁን እዚህ ሆነው በእውነተኛነት ለኢትዮጲያ ህዝብ እየታገሉ ያሉት ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስን፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ ማርያምና ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራን ያለኝን እጅግ የላቀ ታላቅ አክብሮት በእናንተ በኩል አድርሱልኝ። የኢትዮጲያ አምላክ ይጠብቃችሁ፤ ጌታ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን በሉልኝ። በተረፈ መላው የኢትዮጲያ ህዝብ በሃሳብም በፀሎትም ከእናንተ ጋር ነው በሉልኝ። እናት ኢትዮጲያን የሸጧት፣ የከዷት፣ ያዋረዷት ደግሞ የሥራቸውን አያጡትም። ጊዜ ይወስዳል እንጂ። መልዕክቴን አደራ አስተላልፉልኝ። በእግዚአብሔር ስም እለምናችኋለሁ አደራ! አደራ!!
ጌታቸው በቀለ (አዲስ አበባ)

---

ላንዳፍታዎች፤ ሰላም ለእናንተ ይሁን አሜን! ባጋጣሚ ቁጥር "4"ን ወንድሜ አምቦ አመጣልኝ። አሁን ስንተኛ እትም ላይ እንደደረሳችሁ ባላውቅም፤ የአቀራረባችሁ ኅብር በጣም ደስ የሚያሰኝና የሚስብ ነው። በተለይ የኢትዮጲያን ኮሚኒቲ ሕይወትን በአሜሪካ የሚያሳየው አምድ በጣም የሚጥም ነው። የምታስነብቡን የመተጋገዝ ብስራትንና ያላችሁ ፍቅር እንባ ያስቀርራል! ወላዲት አምላክ ታዝልቅላችሁ። ኢትዮጲያዊ በመሆኔ በአኩሪ ሥራችሁ ረካሁ። ኮራሁ! በርቱ። የፍቅር፣ የሰላምና የአንድነት አስኳልነታችሁ እንዲህ ሁሌ ለዓለም አሳዩት።
ወጣት ፋሲል ተፈራ (ከአምቦ ሀገረ ሕይወት)

---

ለላንዳፍታ መጽሔት፤ "ዳሎል የተከፋፈለው በዘር ልዩነት አይደለም: በሚል ርዕስ ከዝግጅት ክፍሉ የቀረበው እሰየው አሰኝቶናል። ብዙዎቻችን ዳሎል በሚባል የሚታወቀውን የሀገራችን ልጆች ባንድ በሀገርም ሆነ በውጭ ዕድሉ ያጋጠመን በመድረክ ላይ ሲጫወቱ ተመልክተናል። አንዳንዳችንም በካሴት፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔት ሰምተናቸዋል። ግራም ነፈሰ ቀኝ ሁለቱ ቡድኖች በመለያየታቸው ምክንያት ያልገባቸው ሰዎች በተለያየ መንገድ ተርጉመውት ነበር፤ አሁን ግን እንደዚህ አይነቱን ሀቅ ላንዳፍታ ያወጣው ስለሆነ ለሁለቱም ቡድኖች የምሰጠው ምክር ለወሬኛ ቦታ አትስጡ እያልኩ በመጽሐፉም ላይ እንደተገለፀው ባንዲራቸውን ለብሰው ሲጫወቱ በየጊዜው የምናየው ነውና በርቱበት እያልኩ ለላንዳፍታና ለዝግጅቱት ክፍሉ ምስጋናና ዕድሜ እየተመኘሁ በዚሁ የምሰናበታችሁ የክለቡና የባንዱ ደንበኛ ወንድወሠን ይመር (ቺካጎ) ነኝ።

---

ሰላምታዬ አይለይህ የሩቋ! ለምን የሩቋ ብዬ እንደሰየምኩህ ሳትረዳኝ አትቀርም። በሺዎች የሚቆጠር ኪሎ ሜትር ተራርቀን የምንገናኝ በመሆናችን፤ በወረቀት ላይ ቀለም አፍሰን ሃሳብ ለሃሳብ የምንገናኝ፣ የምንለዋወጥ ነንና ርቀቱ የትዬለሌ ሆኖ ታይቶኝ ነው። በዚህ ከተግባባን ወደዋናው ቁምነገር ልግባ። ለመጀመሪያ ጊዜ መፅሔታችሁን "ላንዳፍታ" 2ኛ ዓመት ቁጥር 1

ከፊት ሽፋን ጀምሬ ውስጧን ይዘትዋን አጣጥሜ አነበብኳት። ይህ ከዚህ ሳይባል አርክታኛለች። ስለዚህም የመጽሔታችሁ እድምተኛ ለመሆን ተነሳስቻለሁ። መቼም አንድ ሰው አዲስ ቤት ለመመረቅ ሲሄድ በአገራችን ወግና ባህል መሠረት የቤት ለንቦሳ ምናምን ተይዞ ነው። በመሆኑም እኔም ወደእናንተ ስገባ ሲያጐርሱት ያላጐረሰ ከቀማኛ አንድ ነው እንደሚባለው የአበው ምሳሌ እንዳይሆንብኝ "የአበው ቅርስ" ለሚለው አምዳችሁ ተስማሚ ትሆናለች ብዬ ያሰብኳትን ከአንድ መጽሔት ያገኘኋትን ፅሑፍ ልኬልሃለሁና ተቀበለኝ። ጽሁፉን በደብዳቤው መጨረሻ ታገኛታለህ።

ንጉሡ ሰሙ (አዲስ አበባ)

---

ይድረስ ለ'ላንዳፍታ' መፅሔት አዘጋጅ:- ሠላምታዬ በአየር ይድረስህ። እንደምን አለህ። ሰላምና ጤና ምን ጊዜም ካንተ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔርን እማፀናለሁ። የዘወትር ምኞቴ ነው። "ያላዩት አገር አይናፍቅም" እንዲሉ በሃሳብ ወደአንተ የምታሻግረኝ ድልድይዋ መጽሔትህ ላንዳፍታን ባላገኝ ኖሮ ስለአንተ ያለኝ አመለካከት ባልፀና ነበር። እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። የ1985 ቁጥር 4. መፅሔትህ በአጋጣሚ ከእጄ ገብታለች። እዚህ አገር ቤት መጽሔትህ በብዛት አልተሰራጨም የሆነው ሆኖ እኔን በለስ ቀንቶኛል። በሳቅ ልብን እያፈረሰች፣ በእውቀት አዕምሮን እየገነባች፣ በደስታ እያስፈነደቀች፣ በቁም ነገር እያዋዘች ካንጀት የምትጐዘጐዝ ፍትፍት የሆነች መጽሔት ናት። ፍፁም የምትወደድና የማትሰለች መጽሔት ናት። ብቻ አድናቆቴን ለመግለፅ ቃላት ያጥሩኛል ከሚነሳ በቀር የሚጣል የለባትም። በብዙ መንገድ ከማደንቃቸው አምዶች "ዘሬን አትጠይቁኝ" "አሜሪካም መጣን" እና "ጓደኛ ለሚፈልጉ" የሚሉትን ለአብነት ያህል ናቸው።አዘገጃጀቱ ለየት ያለ በመሆኑ በሚያነቧት ሰዎች ዘንድ ተወዳጅነትን እንደምታተርፍና ከአንተም ከአዘጋጁ ጐን ለመቆም የሚያቅማማ እንደማይኖር ያለ ጥርጥር በአስር ጣቴ እፈርማለሁ። በርታ። እኔም በበኩሌ ድርሻ ለመወጣት በልብ ወለድ፣ በግጥምና የማውቃቸውን ቁምነገሮች በመላክ ከተከታታይነት ወደተሳታፊነት እንደምሸጋገር ስገልፅልህ ልቤ በደስታ ትዘላለች። እስከዚያው ደህና ሁንልኝ። መጽሔቷን በሴት ፆታ የምጠራት ስለወደድኳት ነው የሚወዱት ሰው ወንዱን እንኳን "አንቺ"እያሉ በሴት ይጠራ የለ እንደዛ ነው። እግዚአብሔር ይርዳን-ከሀይማኖት አከበረኝ(አዲስ አበባ)

---

ለላንዳፍታ መፅሔት አዘጋጅ፤ከሁሉም በፊት ሰላምና ጤና እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞቴን እገልፃለሁ።ጉድ ልንገራችሁ መቼም ትውውቅና ሞት አንድ ቀን ነው ይባላል። ታድያ ይህቺን ደብዳቤ ለእናንተ ከመጻፌ 3 ቀን በፊት ከጓደኛዬ ጋር አንድ ቦታ ተቀጣጥረን በቀጠሮአችን መሠረት በቀጠሮ ቦታ ስጠብቀው እንደአጋጣሚ ቀኑ ኃይለኛ ፀሐይ ያለበት በመሆኑ በአንድ ጥላ ስር ካለች መኪና ተደግፌ ስጠብቀው የመጽሔታችሁ የላይኛው ሽፋኗ ወደ ላይ ተገልብጦ መኪናው ውስጥ አየኋት። ላነባት በጣም ፈለግኩ፣ ጓጓሁ ዳሩ ምን ላድርግ መኪናዋ ተቆልፋለች። የሰው መኪና አልሰብር! በዚህ ሁኔታ ላይ ከወዲህ ወዲያ ስንቆራጠጥ ባለቀጠሮው ጓደኛዬ መጣ። ሁኔታውን ነገርኩት። ታድያ ምን እናድርግ እንሂድ አለኝ። እኔ አልሄድም እያልኩ ስሟገት አንድ የየመንና የኢትዮጲያዊ ዜጋ ድብልቅ የሆነ ወጣት ልጅ መጥቶ መኪናውን ከፈተ። እኔም ተጠግቼ ሰላምታ ከሰጠሁ በኋላ መፅሐፉን ላነብ እንደምፈልግ ገለፅኩለት። "እኔም አላነበብኳትም አንድ ጓደኛዬ ነው ከአ.አ. የላከልኝ ሆኖም ይህን ያህል ከጓጓህ ውሰድና አንብበህ ከ2 ቀን በኋላ መልስልኝ" በማለት የምመልስበትን ቦታ ቀጠሮ ሰጥቶኝ መጽሐፉን አስረክቦኝ ሄደ። ከጓደኛዬ ጋር ወዲያው መጽሔቷን ማገላበጥ ጀመርን። በእውነቱ በውስጧ የተጻፉት ጽሑፎች በትምህርት ሰጪነታቸው፣ በአዝናኝነታቸው የሚማርኩ ናቸው። በጣም ውብ ድንቅ ነች። እኔ በበኩሌ ስሟን ላንዳፍታ ሳይሆን "የማር ጠብታ" ብላት ይሻለኛል። መጽሔትዋ የበሰለች፣ ስሜትን የምትኮረኩር፣ የምታስተምር፣ የምታመራምር፣ ያለፈውን የአሁኑንና የወደፊቱን የምታሳይ ነፀብራቅ ነች።የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል ይሏል ይህ ነው። አቦ አላህ በረካ ያድርጋችሁ። በርቱ ተበራቱ። መጽሔታችሁ አንድ የሚጣል ነገር የላትም። እንግዲህ ሐተታ አላብዛና ያነበብኳት መጽሔት 2ኛ ዓመት ቁጥር 1. የሽፋኑ ፎቶ ሬጀንት ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ የምትለዋ ነች። ስለዚህ የወደፊቱን እትሞች የማገኝበት ሁኔታ ብትገልፅልኝ ከነመላኪያው ለመላክ ዝግጁ ነኝ። አደራዬ በዚህ በኩል የጠበቀ ነው። ኢንፎርሜሽኑን በአድራሻዬ ላኩልኝ። የምኖረው በመካከለኛው ምስራቅ ግዛት በአገረ የመን ሰንዓ ከተማ ነው። በመቀጠልም መጽሔቷን ተወዳጅ ካደረጋት ዓምድ አንዱ የትውውቅ ዓምድ ስለሆነ እኔና ጓደኛዬ ከዚች ደብዳቤ ጋር ልከናልና ለየባለአድራሻዎቹ ላኩልንና ውጤቱ ካገኘን መጽሔትዋ እግረመንገዷን ባለውለታችንና አለኝታችን ትሆናለች።

ከተፈራ ተ/ ኃይማኖት (የመን-ሰንዓ)

---

## ውድ አንባቢያን

የተላኩልንን ደብዳቤዎች በሙሉ ለማውጣት ቦታ ያንሰናል። በሚቀጥሉት እትሞች እናወጣለን። ታድያ አጠር አጠር አድርጉት።

---

## CALIFORNIA MART

2080 Cheshire Bridge Road
Atlanta, GA 30324

ካሊፎርኒያ ማርት

የቅቤ ማንጠሪያ
ሽንብራ
ስንዴ
ምስር
ጤፍ
ቅቤ
አይብ
ድርቆሽ
ዳቦ ቆሎ

የክትፎ ሥጋ
የጥብስ ሥጋ
የጥሬ ሥጋ

እንጀራ
በርበሬ
አዋዜ
ሚጥሚጣ
የሻይ ቅመም
ናና
ጥቁር አዝሙድ
ነጭ አዝሙድ

ሱቃችንን ጎብኙ።

(404)320-6747

## GHION ETHIOPIAN RESTAURANT

BREAKFAST - LUNCH - DINNER

Fine Ethiopian Eatery

ጊዮን ኢትዮጵያ

ቁርስ
ምሳ
ራት

ጎብኙን
በአቀራረባችን ትረካላችሁ።

668 Amesterdam Ave.
(Between 92nd and 93rd St.)
New York, N.Y. 10021
(212)875-8722

## TASTE OF ETHIOPIA

ETHIOPIAN CUSINE

197 Auburn Av.
Atlanta, GA 30303
(404)681-9406

ባህላዊ የኢትዮጵያ
ምግብ ቤት
በንጹህ ጤፍ እንጀራ
ምሳና ራት
ምሳ – ከ$4 እስከ $6 ብቻ
ራት – ከ$4 እስከ $6 ብቻ
(ለልዩ ዝግጅት ዋጋችን ለየት ሊል ይችላል)
የምግባችንን ጣዕም ይወዱታል!
ዋጋችንም ርካሽ ነው!
ብቅ ይበሉ!

LUNCH $4.00 TO $6.00
DINNER $4.00 TO $6.00
*(Special order price may vary from the above.)*
Open 11:00 A.M. to 11:00 P.M. 7 days a week

## SWEET AUBURN GROCERY

እስዊት ያበርን
ግሮሰሪ

የጤፍ ዱቄት
በርካሽ ዋጋ

ጠቅላላ የምግብ ዕቃዎች

210 Auburn Avenue
Atlanta, GA. 30303
(404) 577-6756

# የአልማዝ ደምሰው አሟሟት ምርመራው እንደገና ሊካሄድ ነው !

ባለፈው እትማችን በኦርላንዶ ፍሎሪዳ በምትሠራበት ቦታ ሞታ ስለተገኘችው እህታችን አልማዝ ደምሴ ምርመራ መዘጋት ጉዳይ አቅርበን ነበር። "አልማዝ ራሷን ገደለች፤" ብሎ የኦርላንዶ ፖሊስ ፋይሉን መዝጋቱን፣ ዘመዶቿ፣ ጓደኞቿና የትምህርት ቤት ጓደኞቿ አልማዝ ራሷን ልትገድል የምትፈልግበት ምክንያት እንደሌላት በመግለጽ ጉዳዩ በደምብ እንዲጣራ በተደጋጋሚ በማመልከታቸውና፤ በተለይም በየቦታው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ነገሩ ያሳዘናቸው ወገኖች ሁሉ በደብዳቤ፣ በስልክ ባደረጉት የአቤቱታ ግፊት ምርመራው እንደገና እንዲካሄድ የፍሎሪዳ ፖሊስ ኮሚሽነር መወሰኑን ለመረዳት ችለናል። ወንድሟ ኃይሌ ደምሰው ለዝግጅት ክፍላችን በጻፈው ደብዳቤ እንደጠቀሰልን በተደረገው የግል ምርመራ (private investigation) አልማዝ ሕይወቷን ያጣችው በሰው እጅ ለመሆኑ መረጃዎች ተጠናቅረዋል። የኦሬንጅ ካውንቲ ሸሪፍ ቢሮ ከዲቴክቲቮ ባገኙሁት መረጃ መሠረት በማለት የወሰደውን አቋም እንደገና ምርመራ እንዲደረግ የፍሎሪዳ ፖሊስ ኮሚሽነር ማዘዙ አንድ ውጤት ነው። ይህ ሊሆን የበቃው ፍትህ ፈላጊ የሆነው ኢትዮጵያዊ ከያቅጣጫው ያደረገው የአቤቱታ ግፊት ነው። እንዲያ ባይሆንማ ነገሩ ተደባብሶ በቀረ ነበር።

ውድ አንባብያን፤— የትብብርን፣ የመደጋገፍን ጥቅም ከዚህ መማር እንችላለን። ዛሬ እንቁጣጣሽን አብራን ባልዋለችው እህታችን አልማዝ የደረሰው ነገ በኛም ሊደርስ ይችላል። በተለያዩ ምክንያቶች የሚነሱትን ልዩነቶቻችንን እያጉላን ስንከፋፈል ለጥቃት እንመቻለን። በጋራ የምናሰማው ድምጽ ተሰሚነቱ ከፍተኛ ነው። አንድነታችንን የሚያላላውን ነገር ሁሉ መኮነን አለብን። አንድ ካልሆን ደግሞ ድምጻችን አይሰማም፤ ለማንኛውም ነገር። ጥቃትን ማን ይወዳል? ስለዚህም የአልማዝ ጉዳይ ተደባብሶ እንዳይቀር የምናደርገው ጥረት አሁንም መቀጠል አለበት። ወንድሟ ኃይሌ የጻፈውን ደብዳቤ እንዳለ አቅርበነዋል።

"ውድ የላንዳፍታ አዘጋጅ፤— በአልታወቀ ሰው ለጠፋው የእህቴ ነፍስ ምርመራ እንዲደረግ አንተና መጽሔትህ (ላንዳፍታ) ላደረጋችሁት ያልተቆጠበ ጥረት አመሰግናለሁ። እንደሚታወቀው የOrlando ፖሊስ ካለበቂ ምርመራ እህቴ በገዛ እጇ ነው ሕይውቷን ያጠፋችው በሚል ምክንያት ምርመራውን ዘግቶ ነበር። ነገር ግን ከFeb. 23 ጀምሮ እኔ ከቤተሰቤና ከጓደኞቼ ጭምር በመሆን የግል ምርመራ (Private Investigation) በማስደረግ ሕይወቷን በገዛ እጇ ያላጠፋች መሆኑንና በአኳያው ግን ሕይወቷ ያለፈው በሌላ ሰው እጅ መሆኑን ብዙ መረጃዎች ለማግኘት በቅተናል። ለዚሁ ይረዳህ ዘንድ በግል ምርመራ የተፃፈውን ዘገባ አያይዤ ልኬልሃለሁ። ብዙ ኢትዮጲያዊያን ከU.Sና Canada በEthiopian Review ያወጣሁትን የፍትህ ጥሪ (Call For Justice) በመመልከት ምርመራው ይከፈት ዘንድ ለኮንግረስ ተወካዮቻቸው፣ ለAttorney General, ለflorida Governor እንዲሁም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች አቤቱታቸውን አሰምተዋል። አቤቱታቸው የውሃ ሽታ ሆኖ አልቀረም። ትብብራቸችን ባደረገው ጥረት አንድ እርምጃ ተራምደናል። የFlorida Police Commissioner የእህቴ አልማዝ አሟሟት ሁኔታ እንደገና እንዲመረመር ወስኗል። በኢትዮጵያውያን፣ እንዲሁም በሌሎች ጉዳዩ ባሳሰባቸውና ፍትህ ወዳድ በሆኑ ግለሰቦች የታየው ህብረት ለዚህ እንዳበቃን ስገልጽልህ በጣም ደስ እያለኝ ነው። ቃላት የማላገኝለትን ከፍተኛ ምስጋናዬ በናንተም በኩል እንዲደርስልኝ በትህትና እጠይቃለሁ። ወገን ለወገኑ ደርሷል፤ ትብብርም ለዚህ አብቅቶናል በልልኝ። በዚሁ አጋጣሚ ለላንዳፍታ አንባቢዎች ላሳውቀው የምወደው ጉዳይ የፍሎሪዳ ፖሊስ አሟሟቷ እንደገና እንዲመረመር ውሳኔ ቢሰጥም ጥረታችን እዚህ ላይ መቆም አለበት ማለት እንዳልሆነ ነው። ለጉዳዩ ክብደት ለመስጠት ከዚህ በፊት ውድ የላንዳፍታ አንባቢዎች እንዳደረጉት ሁሉ ለCongress ተወካዮቻቸው፤ በተጨማሪም፤ ለJames T.More, Commissioner & Florida Department Of Law Enforcement P.O.Box 1489 Tallahassee, Fl 32302 እንዲፅፉና ምርመራው በትክክል ይፈፀም ዘንድ እንዲያሳስቡ ያደርጉልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ። ለተደረገልኝ ነገር ሁሉ አሁንም ምስጋናዬ የላቀ ነው። እኔም ሁኔታውን በየጊዜው እገልጽላችኋለሁ።"

ኃይሌ ደምሴ አንዳርጌ (ኦርላንዶ፣ ፍሎሪዳ) ስልክ፤— (407)578-1830

# እናስታዋውቃችሁ

በአሜሪካ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጲያዊያን ቁጥር እያደገ በመምጣት ላይ መሆኑ በጉልህ እየታየ ነው። ይህ በብዛት የተሰደደው ወገናችን በተለያዩ ክፍለ ግዛት ተበትኖ ስለሚገኝና በውል መዝግቦ የያዘው ባለመኖሩ ቁጥሩ ይህ ነው ብሎ ለመገመት ያስቸግራል። በደፈናው ካናዳን ጨምሮ ወደ 200,000 የሚገመት መሆኑ ይነገራል። ይህ ቁጥር እየበዛ በመጣ ቁጥር ችግሩም ያንኑ ያህል እየበዛ ነው። ስለዚህም በየቦታው የሚቋቋሙት የኢትዮጲያውያን ኮሚኒቲ ማህበራት ለሚደርሱ ችግሮች በጣም ጠቃሚ ናቸው እንላለን። የኮሚኒቲ ማህበራት በሌሉበት ቦታዎች ያሉ ወገኖቻችን እንደ ዕድር ዓይነት ስብስብ በመፍጠር የመረዳዳት ተግባራት እያከናወኑ መሆናቸውን ስናይ እንኮራለን። በደስታም ሆነ በሃዘን ብሎም በክብረ በዓላት ወቅት በራሳችን ባህል የምናደርገውን ሁሉ ለመፈፀም የዚህ አይነቶቹ የመሰባሰብና የመረዳጃ ማህበራት ዕድሮች ሆነ የኮሚኒቲ ማህበራት አስፈላጊነት በሰፊው የምናትት ሲሆን በዛሬው ጽሑፋችን ይህ ሁኔታ ጉልቶ በማይታይበት ቦታ ግለሰቦች በራሳቸው አነሳሽነት የሚያደርጉትን አስተዋፅዖ ለማሳየት እንሞክራለን። በተለያየ መልኩ ቀደም ብለው የመጡ ወይም ኋደኛ ዘመድ ብለው የመጡ ወገኖቻችን የሚያውቋቸው ሰዎች ስላሉ ችግር ቢደርስባቸው ጠጋ የሚሉበት ሁኔታ አያጡም። በስደት በተለያየ ቦታ ቆይተው የገቡ፣ ከራሳቸው በስተቀር ማንንም ኢትዮጲያዊ ወገናቸውን ባሉበት ቦታ ለማግኘት ችግር ያለባቸው ወገኖቻችንን ቤቱ ይቁጠራቸው።

እስቲ እንዲህ ባለው ሁኔታ አንድ የደረሰ ታሪክና ለዚህም ችግር በግሏ ተነስታ ከፍተኛ የወገን አስተዋፅዖ ስለአደረገችው ኢትዮጲያዊት እንንገራችሁ።

ኤልሣቤጥ ገበየሁ ትባላለች። የምትኖረው በሲያትል ዋሺንግተን ነው። ኤልሣቤጥ በስደት ከኖረችበት ከኬኒያ ወደ አሜሪካ ከመጣች አራት ዓመትዋ ነው። ቀደም ሲል ካሊፎርኒያ እንደነበረችና በቅርቡም ወደ ሲያትል እንደመጣች ለማወቅ ችለናል። የአዲስ አበባው ልዑል መኰንን ት/ቤትና የጄኔራል ዊንጌት ት/ቤት ተማሪ የነበረችው ኤልሣቤጥ አሁን በሲያትል ሆስፒታል ውስጥ የላብራቶሪ ቴክኒሺያን ናት። በሰንፍራንሲስኮ የተደረገውን የ1993 የወይዘሪት ኢትዮጲያ ቁንጅና ውድድር አዘጋጅ ነበረች።

ስለ ወጣቷ የተባረከ ተግባር ያበሰረንን ከሲያትል ዋሺንግተን የተላከልንን ደብዳቤ ካቀረብንላችሁ በኋላ ከኤልሳቤጥ ጋር ያደረግነው ቃለ መጠይቅ ይቀጥላል።



ኤልሣቤጥ ገበየሁ

---

"ለተከበራችሁ የላንድ አፍታ አዘጋጆች፤

የመፅሔታችሁ የቅርብ ጊዜ ደንበኛ ነኝ። በውነቱ ብዙ ቁም ነገር ያዘለች ነች። እሰየው በርቱ እላለሁ። በሰኔ እትማችሁ ላይ ስለ ሁለት ኢትዮጲያዊያን በፈረንጅ አገር መገደል አንብቤ በሲያትል ዋሽንግተን ውስጥ በጩቤ ተወግቶ ሬሳው መንገድ ላይ ስለተገኘው ስለ 27 ዓመቱ መስፍን መንገሻ ታሪክ አስታወሰኝ። ማንም ስለሱ ያነሳም አለመኖሩ አሳዘነኝ። ከሟቹ ሌላ መመስገን ያለበት ሰብዓዊ የሰው ፍጡር ተረስቷል። ያንን ነፍስና ስጋው የተለየውን በድን ቀባሪ ጨርቅ አልባሽ አጥቶ ሜዳ ወድቆ ሟቹ ምንም ሰው አለማወቁና በቅርቡ ወደዚህ ከተማ በመምጣቱ፣ ሬሳው ቀባሪ ከሌለው ቦታ ስለሚይዝ እናቃጥለዋለን ሲሉ ያች መመስገን አለባት የምላት ልበ ሩህሩህ ኢትዮጲያዊት በየቤተክርስቲያኑ ልመና ገባች። እንዲያውም ወደ ካሊፎርኒያ በራሷ ወጪ ሄዳ በየደጀሠላሙ መለመኗን ሰምቻለሁ። እንዳውም የ"ጊዜ" ሙዚቃ ባንድን ለምና ዘፈን ሲያሳዩ በ Oakland ከተማ ፈቅደውላት ህዝብን ተማፅና ገንዘብ ሰብስባ ባጠቃላይ ከ8ሺ ዶላር ያላነሰ ሰብስባ ያንን ሊቃጠል የነበረ በድን ለናፈቁት እናቱ ልካለች። ይህች ልጅ በእድሜም ልጅ ከመሆኗ አልፎ በፈረንጅ አገርም ብዙ አልኖረችም። እባካችሁ ይህ ሥራዋ በእናንተ የቤተሰብ መፅሔት ይመስገን። በርቺ እንበላት። ከደግ ሥራዋ ሌላ የምትደነቅበት ብዙ ነገር አለ አሉ። እባካችሁ ይህን ድንቅ ሥራ አስተጋቡ። ሞያውን ለእናንተ ትቻለሁ። ስሟ ኤልሳቤጥ ገበየሁ ትባላለች።"

(ተፈራ አየለ ሲያትል ዋሺንግተን)

---

# ከኤልሣቤጥ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ላንዳፍታ:-

ኤልሣቤጥ ይህን በጐ ተግባር ለማድረግ ምን አነሳሳሽ?

ኤልሣቤጥ:-

በእኔ እምነት በዚች ምድራዊ ሕይወታችን ከሞት በላይ አስከፊ ነገር ያለ አይመስለኝም። ከዚያም በላይ የሟቹ በወጣትነት ዕድሜው በሰው እጅ ሕይወቱን ማጣት፤ ዘመድ ወዳጅ፣ ብዙ እንኳን የሚያውቀው ሰው በሌለበት አዲስ አገር መጥቶ በመጣ በሁለት ወሩ ውስጥ መሞት በሰው ልጆች ላይ ከሚደርሰው አሰቃቂ ነገር የመጨረሻው ነው ብዬ ስላመንኩኝ ነው። ምንም እንኳን በሟቹ ሕይወት ላይ ለውጥ ባላመጣም ለብዙ ዓመታት ያላዩት እናቱና አባቱ እንዲሁም ቤተሰቡ በባህላችን መሠረት አልቅሰው ቢቀብሩት ለእነሱ ትንሽም ቢሆን ሃዘናቸውን ይቀንስላቸዋል ብዬ ስላሰብኩኝ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ ወገኔ የአገሬ ልጅ ነው።

ላንዳፍታ:-

ሟቹን ቀደሞ ታውቂው ነበር?

ኤልሣቤጥ:-

አዲስ አበባ ቤተሰቦቹ የቤተሰቦቼ ጐረቤቶች ናቸው። በዓይን ነው የምንተዋወቀው። ኬንያም ሁለታችን በስደት እያለን ተነጋግረን አናውቅም። ሲያትል ከመጣሁ በኋላ ሲያትል መኖሩን ያወቅሁት ከሞተ በኋላ ነው። ተነጋግረን አናውቅም። ከሁሉ በላይ ለኔ ኢትዮጲያዊ የሆነ ወገኔ ሁሉ ባላውቀውም አውቀዋለሁ ብዬ የማምን ነኝ።

ላንዳፍታ:-

ስለአሟሟቱ እንዴት ልትሰሚ በቃሽ?

ኤልሣቤጥ:-

ቤተክርስቲያን ነው የሰማሁት። ፖሊሶቹ አስከሬኑን የሚያደርጉት ጠፍቷቸው (ዘመድ ወገን ስለሌለው) የሚያቃጥሉት መሆኑን ገለፁ። ይህን ስሰማ ደነገጥኩ። "እንዴት ይቃጠላል? በባህላችንም በእምነታችንም የለም፣ እዚህ ወገን ዘመድ የሌለው በመሆኑ ተሰማኝ።

ላንዳፍታ:-

እንደሰማሽ ምን አደረግሽ?

ኤልሣቤጥ:-

ከዚያ አብረውኝ ከነበሩት ሰዎች ጋር ተነጋገርኩና ፖሊሶቹን ደውዬ ለመንኳቸው። የባህላችንና የእምነታችንን ነገር አስረዳሁ። አስከሬኑንም ገንዘብ አሰባስቤ ወደአገሩ እንዲላክ እስከማድረግ ድረስ እንዲያቆዩና እንዳያቃጥሉት ተማጠንኳቸው። እሺ አሉኝ። እኔም መጀመሪያ ባለሁበት በሲያትል ከተማ ዕርዳታ ስብሰባ ጀመርኩ። ሲያትል ከመጣሁ ያኔ ሦስት ወሬ ብቻ ስለሆነ ብዙ ሰው አላውቅም ነበርና ወደ L.A.ሄድኩኝ። እዚያ ትንሽ ስለቆየሁ ብዙ ሰው አውቃለሁ ብዬ። በሁለቱም ከተሞች በጣም ጥሩ ትብብር አገኘሁ።

ላንዳፍታ:-

ምን ያህል ጊዜ ፈጀብሽ የሚፈለገውን ገንዘብ ለማግኘት?

ኤልሣቤጥ:-

አንድ ወር

ላንዳፍታ:-

ይህን ሁሉ ጊዜ አስከሬኑን አቆዩልሽ?

ኤልሣቤጥ:-

የሚገርመኝ እሱ ነው። በጣም ነው የተባበሩኝ።

ላንዳፍታ:-

እስቲ የመስፍንን ታሪክና አሟሟት ንገሪን።

ኤልሣቤጥ:-

መስፍን መንገሻ ከእናቱ ከወ/ሮ አረጋሽ መኩሪያና ከአባቱ ከአቶ መንገሻ ዱብአለ ጥር 29 1957(እንደኛ አቆጣጠር) በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ። የ1ኛና የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን ያጠናቀቀው አዲስ አበባ ነው። ከዚያም ወደ ኬኒያ በስደት ሄዶ ሦስት አመት ከኖረ በኋላ እ.ኤ.አ. በ1989 ወደ አሜሪካን ሀገር መጥቶ በዋሺንግተን ዲሲና በአትላንታ ለአራት ዓመታት ከኖረ በኋላ ወደ ሲያትል መጣ። Nov.21, 1992 ምሽት ደረቱ ላይ በጩቤ ተወግቶ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። አስክሬኑም Dec. 19, 1992 ወደ ኢትዮዲያ ተልኮ በአዲስ አበባ ከተማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ዘመድ አዝማድ በተገኘበት ስርዓት ቀብሩ ተፈጽሟል። ስለአሟሟቱ ከፖሊሶች ባገኘሁት መረጃ መሠረት የተገደለው በጠብ ነው ብለውኛል። ገዳዩ ተይዞ በምርመራ ከቆየ በኋላ ገዳይነቱ ተረጋግጦ በሁለት ዓመት ተኩል እስራት ተፈርዶበታል።

ላንዳፍታ:-

ሁለት ዓመት ተኩል አልሺኝ?

ኤልሣቤጥ:-

የሲያትል ኪንግ ካውንቲ ፖሊስን ስንጠይቅ "አሟሟቱ በአጋጣሚ የተነሳ አለመግባባት እንጂ ገዳዩ ሁን ብሎ ተዘጋጅቶ ያደረገው ግድያ ስላልሆነ እንዲሁም ገዳዩ የአእምሮ ችግር ስላለበት ከዚህ በላይ ሊፈረድበት አይችልም" አሉን።

ላንዳፍታ:-

የዚህን ያህል ገንዘብ ለመሰብሰብ ካለሽበት ከተማ ወደሌላ ከተማ ሄደሽ ሙከራ ስታደርጊ በሰው ትብብር በኩል ያገጠሽን በመጠኑ ብትነግሪን።

ኤልሣቤጥ:-

የአገሬ ልጆች በጣም ተባባሪዎች በመሆናቸው በኢትዮጲያዊነቴ እንድኮራ አድርገውኛል። በሲያትልም፣ በL.A.ም ጥሩ ትብብር አግኝቻለሁ። ይህን ስል ችግር ገጠመኝ አልልም። በጣም ያልጠበቅሁዋቸው ነገሮች ሁሉ አጋጥመውኛል። ፈቃዳችሁ ከሆነ ስለዚህ ጉዳይ የፃፍኩት የምስጋናና የቅሬታ ጽሑፍ ስላለኝ ብታወጡልኝ ደስ ይለኛል። ስለጠቅላላው ሁኔታ እዚያ ላይ ገልጫለሁ።

ላንዳፍታ:-

ላኪልን። ኤልሣቤጥ ሌላ ተሳትፎ በሌላ መልኩ ደግሞ እንዳደረግሽ ሰምተናል። በቅርቡ L.A.የተካሄደው የኢትዮጲያኖች የቁንጅና ውድድር አዘጋጅ ነበርሽ። በመጀመሪያ ይህን የአገራችን ውበት የሚያንፀባርቅ፣ ሴቶቻችንን የሚያኮራ፣ ኢትዮጲያውያንን በአንድ አዝናኝ ሁኔታ የሚያሳስብ ዝግጅት በማድረግሽ የመጽሔታችን ዝግጅት ክፍል አድናቆቱን ይገልጽልሻል። እንዲያው ለመሆኑ ሃሣቡ እንዴት መጣልሽ? ዝግጅቱን ለማድረግ ችግር አልገጠመሽም? ያሰብሺው ውጤትስ ተሳካ ወይ?

ኤልሳቤጥ፤-

የቁንጅና ውድድሩን ለማዘጋጀት ያነሳሳኝን ነጥቦች በመጠኑ ገልጸሽዋል። እኛን ኢትዮጵያውያን ሴቶችን የሚያሰባስብ፣ የሚያቀራርብ ሁኔታም ለመፍጠር ነው። ውበታቸችን በጓዳ የሚቀር ብቻ ሳይሆን በአደባባይ የሚወጣም መሆን አለበት ብዬም ስለማምን ነው። ዝግጅቱን ለማካሄድ በመጠኑም ቢሆን ችግር ገጥሞኝ ነበር። ከተለያየ ቦታ ባገኘሁት ትብብር ልወጣው ችያለሁ። በመጀመሪያ ላይ ብዙ ኢትዮጲያዊያን ሴቶች ለውድድሩ አይቀርቡም የሚል ፍርሃት ነበረኝ። ሆኖም እንደፈራሁት ሳይሆን ቀርቶ ብዙ ተሳታፊ አገኘሁ።

ላንዳፍታ፤-

በቅርቡ አንድ መፅሔት ላይ ይህን ውድድር በመተቸት አንድ አስተያየት ተጽፏል። አስተያየቱ ዝግጅቱን የሚቃወም ይመስላል። ስለዚህ ምን አስተያየት አለሽ?

ኤልሣቤጥ፤-

ጽሑፉን አንብቤዋለሁ። በመጀመሪያ ነገር የዚህ ዓይነቱ መረን የለቀቀና ብልግና የበዛበት አጻጻፍ እንኳን እኔን አዘጋጅዋን ይቅርና ሌላውንም ቢሆን ቅር ማሰኘቱ አይቀርም። ከሁሉ በላይ የጽሑፉ መልዕክት ምን እንደሆነ አልገባኝም። ለቁንጅና የቀረቡትን ሴቶቻችንን "ቆንጆ አይደላችሁም" በሚል በብልግና አነጋገር የተንጸባረቀ ትምክህተኝነት የተሞላበት አባባል ነው። ጸሐፊውን በጣም ነው የታዘብኩት።

የዚህ ዓይነቱ አስተያየት ወደፊት ልትሠሪ ያቀድሻቸውን ነገሮች እንዳትፈጽሚ ስሜትሽን ይነካዋል ወይ?

ኤልሳቤጥ፤-

በፍጹም አይሰማኝም። በመጀመሪያ ነገር የዚህ ዓይነቱን ዝግጅት ለማድረግ ስዘጋጅና አደባባይ ለመውጣት ሳስብ የዚህ ዓይነቱ የትምክህተኞች አስተያየት ሊመጣ እንደሚችል በመገመት ስለሆነ አያስደነግጠኝም። እንዲያውም የዚህ ዓይነቱን የትምክህት አቀራረብ ለማሸነፍ ሞራሌ የበለጠ ከፍ ይላል እንጂ ተስፋ አልቆርጥም።

ላንዳፍታ፤-

እናመሰግናለን ኤልሳቤጥ። በርቺ።

■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■

## ለ አ ን ባ ብ ያ ን

ኤልሳቤጥ ገበየሁ ከላይ የገለጸችልንን በጐ ተግባር በምታከናውንበት ጊዜ የደረሰባትን፣ ያጋጠማትን ሁሉ በሰፊው የዘገበችበት ጽሑፍ ረዥም በመሆኑ በዚህኛው እትም ላይ ልናወጣው ባለመቻላችን እያዘንን በሚቀጥለው እትም እንዳለ እንወጣዋለን። ኤልሳቤጥንም በዚሁ ይቅርታ እንጠይቃታለን።

■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■

## ልብወለድ

# « እህያና ጠላ ቤት »

ከውሂብ ጥሩነህ (ዳላስ)

ጊዜው የገበያ ቀን ቅዳሜ፣ ሰው ሁሉ ወይ ለመሸመት ወይ ለመሸጥ ወደ ገበያ የሚራወጥበት ጊዜ ነበር። ፀሐይዋም ብርሃንዋን ከአድማስ እስከ አድማስ ዘርግታ ቀኑን አድምቃዋለች። የባህርዳር ከተማ ገበያም እህል ለመሸጥ ከባላገር ተጉዘው በመጡና እዛው ከተማ ውስጥ በሚኖሩ ነጋዴዎች እየተሞላ ነበር። ለወትሮው መርጊያ እህያውን ጭኖ መንገድ ሲጀምር በዚያች ትንንሾቹን መንደሮችና ገበያውን በምታገናኘው መንገድ ላይ እንደነሱ የላባቸውን ዋጋ ለመሸጥ እህያቸውን አስቀድመው የሚጓዙ ገበሬዎች አያጣም ነበር። ዛሬ ግን አንድ ነገር ስለሁኔታው አልዋጥለለት ብሎ ነበር።

"ሰላም ያሳደርሽኝ ኪዳነማርያም ቀኑን የሰላም አድርጊልኝ" አለ ብጣሽ ቂጣውን አፉ አድርጎ እህያውን እየነዳ። ትንሽ እንደተጓዘ ከአፍ እስከጥፍሯ በነጠላ የተሸፋፈነች ልጅ ሁለት ግልገል ፍየሎች እየነዳች በተፋጠነ ሁኔታ አለፈችው። እሱም እንደመገረም አለና ርምጃውን ፈጠን አደረገ። ከአንድ አስር እርምጃ በኋላ ደረሰባትና ጮክ ብሎ "ደህና አድረሻል ወይ?" አላት አሁንም ግራ በተጋባ አይን እየተመለከታት። "እንደምን አደሩ ጋሼ መርጊያ?" አለች አይኗን ከፍየሎቹ ላይ ሳታነሣ።

"ኸረ ለመሆኑ ሰዉ ምን ነክቶት ነው ዛሬ ጥዋት ያረፈደው?" አለ እርምጃውን ከሷ ፍጥነት ጋር ለማስተካከል እየሞከረ።

"እኔ ምን አውቃለው ጋሼ? ምናልባት በጥዋት ወጥተው ይሆናል..." አለችና ድንገት "እህያው!"ብላ ጮኸች። መርጊያ ለካስ ሲያወራ ስለራሱ እህያ እንደመዘንጋት ብሎ ኖሯል።

"ና አንት ወደል!" አለና በያዘው የባህር ዛፍ እንጨት እየደለቀ እህያውን መልሶ ከመንገድ አስገባው።

"ወዴት እየሄድሽ ነው የኔ ልጅ?" አለ መርጊያ ብቻዋን ወከብ፣ ወከብ እያለች የምትሄደውን ልጅ እያየ።

"አባቴ ዛሬ ምች ብጤ ስላመመው እኔና ወንድሞቼ ነን እህሉንና ከብቶቹን የምናደርስለት!" አለችና እርምጃዋን ፍጥነት ጨመረች። እንዲህ እንዲህ እያሉ ትንሽ እንደተጓዙ መርጊያ የፀሐዩ መክረር አይቶ፤

"የኔ ልጅ በይ መንገዱን ቀና ያድርግልሽ። እኔ ወደ መንደር ገባ ብዬ ማለሻለሻ ነገር ቀማምሼ ወደ በኋላ ብቅ እላለሁ።"

"ደህና ይዋሉ!" አለች ያደፈ ነጠላዋን እየተከናነበች። መርጊያ ጠላ ቤት ሲገባ ያለወትሮው ጠላ ቤቱ ጭር ብሎ ጠበቀው። የጠላ ቤቱ ባለቤት እማማ ደመቀች ከሚያሳድጉት የልጃቸው ልጅ ጋር ሆነው ጥጥ ይፈትሉ ነበር።

"እንዴት አደሩ እመይቴ?"

"ደህና አደርክ የኔ ልጅ ግባ" አሉ ፊታቸውን በፈገግታ አብርተው። እህያውን ደጅ ከተተከለው ስልክ እንጨት ጋር እንደ ነገሩ ወሸብ አድርጎ አስሮ ወደ እማማ ደመቀች ጠላ ቤት ዘው አለ።

"እረ ለመሆኑ እመይቴ ሰዉ ምን ነክቶት ነው ዛሬ?" አለ መርጊያ የቀረበለትን ጉሽ ጠላ ፉት እያለ።

"ምኑ የእኔ ልጅ?" አሉ አሮጊቷ ግራ ገብቷቸው።

"ምነዋ እናቴ ለወትሮው እኔ ስመጣ ቤትዎ ሰው አይጠፋም፤ እንዲያው ምን ተፈጥሮ ..." ብሎ ሳይጨርስ እማማ ደመቀች ቀበል አደረጉት።

"አይ የኔ ልጅ ሁሌ አይሞላ..." አሉና ያልተጠየቁትን መቀባጠር ጀመሩ። ልማድ ነውና መርጊያ ጠላውን እየተጋተ ማዳመጥ ጀመረ።

"ያ ከርፋፋው ...የጠጅቱ ባል እህቱን ለመጠየቅ አዲሳባ ወረደ ብላ ያቺ ለፍላፊ ጎረቤቴ ነገረችኝ። እሱ መቼ ለገበያ ቀን እኔ ቤት ሳይደርስ አልፎ አያውቅም ደግሞ እኛ አባ ተኮላ... አይ እሳቸው ብሎ ቄስ... በቀደም እኔ ቤት አምሽተው እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ጠላውን ሲጋቱ አምሽተው ከሞላ እርሻ ውስጥ አለት ላይ ወድቀው ተፈነከቱ አሉ። እኔን ቄስ ያድርገኝ አሁን በወላዲቷ ይሄ አመል ተገቢ ነው?... አይጠጡ አላልኩም ግን ምናለ ልካቸውን ቢያውቁ? ታዲያ ምን ሆኑ ተብለው ቢጠየቁ 'የደመቀች ጦር ወግቶ ጣለኝ' እያሉ ሲያሸሟጥጡኝ ሰምታ ይቺው ጎረቤቴ ነገረችኝ።"

‘ወሬኛ ጎረቤት!’ አለ መርጊያ በሆዱ።

"ነይ አንቺ ልጅ እስቲ ቀስ ብለሽ ከተሸፋፈነው ጠላ ጓዳ ግቢና ለመርጊያ ሙይለት!" አሉ ረጋ ባለ መልክ የሚያዳምጣቸውን መርጊያን እየተመለከቱ።

"ተገበያ በፊት አረፍ ማለቱ ጥሩ ነው? ለመሆኑ ምን ይዘሃል?" አሉት እጃቸውን ጉልበታቸው ላይ አረፍ አድርገው።

"ኸ...ኸ...ትንሽ አተርና ባቄላ ቢጤ አለኝ እመይቴ፤" አለ መርጊያ የለበሰውን ጋቢ አይሉት ቡልኮ ነገር እያጣፋ።

"ዋጋ በስፍር ሰማይ ደርሶአል" አሉ ወይዘሮ ደመቀች የቀረበውን ጣሳ እየሞሉለት።

"ይኸው ማሳችንን በወደላ በሬዎች ሳናቋርጥ እንለዋለን...ዛዲያ..."አለ መርጊያ የጠላውን ጉሽ በጣቱ እያዘዋወረ።

"ዛድያ ዝናቡም እንደወትሮው ጊዜውን ጠብቆ አይመጣ፣ የምናስገባውም ከእጅ ወደአፍ ሆኗል። እንኳን ለገበያ ተርፎ የሚሸጥ ለራስም አልበቃ እያለ ነው።"

"በለውስ እንዴት ነው?" አሉ ወ/ሮ ደመቀች የመርጊያን ታናሽ ወንድም በለውን በእዕምሮአቸው እያሰላሰሉ።

"ኤሄሄሄ...የሱን ነገር ባያነሱት" አለ መርጊያ እንደመሳቅም እንደመቆጣትም እየ ቃጣው። ሞቅታ እየመጣ ነበር።

"እንዴት?" ወ/ሮ ደመቀች ጥሩ ወሬ ለመስማት አሰፍስፈው።

"እንዲያው...እንዲያው ሞኝነት አይሉት ብልጠት ...ታዲሳባ ያለውን የባልንጀራውን ሱቅ አይቼ እመጣለሁ ብሎ ባለፈው ጊዜ ተዚያው ድረስ ሂዶ ነበር።"

"እሺ?" አሉ ወ/ሮ ደመቀች።

"ዛዲያ...መቼም ያለችውን ወደ ዘጠና አምስት ብር ይዞ ነበር የሄደው። ዛዲያ ባልንጀራው ዱቁን ለሰው ሸጦ ኖሮ የሚቀበለው ሰው አጥቶ ሁለት ቀን ከረማታ!" አለ ሣቅ ሣቅ እያለ።

"የት አያደረ ?" አሉት አሮጊቷ ፊታቸውን በሃዘኔታ ጭፍግግ አድርገው።

"አለ አሉ...ይሄ እየተከፈለበት የሚታደርበት ቦታ! ዛዲያ መሳፈሪያ አልበቃው ብሎ፣ ባልንጀራውንም የሚያውቅለት አጥቶ መከራውን ነው ያየው። ሁዋላ የቤቱ ባለቤቶች ገራገር ኖረው መሣፈሪያውን ችለውት ተመልሶ መጣ!" አለና በሣቅ ይንፈረፈር ገባ።

"እንደሚያዩት የማረሻውም ዋጋ ወደድ ይላል የሚያረገው ነገር ጠፍቶት ቁጭ ብሏል" አለና መርጊያ በረጅሙ ተነፈሰ።

"እይ ልጄ ጉድ ተሰራ!" አሉ አሮጊቷ በማስተዛዘን መልክ። ከጥቂት ሴኮንዶች ዝምታና ከንፈር መጠጣ በኋላ ነበር መርጊያ የተቀዳለትን ጠላ በሰፊው የተጎነጨው።

መርጊያ ለካስ ሳያውቀው ወደ ሶስት ጣሳ ጠላጨልጦ ኖሮአል። የጠጣው ያ የጉሽ ጠላ ራሱ ላይ እንደመውጣት ሲቃጣው ይሰማው ነበር።

"እስቲ የጫንከውን አተር ልዬው" ብለው ከሃሣቡ ያባነኑት ወይዘሮ ደመቀች ነበሩ።

"እ...እሺ...ይዩታ!" አለ መርጊያ የቀረችውን ጭላጭ ጠላ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እየተጎነጨ።

መርጊያ ምን እንደሆነ ሳያውቀው አንዳች ነገር በራስ ምታት ሲወጋው ይሰማው ነበር። ከመቀመጫው በግድ ብድግ አለና "በሉ እህያዬን ከደጆ ነው ያሠርሁት አተሩን ወደቤት ላምጣልዎ"

"መርጊያ ...?" አሉ ወ/ሮ ደመቀች በመስኮታቸው ተንጠራርተው ወደውጭ እየተመለከቱ።

"አቤት!" አላቸው አፉን በኩታው እየጠራረገ።

"እህያ የሚባል ነገር ተሂ ደጅ አይታዩኝም፣ ወዴት ነው ያሠርከው?" አሉት ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው።

መርጊያ ምንም መልስ ሳይሰጣቸው ኩታውን እያጣፋ ወደ ደጅ ሮጠ። የገዛ አይኑን ሊያምነው አልቻለም! እህያው ከነተጫነው እህል ጋር ከታሰረበት ቦታ አልነበረም።

በድንጋጤ ላብ ላብ እያለው አህያውን ፍለጋ ሩጫውን አስነካው። ወደገበያ የሚያመራው መንገድ እንደያዘ ብዙ ነጋዴዎችን ሸማቾች ሲቻኩሉ ተመለከተ። ወዴት እንደሚሄድ ግራ ገባው። "ጉድ ሆንኩኮ!"አለ በሆዱ ያን የብዙ ዘመን ጓደኛውን አህያ እያሰበ።

"አንተ ማነህ?..." እያለ አንዱን ዶሮ በቅርጫት ተሸክሞ የሚሄድ ነጋዴ ተጣራ!

ሰውዬው ምንም መልስ ሳይሰጠው ዘወር ብሎ ግራ በተጋባ አይን እየተመለከተው ቆመ።

"ጉድ እኮ ነው ጃል... እህያዬ የምሸጣትን ምናምን ይዞ ጠፋብኝኮ" አለው መርጊያ ቁና ቁና እየተነፈሰ።

"እህ...ዛዲያ እኔን ምን አድርግ ትለኛለህ? ፈልገዋ!" የሚል ድርቅ ምላሽ ሰጠው።

"ምን ያለሽው ነሃ? ኸረ በወላዲቷ...አይተህ እንደሆን ልጠይቅህ ብዬ ነበር...በል ተወው ወንድሜ" አለና የእርምጃውን ፍጥነት ጨመረ በገበያው መሃል መሹለክለክ ለመርጊያ ቀላል አልነበረም።

ገፍትሮዋቸው የሚያልፈው ወይዛዝርት በግልምጫ፣ አቧራ ቡን ያደረጋቸው አዛውንት በርግማን፣ ዶሮዎቻቸውን ያስደነበረባቸው ነጋዴዎች በስድብ መከራውን አሳዩት። "ምን ያለ ቀን ነው በወላዲቷ!"አለ በመገረምም፣ በቁጭትም። መርጊያ እህያውን ፍለጋ ያልገባበት ሥፍራ ያላንኳኳው በር አልነበረም። ከብዙ ሰዓት ውጤት አልባ የሆነ ፍለጋ በኋላ መርጊያ መድከሙን የገዛ ሰውነቱ ነገረው። የፀሐዩን ሙቀት መቋቋም ስላልቻለ ገበያ መሃል ወዳለው አዳራሽ ጥላ ፍለጋ አመራ።

አዳራሹ በረንዳ የተቀመጡት የልብስ ሰፊዎችና ገበያተኞች የመርጊያን የተደናገጠ መልክ ዞር ዞር እያሉ ማየታቸው አልቀረም። እሱም እንደዚያው! ከትንሽ ዕረፍት በኋላ ነበር መርጊያ ሊያምን ያልቻለው ነገር በዓይኑ የተመለከተው። ወንድሙ በለው የጠፋውን እህያ ከነዕቃው እየነዳ ሲያልፍ ነበር በሩቅ የተመለከተው።

"ተመስገን ... ተመስገን!" አለ ሣቅ ሣቅ እያለ። "ከእህያም አዋቂ እህያ የሰጠሽኝ አምላክ ተመስገን!" አለ ደጋግሞ። እህያው እንዴት አድርጎ ቤቱን አውቆ እንደተመለሰ ሊገባው አልቻለም ነበር፤ ለማወቅም አልፈለገም።

መርጊያ ወደጠላ ቤቱ ሲመለስ የገበያውን ነገር ለወንድሙና ለእህያው እርገፍ አድርጎ ትቶት ነበር...ለዛች ቀን!!!

■ ■ ■ ■ ■

# የ ወ ጣ ት ነ ት ጊ ዜ

### ከሽመልስ ሐብቴ አ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት የፈተና ምንባብ የተወሰደ

ዘውዲቱ ግርማ (ሰፈረ ቄራ አዲስ አበባ)

ወጣትነት ከሰው ልጅ ሕልውና ውስጥ ግሩም ድንቅ የሚያሰኝ የእድሜ ክልል ነው። የችግር፣ የብልፅግና፣ የስቃይ፣ የተድላ፣ የሐዘን፣ የደስታ የተስፋና የቀቢፀ-ተስፋ የትፍስህት የመደመምና የአዲስነት ስሜት ነው። እርግጥ የወጣትነት ወቅት ካለፈ በኋላ ትዝታው እያብሰለሰለ ከሚያብከነክን በስተቀር ምንነቱን በግልፅና በተሟላ ሁኔታ አንገነዘበውም። "ልጅነት ተመልሶ አይመጣም" የሚባለው አባባል ራሱ ወቅቱ አንድም ተወዳጅ በመሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ከቁጭት የተነሳ የምንሰነዝረዉ ነው። ወጣትነት የሚያልፍ ወቅት እንዲሆንልንም የምንመኝበት ነው። ማለፍንም በፀፀት በጥልቅ ሀዘን መመልከታችንን ይገልፃል። እንዲህ በቀረው ዘመናችን የሚያጥመነምነን የሚያሰላስለውም ትዝታችን መልካም ወይም መጥፎ ሆኖብን ይሆናል። ወጣትነታችን ትዝ ሲለን ባንድ በኩል ያሳዝነናል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድብቅ ልቦናዊ ትፍስህት ይሰማናል። ማለፉንም በእንባ እንሸጠዋለን። ፈቅደን አንገፍግፎን የምንገላገለው ሳይሆን ልቦናችን እየሳሳ እየጎመጀን ሳናስበው ከእጃችን የሚያመልጠን ጉዳይ ነው። እንዲያውም የሚያዘገየው የሚመልሰው ታምር ቢኖር የማንከፍለው መስዋዕት ባልኖረም ነበር።

ለምን ይህ ይሆናል? ለምንስ የእድሚያችንን ሁሉም ክፍል እንዳመጣጡ አናጣጥመውም? የሚሉ የጥያቄ ናዳዎች ናላችንን ሊበጠብጡት ይችላሉ። ነገር ግን ማንም እንደ ወጣትነት እድሜ የሚሆን ይገኛል የሚለው በቀላሉ ልንገፋው አንችልም፣ ምክንያቱም የሕይወት ማርና ሬት፣ አስገራሚና አስፀያፊ፣ ገጠመኞች ባንድነት ተጣምረው የሚገኙበትና ጎልተው ደምቀው የሚታዩበት የእድሜ ክልል ወጣትነት ነው። በሌላው የእድሜ ክልል ግን ደብዛዛ ነው። ለመሆኑ የሕይወት ምሬትና ጣሟ ውስጣዊና እውነተኛ ገፅታዋ ምንድነው? ጠልቆ እየተሰማን ዘልቀን እያወቅነው ደፍረን የማንገልፀውና ለግል ብቻ የሚቀር መራራነት ጎምዛዛነት አንግሸጋሽንት፣ ጣፋጭነት፣ እፍነክናኪነትስ አለ ወይ የሚሉ ጥያቄዎች የአዕምሮ ነውጥ ሊፈጥሩ ይችላሉ።

■ ■ ■ ■ ■

# « ጨ ብ ጨ ባ »

አጭር ልብ ወለድ
ከዘላለም መስፍን (መቂ)

... እሱ ...

... ያለ ጊዜ በመጣ ምጥ በችኮላ በመወለዱ ነገር ችኩል ባህርይ እንዲኖረው ምክንያት ሣይሆንበት አይቀርም። ገና ዓመት ሣይሞላው 'ዳዴውን' ሳይጨርስ ድክድክ ማለቱ፤ ቤተሰብ በቅርቡ ጥሩ እረኛ እንደሚያገኙ ተማምነዋል። ...

... አራት ዐመት ሆኖት በአሉት 'መአት' ኪሶች ጥራጥሬ ተሸክሞ ከብቶችን ማሰማራት የተለመደ ተግባሩ ሆኖዋል። ...

...ተፈጥሮ ዕድሜውን የምትቆርጥለት–እሱ ስምንት ሲሆነው በተፈጥሮ መመሰጥ ጀምሮአል። እጅግም ይመሰጣል። ጫካ ጫካውን፣ ሜዳ፣ ሜዳውን፣ ተራራውን...ያካልላል–ፋታ ሲያገኝ። መላ ቀልቡ ወደ ተፈጥሮ ወደ አካባቢው ወደ ራሱ ሊያደርግ ሣይሆን አይቀርም...ፍላጎቱ...

...አሥራ ሁለት ዓመቱ በመባቻ ላይ ርዝመትና ጥልቀት ያላቸውን ወንዞች...በዋና ማቋረጡ የሚደነቅ ነበር። እስከ ሁለት ደቂቃ ባላነሰ በውሃ ውስጥ መስመጥ መቻሉን በዚህ አለም የሚያውቅለት ማንም የለም – ከዚያ እግዜር በቀር። ቢኖር 'ሁለት ሣንባ አለህ?' ብለው ከመጠየቅ አይመለሱም – በመደነቅ!...

... 'ታላቅ' አዳኝ ሆኖአል – አሥራ ስምንት መባቻ ላይ። ጥንቸል፣ ጅግራ፣ ድኩላን...ሮጦ ለመያዝ ይመኛል። አሊያም ልቡና አይኑ አብሮት ይከንፋል ወይ ደግሞ...። ሐምሳ ኪሎሜትርና ከዚያም በላይ ለገበያ አሊያም 'ለሽርሽር' በየቀኑ መጓዙ የተለመደም ሆኖአል። ወላጆቹ 'ሮጦ አልጨረሰም' ብለው ሊድሩት አልፈለጉም። ጉሀ ሣይቀድ ወጥቶ በመሃል ይከተታል – የት አግኝተውት? አንድ ነገር አልተገነዘቡለትም – መሮጥ እንደማያቆም። ሮጦ ዓለምን ለራሱ ሊያደርግ ነው የሚፈልገው – እሱ። ደግሞ ዓለም መብዛቷዋ! ጣጣ ነው እቴ – ለእሱ። ቤት ውስጥ – ጠባብ ጎጆ ሆነችና መሮጥ አልተቻለም። ሲበላም፣ ሲተኛም...ችኮላው አይጣል ነው። ...

...ቂል ነው ደግሞ አሉት – አሥራ ስምንተኛው የልደት በዓሉ 'ታስቦ' ሲውል። ከፈረስ እኩል (ባይሆን ከኋላው ሳይርቀው) ሲሮጥ ያዩት። 'ለምን ተቀምጦ አይጋልብም? 'አሉት። እሱ – 'ለጉድ' የፈጠረው ግድ የለውም። ወላጆቹ የሰው ነገር መሮዋቸው"... 'ይህ ሩጫህ ይቅርብህ። ቤተሰብ መስርተህ የተከበርክ ሁን...' ብለውት ነበር። እሱ እንደሆነ ሳንባ እንጂ ልብ የት አለውና! በምን 'ልብ' ልብ ሊልላቸው ኖሮአል? መጨረሻም ላይም 'ሌላው' ባይሆን 'አርፎ ይቀመጥ' ሲባል ተመከረ። ያው ነው። ሳንባ ብሎ እግር ብቻ አይደል – ሁለቱም ለመሮጥ...ለማሰቢያም ለመቀመጫም አይሆንም!...

...ሃያዎቹ መጀመሪያ በኑሮው 'ብስጩ' ሆኖአል። በሌላው አእምሮ አንድ ነገር አሰበ። ወደ አዲስ አበባ ኮበለለ።...

"ይህንን ታዋቂ ውድድር በአስደናቂ ሁኔታ በማሸነፍህ ምን ይሰማሃል?" ሲል ጠየቀው – ታዋቂው የቢቢሲ የስፖርት ጋዜጠኛ።

"ጨብጨባ" ብቻ ነበር የመለሰው – አንድም የመድከም ምልክት የማይታይብት ኢትዮጵያዊው ማራቶኒስቱ – አትሌቱ – እሱ።

* * * * *

# የዴብራ ጦስ

(በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብ ወለድ)
ከገረሱ

"የዴብራ ጦስ" በተሰኘ ርዕስ የተጻፈው ልብወለድ ረዥም ስለሆነ በተለያዩ ክፍሎች በተከታታይ ይወጣል።

## ካለፈው የቀጠለ . . .

## ክፍል ሦስት

ካሣሁን ከዴብራ ጋር የፈጠረው ግኑኝነት በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ከተጠበቀው በላይ ሆነ። ካሳሁን ከአበሻ ጓደኞቹ ጋር የነበረው ግንኙነት እየቀነሰ ዴብራ በፈጠረችለት አለም ውስጥ ገባ። ከሥራ ሲወጣ ትጠብቀውና ተያይዘው እሷ በመረጠቻቸው ቦታዎች መዝናናት፤ እሷ አለችው ቦታ መሄድ ነበረበት። ጓደኞቹ መጥፋቱ ትንሽ ግር ቢላቸውም እሱ በሚሰጠው በሥራ መብዛት ምክንያት እየተረዱለት ብዙም አላስቸገሩትም።

ከሥራ ወጥቶ ዴብራን ይዞ አንድ ሁለት ክለብ ጨፍሮ እቤቱ መግባት፣ ያንን የአልጋ ላይ ጨዋታ መጫወት፣ በነጋታው ተነስቶ ሥራ መሄድ በቃ ይኸው ሆነ የዕለት ተዕለት ፕሮግራሙ።

በተገናኙ በአራተኛው ወር ገደማ ነው አንድ ቀን ሥራ ቦታ ትደውልለትና ዛሬ ማታ የሚነጋገሩት ጥብቅ የሆነ ጉዳይ እንዳለ ትነግረዋለች። እሱም የዛን ዕለት ቀደም ብሎ ከሥራ ይወጣል። ካለችበት ቦታ ሄዶ ወሰዳትና እቤት እንዲሄዱ ትጠይቀዋለች። ዴብራ ከካሳሁን የምትፈልገው ነገር ካለ ያንን ለመጠየቅ አመቺ ቦታዋ እሱ ቤት ነው፣ አልጋ ላይ፤ የሚፈልገውን ከማድረጉ በፊት የምትፈልገውን ትጠይቅና ቃል ታስገባዋለች ። ይሄ ብዙ ጊዜ ሰርቶላታል።

እቤት እንደደረሱ ያው ሁሌ እንደምታደርገው ሽንት ቤት ገብታ ለአንድ አስራ አምስት ደቂቃ ቆይታ አይኗ ፍም መስሎ ትመጣለች። ሳሎን ቁጭ ብሎ ነበር። ሄዳ እጁን ትይዝና ወደ መኝታ ክፍሉ ትመራዋለች።

"ዛሬ ትልቅ ነገር ነው የምነግርህ?"

"ምን ይሆን?" አልጋ ጫፍ ላይ ቁጭ ይላል።

"ኮትህን አውልቅ እንጂ?" ትለዋለች ከፊትለፊቱ ቆማ የሷንም እያወለቀች። ለሰውነቷ ተገዥ እንደሆነ ታውቀዋለች።

"እና ምን መሰለህ? ችግር ላይ ነኝ።"

"ምን አይነት ችግር?"

"አብሬአት ከምኖራት ጓደኛዬ ጋር ተጣላሁ፤"

"ምነው?" ከጓደኛዋ ጋር እንደምትኖር ነግራው አታውቅም። እሱም ስለአኗኗሯ ጠይቋት አያውቅም።

"ነገሩ ብዙ ነው? ብቻ ቤቱን እንድለቅ ዛሬ ነገረችኝ፤ ቅልስልስ ያለ ፈገግታ እያሳየችው።

"ታድያ ምን ተሻለሽ?" ካሳሁን በርግጥ አሳብ ገባው።

"እኔ እንጃልኝ? ቤቱ ደግሞ ክራዩ በሷ ስም ነው፤ እኔ ምንም መብት የለኝም።

"ሌላ ቤት መከራየት ነዋ? ምን ችግር አለበት?" ይላታል። ካሳሁን ለማፅናናት ያለው ነው።

"አንተ ደግሞ ትገርማለህ! ዝም ብሎ ቤት መከራየት የሚቻል መሰለህ?"

"ምንድነው ችግሩ?"

"አንተም ታውቀዋለህ፣ የዋስትና ተቀማጭ ገንዘብ (Security Deposit) ያስፈልጋል። እኔ ደግሞ አልተዘጋጀሁበትም። ምን እሱ ብቻ? ከአንድ ቤት አንድ ቤት ስትገባ ስንት ወጪ እንዳለ ታውቃለህ። ደግሞ ይህ ይመጣል ብዬ አላሰብኩም፣ ተቀማጭ ገንዘብ የለኝም።"

ካሳሁን በመጠኑም ቢሆን ጥያቄዋ ገባው። እሱም ቢሆን በዚህ ባለፉት አራት ወራት ከእሷ ጋር ዓለሙን ሲያይ ብዙ ገንዘብ አጥፍቶአል። "ገንዘብ አምጣ ልትለኝ ይሆን እንዴ?" አለ በሃሳቡ።

"ታድያ አንቺ ምን አሰብሽ?"

"እኔማ ምን አስባለሁ። መፍትሄ ባጣ አይደል ምክርህን የፈለግሁት።"

ካሳሁን አሳብ ይዞት ምንም መልስ ሳይሰጣት በመቆየቱ በሃሳቡ ዉስጥ ጣልቃ ትገባለች፤

"እንግዲህ ያለኝ ምርጫ እናቴ ያለችበት እስቴት move ማድረግ ነው።" አለች አይኗን አይኑ ላይ ትክል አድርጋ የሚለውን በጉጉት እየጠበቀች።"

"እሱ ምን ጥሩ መፍትሄ ነው?" አላት። ዴብራ ጥላው ልትሄድ፣ አይደረግም።

"በላ ሌላ ምን አማራጭ አለኝ፣ አትነግረኝም? "

"ሌላ እስቴት መሄድ እኮ ችግር አለበት። እዛ ሄደሽ ሥራ መፈለግ አለብሽ፤ የመጓጓዣ ወጪ አለበት።"

ካሳሁን ዴብራ ሥራዋ ምን እንደሆነ በእርግጥ አያውቅም። በአንድ ኩባንያ ውስጥ በጸሐፊነት ተቀጥራ የምትሰራም የሚመስለው ጊዜ አለ። አንዴ ጠይቋት ነገሩን ሽፋፍና አልፋበታለች። እሱ ምን ቸገረው?

"ታድያ ምን ላድርግ?" ወይ ደግሞ...አለ አይደል አንተ Security Deposit የምትሰጠኝ ከሆነ ይሆናል፤ . . .ሌላ ደግሞ እዚህ ከአንተ ጋር ብቆይ ሁኔታው እስኪመች፤..." የሚለውን ለመስማት ቸኮለች። ለካሳሁን ግን ሁለቱም ቢሆን ችግር መስሎ ታየው። ቁርጥ ያለ መልስ መስጠት ቸገረው።

ቤቱ ከገባች ሚስት ሆነች። ሌላ ቤት ተከራይታ ብትገባ የገንዘብ ወጪ ሊያመጣ ሆነ። አንድ ጊዜ ብቻ የሚከፍለው ቢሆን ጥሩ፤ ግን በየወሩ የቤት /ኪራይ ጎደለኝ ሙላልኝ፣ ወይም ክፈልልኝ እንደምትል ከወዲሁ ግምት ገባ። እቤቱ ብትኖር ችግሩ ምንድነው? እሱም ጥቁር፣እሷም ጥቁር፣ በዚህ ላይ ይወዳታል። ለእፍታ ጥቁር አሜሪካኖችን አግብተው በደስታ የሚኖሩ ኢትዮጲያውያኖችን አስታወሰ።

"ቤት ግቢ ካልኳት ጠቀለለችኝ ማለት ነው። ባገባትስ ምናለ? መቸም አበሻው አልተገኘ" አለ በሃሳቡ። "ወሳኙ ፍቅር ነው፣ መግባባት ነው።"

ዴብራ ዝምታው ትንሽ ቢያሳስባትም ልታቻኩለው አልፈለገችም። ያንን የሚደስትበትን ገላዋን የሸፈነውን ልብስ "ወበቀኝ"በሚል ምክንያት ማወላለቅ ጀመረች።

"ከአንተ ጋር ብቆይ ስትይ አልገባኝም?" አላት።

"ሴት ልጅ ከምትወደው ወንድ ጋር አብራ መኖር በእናንተ ባህል የለም እንዴ?" አለቺው ከንፈሯን ጣል አድርጋ።

"ተጋብተው ማለትሽ ነው?"

"ባይጋቡስ፤"

"አብሮ መኖር ከተጀመረ ከጋብቻ ምን ይለየዋል?"

"እግባኝ ብልህ አታገባኝም የኔ sweet" አለችውና አጠገቡ ጠጋ አለችና በከንፈሮቿ አፍንጫውን ነካችው።

"ጋብቻ እኮ ቀላል ነገር አይደለም"

"እኔም ቀላል ልጅ አይደለሁም። sweet አይደለሁም እንዴ?" አለችው።"

"sweetማ sweet ነሽ።"

"ስማ፤ አብሮ መኖር ማለት መጋባት ማለት አይደለም። መተዋወቅንና መግባባትን የሚያጠናክር ዘዴ ነው። እዚህ በሰለጠነው አገር እንደዚህ ነው ቢገባህ።"

"እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ?"

"ሁለትም ጠይቀኝ"

"ከእኔ ጋር አብሮ የመኖርን ሃሳብ ያቀረብሺው ጓደኞሽ ከቤቴ ውጪ ስላለችሽ እንጂ በእኔ ላይ ያለሽ ፍቅር ገፋፍቶሽ አይደለም፤ ልክ ነኝ ልክ አይደለሁም?"

ዴብራ ያላሰበችው ጥያቄ ነበር።

"ስማ ባልወድህ ኖሮ ይህን አማራጭ አልሰጥህም። ገባህ፤ ቀጥታ ለአንተም ሳልነግርህ እናቴ ጋ እሄድ ነበር።" ቆጣ እንደማለት አለች።

"አትወጂኝም አላልኩም እኮ፣ sorry! ተቀየምሽ እንዴ?"

"እንዴት አልቀየምም!"

"sorry በቃ ተይው፤"

"እሺ ምናልክ ታዲያ?"

"ትንሽ ጊዜ ስጪኝና ላስብበት አይሻልም?"

"አብረን መኖር የሚያስቸግር ከሆነ ፈልጌልሽ እዚሁ ቅርብ ትከራያለሽ፤ ለማንኛውም ጥቂት ቀናት ስጪኝና ላስብበት ok?"

"ምንድነው ችግሩ አብሮ መኖር?... ሌላ ኢትዮጵያዊት ሴት ስትመጣ እንዳላይብህ ነው፤ አይደል?" አለችውና ኩርፍ አለች። ኩርፍ ስትል አይኗ እንደሚያባብል ታውቃለች። መሣሪያዋ ነው።

"Come on Debra ነግሬሽ፣ በፍቅር እንጂ በዜግነት ልዩነት እንደማላምን። ምን መሰለሽ? በቅርቡ እናቴን ከአገር ቤት አስመጣለሁ። ከእኔ ጋር አንድ ስድስት ወር ትቆያለች። እንደምታውቂው ቤቱ አንድ መኝታ ቤት ብቻ ነው፤ ይህ ነው ያሳሰበኝ።"

"በል እሺ ለማንኛውም አስብበትና ቶሎ ንገረኝ። በሳምንት ጊዜ ውስጥ ቤቱን መልቀቅ አለብኝ።"

ዴብራ ትንሽ አምሽታ ካሳሁንን አስደስታ ከሸኘች በኋላ ትልቅ ሃሳብ ውስጥ ገባ። ለአፍታ ከአገር ቤት ከመጣ ያሳለፋቸውን የአምስት ዓመት ጊዜያት አስታወሰ። በዚህ ጊዜያት ውስጥ ሥራውንም እየሠራ ትምህርቱን በትርፍ ጊዜው እየቀጠለ፤ አገር ቤትም ዘመዶቹን እየረዳ ሲኖር በዚህ በኩል ያለው ኑሮ ተሳክቶለት የሴት ጓደኛ የማግኘቱ ጉዳይ ግን ዴብራን እስካገኛት ጊዜ ድረስ ሕልም ሆኖበት ነበር። የአበሻ ጓደኛ ለማግኘት ያልሄደበት ቦታ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም። በተፈጥሮ ያለበት ዓይንአፋርነት እንቅፋት ሆኖበት ትንሽ መንገድ አግኝቶ ሲጓዝ ሴቶች ለመግደርደርም ብለው ፊት ሲነሱት፣ ሲሽኮረምሙ "እይ ባትፈልገኝ ነው" ብሎ ይሸሻል። አይገፉበትም። በተለይ አንጀቱ ብጥስ ያለው አንዴ አንዷን አበሻ ፓርቲ ላይ ያገኛትና በጠጣው ቢራ ኃይል ተገፋፍቶ ይተዋወቃታል። ትንሽ እንዳወሩ "የመጣሽው ከየት ነው?" ትለዋለች። "ከኢትዮጲያ ነዋ" ይላታል። "ማለቴ ከአዲስ አበባ ወይስ ከክፍለ ሀገር" ትለዋለች። "የመጣሁት ከደብረማርቆስ ነው "ይላታል። "ነው እንዴ?" ትለዋለች። "ምነው?" ሲላት "አዲስ አበባን አታውቀውማ" ትለዋለች። "አላውቀውም፤ የመጣሁት በሱዳን በኩል ጠፍቼ ነው" "እኔ የመጣሁት ከአዲስ አበባ ነው፣" ትለዋለች። ካሣሁን መጀመሪያ ነገሩ አልገባውም ነበር። ፊት የነሳችው ቆይታ "ይቅርታ ጓደኛዬን ላናግራት" ብላ ጥላው ስትሄድና በዚያው ስትቀር ነው ነገሩ የገባው። ታዲያ ሌላ ጊዜ እንዲሁ እንዳጋጣሚ ካንዷ ጋር ይተዋወቅና እጅሬ ካለፈው ተምሮ የለም "ከየት ነው የመጣሽው?" ስትለወው "ከአዲስ አበባ" አላት ውሸቱን። "አዲስ አበባ ከየት ሰፈር?" አለችው። "ፒያሳ" አላት። "ፒያሳ ምኑ ጋ?" ስትለው ከየት ያምጣ። እሱ አንድ ሁለቴ ለዕረፍት ነው ለአጭር ጊዜ የሄደው። የሚለው ጠፍቶት አርዕስት ለመቀየር ቢሞክርም ሁኔታው አልጥም ያላት ልጅ ብዙም አብራው መቆየት አልፈለገችም። ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነው የአበሻ ሴቶች በጣም ውድ ስለሆኑ ሽሚያውንና ውድድሩን ለማለፍና አንዷን ለማግኘት ሕልም ከሆኖበት ከራርሟል። አንድ ሰሞን ደግሞ ከአገር ቤት ማስመጣት የሚል ዓላማ ሲያቅድ ሰንብቶ የጓደኛው ወንድም ስንት ገንዘብ አፍስሶ ያስመጣት ልጅ ሁለት ወር ሳትቆይ እነደጠፋች ሲሰማ ተወው።

ካሣሁን የአበሻ ሴት ለማግኘት የነበረው ተስፋ እየደበዘዘ ሲሄድ ነው ዴብራን ያገኛት። "ታዲያ ዴብራ ምን ወጣት?" አለ በሃሳብ ባህር ውስጥ እንዳለ። በቅርብ ባያውቃቸው እንኳ እሱ የሚኖርበት ከተማ የሚኖሩ ሁለት አበሾች አሜሪካን አግብተው፤ ቤት ገዝተው ልጅ ወልደው ተከብረው ይኖራሉ።

"ዴብራን እቤቱ ካገባሁ ሚስት ሆነች ማለት ነው፤" አለ ባሳቡ። እንግዲህ እናቱ በቅርቡ ሲመጡ በአፍ የማይግባቡ፣ በባህል የማይገናኙ የልጃቸውን ሚስት ሊያገኙ ነው። እማማ ታዲያ እንደ ባህላችን ዴብራን የልጃቸውን ሚስት "እስቲ ይህን አምጪ፣ ይህን አድርጊ" ሊሉ ነው። ዴብራ ስትታዘዝ ታየው። ሳቁ መጣ የሚፈጠረው ሁኔታ ለአፍታ በሃሳቡ መጥቶበት። ቢሆንም እሱ ካስረዳት ዴብራ ሊገባት እንደሚችል አስቦ ተጽናና።

ጭልጥ ባለ ሀሳብ ውስጥ ገብቶ ሳለ ስልክ ተደውሎ አባነነው። ስልኩን አነሳ። እሷው ነበረች።

"በአስቸኳይ እንድትመጣ፤" ትለዋለች ዴብራ።

"ምነው፣ ምን ተፈጠረ?" ይላታል።

"ቶሎ ና፣ እሱን የማስረዳበት ጊዜ የለኝም፤ ኋላ እነግርሃለሁ፤" ትለዋለች።

ስልኩን ይዘጋና ጃኬቱን ደርቦ ሊያመጣት ወጣ።

. . . በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል።

■ ■ ■ ■ ■ ■

# ኑሮ  በአሜሪካ



## ሥራ ማግኘት. . . እንዴት?

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል

ዛሬ በአሜሪካን አገር እንኳን ከተለየ አገር ለመጣ ይቅርና ለአገሬው ሰው ለራሱ ሥራ ለማግኘት ችግር አለ። ሥራ ያለመኖሩን ጉዳይ ለጊዜው በጥያቄ መልክ እናስቀምጥና ያለውን ሥራ ራሱ ማግኘት ስለሚቻልበት ሁኔታ ብንወያይ መልካም ይመስለናል። ብዙ ኢትዮጺያውያን በሙያቸው ሥራ አያገኙም። በከፍተኛ ደረጃ በአዕምሮ ሥራ የሠለጠኑ ወገኖቻችን በቀን የጉልበት ሥራ ተሠማርተው የተማሩትን ትምህርት፣ የገበዩትን ዕውቀት እስከመርሳት እንደደረሱ እናያለን። ለዚህ ችግር ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

1ኛ የአገሬው ሰው አለመሆን ራሱ አንድ ችግር ነው። ቅድሚያ ለአገሬው ሰው አለ። ይህ ደግሞ የትም ያለ ስለሆነ ልንገረምበት አይገባም።

2ኛ የቀለምም ጉዳይ አለ። አንዳንዱ ቀጣሪ ድርጅቶች ለይስሙላ "ድርጅታችን በአቀጣጠር በኩል ጾታ፣ ቀለም፣ ኀማና ዘር አይመለከትም" የሚል መመሪያ ይኖራቸዋል እንጂ በተግባር አያውሉትም። "Affirmative Action" የሚለውን መመሪያ ተከታይ ለመምሰል በወረቀት ላይ በቲዎሪ ደረጃ ብቻ የሚያስፍሩት ነው። ይህም ሌላው ችግር ነው።

3ኛ በተቀጣሪው በኩል ያለ ችግር ደግሞ አለ። ሥራ የሚገኝበትን ቦታ ያለማወቅ፤ ሥራውን ለማግኘት ያቀራረብ ችግር፤ ኢንተርቪውን ሆነ ፈተናውን የማለፍ ችግር በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በ1ኛና በ2ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያስፈርነውን ችግሮች ለመፍታት መቼም እንደማንሞክረው ይታወቃል። እነኚህ ችግሮች እንዳሉ ሆነው በ3ኛ ተራ ቁጥር ያስፈርነውን እንመልከት። መሥራት የምንችለውን ሥራ እንዴት ማግኘት እንችላለን? መሥራት የምንችለውን ሥራ እንዴት እንመረምራለን? ቀጣሪዎች ከሙያችን ሌላ ምንድንነው የሚፈልጉት? ይህንና ይህን በመሳሰሉት ጥያቄዎች ላይ እናተኩራለን። መቼም መቶ በመቶ የሚሠራ ዘዴ ነው ብለን ባንኩራራም ከአንዳንድ አሠሪዎች፣ ከመጽሐፍት፣ ልምዱን ካላቸው ሰዎች ያገኘናቸውን ሃሣቦች ከኛ ባህላዊና ግለሰባዊ አቀራረፅ ጋር በማስተዋደድ አንዳንድ ምክሮችን ልንለግስ እንሞክራን።

1ኛ. ለኛ የሚሆን ሥራ የሚገኝባቸው ቦታዎች እንዴት ማወቅ እንችላለን?

2ኛ. ራስ ማዘጋጀት ማለት ምን ማለት ነው?

3ኛ. በእኚህ ቦታዎች ግላዊ ጉብኝት ስለማድረግ

4ኛ. የሥራ ማመልከቻ ቅጽ አሞላል፣ ማመልከቻ አጻጻፍ፣ ሬዙሜ አዘገጃጀት፣ አቀራረብ

5ኛ.የቀድሞ ሥራ ልምድ ምስክርነት አስፈላጊነትና ዝግጅት (Reference persons)

6ኛ ኢንተርቪው አወሳሰድ

እስቲ እነኚህን ርዕሶች በየተራ ጠለቅ ብለን እንመልከት።

### 1. ሥራ የት ይገኛል?

ሥራ ማግኘት የሚቻለው ሰው በማወቅ ብቻ ነው ብለው የሚያምኑ አሉ። ምንም ያህል ዕውቀት ይኑር፣ ምንም ያህል ችሎታ ይኑር፤ ሁነኛ ሰው ካልታወቀ ዋጋ የለውም ብለው ይናገራሉ። አንዳንዶች ደግሞ የዕድል ጉዳይ አድርገው ይቀበላሉ። ይህ ማለትም ሥራ ፈላጊው አንድ ቀን ጠዋት ተነስቶ ሥራ ሲፈልግ እንዲጋጣሚ ሠራተኛ በአስቸኳይ የሚፈልግ ያጋጥመውና ወዲያው ይቀጠራል። በትምህርት ቤት በኩል፣ በቀጣሪ አስቀጣሪ ድርጅቶች፣ በመሳሰሉትም በኩል ሥራዎች የሚገኙ መሆናቸው ይታወቃል። ኮሌጆች፣ ዩኒቨርሲቲዎች Career Placement (የሥራ ምደባ) አገልግሎት ክፍሎች አሏቸው። በመመረቅያ ዓመት ላሉ ተማሪዎች የበለጠ አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል ነው። እነኚህ ሁሉ መንገዶች በተለያየ ጊዜ ሠርተዋል፣ ይሠራሉም። ሌሎችም ብዙ ዘዴዎች አሉ።

ብዙ ሰዎችና ጥናቶች፣ ሥራ ፈላጊዎች ሥራ ይገኛሉ በሚባሉ ቦታዎች ሁሉ የሚያደርጓቸውን ጉብኝቶች የበለጠ ውጤት አሏቸው ብለው ይጠቁማሉ። ሥራ ፈላጊዎች ከሙያቸውና ከችሎታቸው ጋር ተመጣጣኝነት አለው ብለው የሚያምኗቸውን ድርጅቶች በር ማንኳኳት ይኖርባቸዋል የሚል ምክር ይለግሳሉ።

## 2. በግል ጉብኝት ለማድረግ ቅድሚያ ዝግጅት - ራስን መመርመር፤

በግል ጉብኝት ከማድረግ በፊት ሥራ ፈላጊው ራሱን መመርመር አለበት። በትምህርት የተገኘ ዕውቀት ብቻ ወሳኝ መሆን እንደማይችል ማወቁ ብልህነት ነው። ራስን መመርመር ስንል ምን ማለታችን ነው? ችሎታዬ ምንድነው? ጠንካራ ጎኔስ ምንድነው? ደካማውስ? ራስን ማታለል ሞኝነት ነው።

ሰው በተፈጥሮው ፍፁም አይደለም። ደካማ ጎኖች አሉት። ይህን ማወቅ ብልህነት ነው። ይህ ማለትም ደግሞ "ደካማ ጎኔ ይህ ነው" ብሎ ለማወጅ አይደለም። ከቀጣሪዎች ጋር በሚደረግ ውይይት ወቅት ለመጠንቀቅ ይረዳል። አንዳንዱ ሲሠራም ሆነ ሲናገር በተፈጥሮ ዝግተኛ (slow) ነው። አንዳንዱ ችኩል ነው፤ አንዳንዱ ቶሎ ሆድ ይብሰዋል፣ ወዘተ... ስለራስ አጢኖ ማወቅ ያስፈልጋል። ያልሆኑትን መስሎ መታየት መሞከር ከትዝብት ላይ ይጥላል። ያውም ሥራው ቢገኝ። ራስን ሆኖ መቅረብን የሚያህል ነገር የለም። ያልሆነውን መስለን እንቀርብና ሥራው ተገኝቶ ሲጀመር ጉድ ሲወጣ መባረር አለ። ከአንድ የሥራ ቦታ የተባረረ ደግሞ በሌላው ቦታ ሥራ ለማግኘት በጣም ችግር ይኖርበታል።

ድክመታችንን፣ ጠንካራ ጎናችንን፣ ስሜታችንን እንዴት እንደምንቆጣጠር፣ ማጤን አለብን። ከሥራ ውጭ ደስ የሚለን ነገር (Hobby ወይም Interest) አችንን አጢነን ማወቅ አለብን። ቀጣሪያችን አደን ይወዳልና እኛም አደን እንወዳለን ማለት አይኖርብንም። መዋሸት ደግ አይደለም። ቀደም ብሎ የራስን ድክመት ማወቅ ምናልባት በኢንተርቪው ሆነ በውይይት ወቅት ይህን ድክመት የሚያስስ ጥያቄ ቢነሳ ጥሩ መልስ ለመስጠትም ያዘጋጀናል። ችሎታችንን በርግጥ እንገምግም። የማንችለውን እንችላለን ብለን ቀባጥረን ኋላ ውሉን መፍቻ ይጠፋል። "ይህን እችላለሁ፣ ይህን በአጭር ጊዜ መማር እችላለሁ፣ ይህን ፍፁም አልችልም፣ ይህን መሥራት ደግሞ አልወድም፣" ብለን መገምገም ያስፈልገናል።

## 3. የግል ጉብኝት ከማድረግ በፊት የቀጣሪዎችን ሁኔታ ማጥናት

የራስ ችሎታና ሁኔታ ተመርምሮ በዚህ ድርጅት ውስጥ ብሠራ ያዋጣኛል ተብሎ ግምት ከተወሰደ በኋላ ያንን ድርጅት ደግሞ ማጥናት ያስፈልጋል።

ሥራ ለመፈለግ እንደተኬደ ሣይሆን እንዲያው ስለድርጅቱ ለማወቅ እፈልጋለሁ በሚል ሰበብ ወደ ድርጅቱ ሕዝብ ግንኙነት ክፍል ብቅ ብሎ አንዳንድ የተፃፉ ነገሮች ወስዶ ማንበብ፤ የድርጅቱን ዓላማና ተግባር፣ እስካሁን ያደረጋቸውን ድርጊቶች፣ ስንት ሠራተኞች እንዳሉት፣ የሠራተኞች ሁኔታ ወዘተ... ማጥናት በጣም ይረዳል። በጽሑፍ ካለ ጥሩ፤ ከሌለም ከዚያው የሚሠሩ ሠራተኞች ከአንዱ ጋር መተዋወቅና አንዳንድ አሳቦችን ማግኘት። አለቆች ምን እንደሚያስደስታቸው ፣ ምን እንደሚያስከፋቸው? ሠራተኞችን እንዴት እንደሚይዙ? በመጠየቅ መረዳት ትልቅ አስተዋጽዖ አለው። ጉብኝቱን የበለጠ ፍሬያማ የሚያደርገው በሚጎበኘው ድርጅት የሥራ መብዛትና የሠራተኞች እጥረት መኖሩ ሲታወቅ ነው። አንዳንድ ጊዜ የቢሮክራሲው ሰንሰለት ያራዝመውና ሥራው እያለ ማስታወቂያው ቶሎ ላይወጣ ይችላል። በቅድሚያ የግል ጉብኝት ማድረጉና ከቀጣሪዎች ጋር ውይይት ማካሄዱ ጠቃሚ የሚሆነው ማስታወቂያ ከወጣ በኋላ ብዙ ተወዳዳሪዎች ቀርበው የሥራውን ማግኘት ዕድል ከማሳነስ ስለሚያድነው ነው። በጉብኝቱ ወቅት እንዲረዳ ቁልፍ ቁልፍ የሆኑትን ሰዎች ማወቅ፣ ስነልቦናዊ አመለካከታቸውን ጠይቆ መረዳት ብልህነት ነው።

## 4.ጉብኝት ማድረግና ቀጣሪዎችን መገናኘት

ከላይ እንደተገለፀው ሥራ ፈላጊው ራሱን ከገመገመና የድርጅቱን ሁኔታ ካጠና በኋላ ቀጣሪዎችን ለመገናኘት ዘዴ መፈለግ አለበት። አንዳንዴ ደውሎ ቀጠሮ መውሰድ ብቻ በቂ ሊሆን ይችላል። በማስታወቂያ መልክ የወጣ ሥራ ከሆነ የሥራ ማመልከቻና ሬዜሜ መላክ ሊበቃ ይችላል። ማስታወቂያ ባይወጣም አንዳንድ ድርጅቶች በተለይ አነስተኛ ድርጅቶች የፔርሶኔል ክፍላቸው ለማስረዳት ዝግጁ ነው።

ቀጣሪዎችን በማነጋገርያ ወቅት የሚከተሉትን መጠንቀቅ ያስፈልጋል፤

1. ንጽሕና ጠብቆ መሄድ

2. በድርጅቱ ውስጥ ከማንኛውም ሰው ማለትም ከሪሴፕሽኒስቷ ጀምሮ የሚደረገው ንግግርና የሚቀርበው ጥያቄ ትህትና የተሞላበት፣ ፈገግታን ያስከተለ መሆኑ ጠቃሚነት አለው። "ቁጭ በልና ጠብቅ፤ ዛሬ ሰው ልናነጋግር አንችልም፤ "ወዘተ... የመሳሰሉ መልሶች ሲሰጡ በጸጋና በትህትና መቀበል ይረዳል። ምንችክ ያለ አነጋገርን ማስወገድ፤ ዓይን አለማፍጠጥ፤ ድርቅ ድርቅ አለማለት፤ ያልገባን ነገር በጽሞና መጠየቅ፤ የመሳሰሉትን መዘንጋት አያስፈልግም።

3. ቁጭ ብሎ መጠበቅ ቢያስፈልግ ቁጭ አሉበት ቦታ ሲጋራ አለማጨስ፤ አለመቁነጥነጥ፤ ሠላሜ ጊዜ እየተነሱ "ጊዜው ገና ነው?" እያሉ አለመጠየቅ፤ በትዕግስት፣ መጠበቅ፣

ፈተናው ከዚሁ ነው የሚጀምረው።

## 5. የሥራ ማመልከቻ አሞላል

የሥራ ማመልከቻ ቅፅ በሚሞላበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

1ኛ. መሞላት ያለበትን ነገር ጉልህ በሆነ ጽሑፍ እውነት በተሞላበት መንገድ መሙላት። የልደት ቀን፣ ዕድሜ፣ ስም፤ ልክ ፓስፖርት፣ ግሪንካርድ ወይም መንጃፈቃድ ላይ በተሞላው ዓይነት መሙላት።

2ኛ. አድራሻን በትክክል መሙላት፤ ማመልከቻ ላይ የሚፃፈውን ማንኛውንም ነገር ግልፅ በሆነ በሚነበብ መልክ ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይ ስማችን ከነሱ ለየት ስለሚል ለማንበብ እንዳይቸግራቸው አለመቀጣጠል። በማመልከቻው ላይ የሚሞላው የስልክ ቁጥር በአቅራቢያችን ያለውን መሆን አለበት። አንዳንድ አሰሪዎች ደውለው መልዕክት መተው አይፈልጉም።

## 6.የሥራ ኢንተርቪው

አንድ ተቀጣሪ ማመልከቻውን ሞልቶ፣ ሬዜሜውንም ልኮ ቀጣሪው ድርጅት ያንን መርምሮ ለኢንትርቪው ከጠራው ሥራውን ለመሥራት ዕምነት ጥለውበታል ማለት ነው። አመልካቹ በወረቀቱ ላይ ያሰፈረው እውነተኛ ለመሆኑ፤ አቀራረቡ፤ አነጋገሩ፤ ዕምነቱ ከድርጅቱ አላማ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን የሚያጣሩበት ዘዴ ኢንተርቪው ነው። ስለዚህም በሥራ ማግኘት በኩል ኢንተርቪውን ማለፍ ትልቅ ሚና ይጫወታል። እንግዲህ ኢንተርቪው ተደራጊው አመልካች በደንብ መዘጋጀት አለበት። ከኢንተርቪው ፊት አመልካቹየሚከተሉትን መረጃዎች በደንብ አጠናቅሮ መያዝ አለበት።

1. ስለድርጅቱ ዓላማና ተግባር

2. የድርጅቱን አወቃቀርና የአሠራር ዘዴ

3. የድርጅቱን ስፋት

4. በድርጅቱ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ክፍሎች

5. ድርጅቱ ካከናወናቸው ተግባራት በኅብረተሰቡ ውስጥ ጐልተው የሚታዩትን

6. የድርጅቱን ጠንካራና ደካማ ጐኖች

እነኚህን መረጃዎች ቀደም ብሎ ከድርጅቱ የሕዝብ ግኑኝነት ክፍል ማግኘት፤ የድርጅቱን ዓመታዊ ሪፖርቶች፣ በድርጅቱ የሚወጡ መፅሔቶች፣ ጽሑፎች፣ ጋዜጣዎች ማንበብ፤ ወይም ደግሞ ድርጅቱ ውስጥ ከሚሰሩ ጓደኞች መጠየቅም ይቻላል።

በድርጅቱ ተጠቃሚ የሆኑ የውጭ ሰዎችም (Clients) ሌሎች ምንጮች ናቸው። ከብዙ ጥናቶች በተገኙ መረጃዎች በደንብ በመረጃ ተጠናክረው ኢንተርቪው የገቡ ሰዎች ኢንተርቪው አድራጊውን በመማረክ አብዛኞቹ ያመለከቱበትን ሥራ ለማግኘት ችለዋል። አመልካቹ በቅድሚያ አውቆ ሊዘጋጅባቸው የሚገባ በኢንተርቪው ላይ የሚነሱ መሠረታዊ ጥያቄዎች አሉ። እነኚህ ጥያቄዎች በሁሉም ባንል በአብዛኛው የሚነሱ ስለሆኑ ቀጥለን እናቀርባቸዋለን። ትርጉሙ ምናልባት ለዛውን ይቀንስ ይሆናል በማለት የእንግሊዘኛውንም አብረን አቅርበናል።

1. እዚህ ድርጅት ለመቀጠር ምን አነሳሳህ?

Why did you apply for a position in this organization?

2. ስለድርጅታችን ምን ታውቃለህ?

What do you know about our organiztion?

3. ለምን ዓይነት ሥራ ነው ያመለከትከው?

For what specific position are you applying?

4. ይህን ሥራ መሥራት እችላለሁ ለማለት ያነሳሳህ ምንድነው?

What makes you think you can do this job?

5. ምን ዓይነት ሥራ ነው መሥራት የምትወደው?

What type of work do you like best?

6. የተማርከውን ትምህርት በጣም ወደኸዋል ወይ? ከወሰድካቸው ኮርሶች የትኞቹን ወደድክ?የትኞቹን ጠላህ? የትምህርት ውጤቶችህ እንዴት ነበሩ?

Do you enjoy your education? What are the courses you liked least and best? What kinds of grades did you get?

7. እንዴት ነው ትምህርትን መቀጠል ትፈልጋለህ? ካልፈለግህ ለምን?

Do you plan to continue your education? If not, why not?

8. ከአንድ አምስት ዓመት በኋላ ምን አደርጋለሁ ብለህ አቅደሃል? ከአስር ዓመት በኋላስ?

What do you hope to be doing five years from now? ten years from now?

9. እስቲ ስለሕይወት ታሪክህ ትንሽ አጫውተን

Please, tell us about your self?

10. ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታህ እንዴት ነው? ከምን ዓይነት ሰዎች ጋር መሥራት የሚያስቸግር ይመስልሃል?

Do you get along well with people? What kinds of people do you find it difficult to work with?

11. ከዚህ በፊት ስለነበረህ የትርፍም ይሁን የሙሉ ሥራ አጫውተን። ከነዚህ ሥራዎች የተማርከውን ንገረን።

What full oor part-time jobs have you held? What did you learn from them?

12. ከሥራና ከትምህርት ውጪ ምን ማድረግ ደስ ይልሃል? (Hobby)

What are your hobbies?

13. ስንት ብር ደመወዝ ብንከፍልህ ፈቃደኛ ነህ?

What salary do you expect?

14. እኛን የምትጠይቀን ነገር ካለ?

Is there any thing you want to ask us?

አመልካቹ የሚጠይቃቸውን አንድ ሦስት አራት ጥያቄዎች በቅድሚያ ተዘጋጅቶበት መያዝ አለበት። ጥያቄዎቹ በሳልና እራስን የማያስገምቱ ከደመወዝና ከጥቅም ውጪ የድርጅቱን ዓላማና ተግባር የተመለከተ መሆኑ ጥሩ ነው። ለዚህም በቅድሚያ መዘጋጀቱ ብልህነት ነው።

በኢንተርቪው የሚነሱ ጥያቄዎች እነኚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም። በአብዛኛው ከሚነሱት ለአብነት ያህል ነው ያቀረብነው። አንባቢያን የምትጠቁሟቸው ጥያቄዎች ካሉ ላኩልን።

በሚቀጥለው እትም እነኚህ ጥያቄዎች ስለሚኖራቸው መልሶች እንመረምራለን። በተጨማሪ የኢንተርቪው አድራጊዎችን አቀራረብ፣ ባህሪ፣ ስነልቦናዊ ገፅታቸው በተለያየ መልኩ እናያለን።
ኢንተርቪው ሊወሰድም ሆነ ከተወሰደ በኋላ መደረግ ስለሚገባቸው ጉዳዮች እንወያያለን።

እንባቢያን በተለይም በዚህ ሙያ ልምዱን ያላችሁ አስተዋፅዖ እንደምታደርጉ ተስፋ እናደርጋለን።

## ውድ አንባብያን፤

በዚህ በቀረበውና በተከታታይ በሚወጣውም አስተያየት፤ ማሻሻያ ወይም ተጨማሪ ሃሳቦች፤ በተለይም ከደረሰባችሁ ልምድ አኳያ ገጠመኞቻችሁን ዘግባችሁ ብትልኩልን በሥራ እጦት ምክንያት ችግር ላለባቸው ወገኖቻችን ረዳት ይሆናል።

ከዚህ በተረፈ በጤና አጠባበቅ በኩል ከጤና ባለሙያዎች ምክር እንሻለን። እስቲ ይህችን ጥያቄ የጤና ባለሙያዎ፡ ች ተመልከቷት።

"አሜሪካን አገር እንደመጣሁ ትምህርት ቤት ስገባና የጤና ምርመራ ሳደርግ ለሳምባ ነቀርሳ የተደረገልኝ ምርመራ POSITIVE ነው ተባለ። ደነገጥኩ። ሁለት ጊዜ ራጅ ተነሳሁና ጤነኛ መሆኔ ተረጋገጠ። ተመሳሳይ ሁኔታ ብዙ ኢትዮጵያውያኖች እንዳጋጠማቸው በኋላ ልረዳ ችያለሁ። ይህ ለምን እንደሆነ ዘርዘር አድርጉ የሚያስረዳኝ እሻለሁ።"

እንግዲህ የጤና ባለሙያዎችን አስተያየት እንጠብቃለን።

**********************

# Lion Of Judah TRAVEL

••••የይሁዳ አንበሳ የጉዞ ወኪል••••

የበረራ ችግራችሁን ለማቃለል የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት በጠቅላላ በሰሜን አሜሪካ ውስጥና ወደ ኢትዮጵያ ለመጓዝ ሁሉ እንደዚሁም ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ አሜሪካ የሚመጡትን ደንበኞች በማገልገል ላይ መሆኑንና አገልግሎት መስጠት መጀመሩን ያስተዋውቃል

ከማንኛውም ዝቅተኛ ዋጋ ተጨማሪ ቅናሽ ከፈለጋችሁ ልናገለግላችሁ ተዘጋጅተናል!!

**Los Angeles (310) 275-7767 East Coast (703) 671-9175**

ከ ሳንዲየጎ, ሎስ አንጀለስ, ሳንፍራንሲስኮ, ሳንሆዜ, ሲያትል, ፖርትላንድ

ወደ ኒውዮርክ, ዋሽንግተን, ዳላስ, ሂውስተን, ሽካጎ, ቦስተን

ደርሶ መልስ የዋጋው መጠን $298.00

የአንድ ጊዜ የዋጋው መጠን $160.00

እንዲሁም ለአዲስ አበባና ለአሥመራ 1199.00

እንቁጣጣሽ

818•776•8484

18040 Serman Way Suite 122 Reseda, CA 91335



# Addisu Gebeya አዲሱ ገበያ

**We Carry Large Selection Of Ethiopian Foods & Spices**

*We have everthing you need to prepare an Ethiopian Feast !*

| DESCRIPTION | QTY(lb) | Price |
|---|---|---|
| 1. Berbere | 1/2 | 3.99 |
| 2. Mitan Shiro | 1/2 | 3.50 |
| 3. Aja | 1/2 | 3.50 |
| 4. Mitmita | 1/2 | 3.50 |
| 5. Awaze | 1/2 | 3.99 |
| 6. Butter Maker | 1 | 13.99 |
| 7. Tef | 1 | |
| 8. Mekelesha | 1 | 13.50 |
| 9. Kik | 1 | 0.49 |
| 10. Bakela | 1 | 1.79 |
| 11. Miser | 1 | 0.89 |
| 12. Kinche | 1 | 0.39 |
| 13. Telba | 1 | 1.25 |

NAME__________
ADDRESS__________
__________
CITY__________
STATE______ ZIP______
Tel. ( )__________

WE DO MAIL ORDER

Please Include $5.50 For Shipping And Make Your Check Or Money Order Payable To: Addisu Gebeya

- JEWELRY
- VIDEOS
- CASSETTES
- REKEBOTE (ረከቦት)
- COFFEE
- ETHIOPIAN ARTS
- ETHIOPIAN DRESS

AND MUCH MORE

2202 18th St. N.W.,
Washington, DC 20009
202 •986 •6013 / 23


# በላንዳፍታ መጽሔት ድርጅቶን ያስተዋውቁ!

በአጭር ጊዜ ውስጥ በጣም ብዙ ተወዳጅነትና አንባብያንን ባፈራችው የአማርኛ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት ድርጅቶን ማስተዋወቅ ብልህነት ነው።


ድርጅቶና ላንዳፍታ አብረው ይደጉ!


ሞዴት ModEth

ሞዴት

ሞዴት (ModEth) ... (Ethiopian Word Publisher) ...

... Each Ethiopic character is typed with the single key assigned to it. ...



... Amharic thesaurus ... multi-lingual ... word translation ... module; ... dBase, ModEth and ASCII ... mail merge and labels printing are included ...

Ethiopian Computers & Software
9781 W. Fremont Pl.
Littleton, CO 80123, U.S.A.

# እኔ አላማረኝም

ከዳዊት አስፋው (ኦክላንድ)

ውሱን ያጣ ሕይወት፣
ስርዓት ያጣ ዘመን፣
ያልታደለ ነፍስ፣
ዕረፍት ያጣ መንፈስ፣
ማረፊያ የሌለው ሰውነት።

ስደተኛው፣

በአለም ላይ ብቻውን የተፈጠረ የሚመስል፣
ብቻውን እየሄደ የሚያወራ፣

ለትምህርት ለኑሮ
ለሕልውና ሲያብሰለስል፣
አንዱም አልሳካልህ ብሎት
ወደ ዕብደት የቃጣው፣

ሰፊ ግቢ የነበረው፣
አሁን ግን መጠጊያ ያጣ፣
ቤት ቢኖረውም ኪራዩ ከአቅም በላይ የሆነበት፣
በብድር በኢንሹራንስ የሚንገላታ፣

በመኪና በቤት ዕዳ የተያዘ፣
በ"ቢሎች" ተወጥሮ ሊፈነዳ የደረሠ፣
ኸረ ስንቱ የስደተኛው ጣጣ!

በስራ ዋስትና አለመኖር፣
ዛሬ ሠርቶ ነገ መባረር፣
ዛሬ ተደስቶ ነገ ማዘን፣
ዛሬ ስቆ ነገ ማልቀስ

ሲገኝ ደግሞ የስራው ዓይነት ክፋቱ፣
ሕክምና ተምሮ ሰሃን አጠባ፣
ኤኮኖሚ አጥንቶ ግርድና፣
ሕግ አጥንቶ ዘበኝነት፣
ኢንጅነሩ መኪና ጥበቃ፣
ንግድ አዋቂው ጠራጊ፣
ምሩቅ ሆኖ ታክሲ ሹፌር፣
አይ ባዕድ ሃገር!

በትምህርት በሥራ የማይመኩበት፣
በዘመድ በወገን የማይኮሩበት፣
የልብ ወዳጅ ደህና ጓደኛ የማይገኝበት፣
ወገን በወገኑ የተጨካከነበት፣
እህት ከወንድሙ የማይስማሙበት፣

የሠው ልጅ የረከሰበት፣
ኡኡ ቢሉ የማይሠሙበት፣

ሌላው ደግሞ
ያለውድ በግድ የሠው ሃብት የሚመኙበት
የሚደፈነው ቀዳዳ የበዛበት፣
ግን እጁ ያጠረበት፣
ንግድ ሞክሮ የከሰረ፣
ትምህርት ጀምሮ ያቋረጠ፣
ፍቅር ጀምሮ የተፈነገለ፣
ትዳር ይዞ የፈታ፣
አግኝቶ ያጣ፣
እንዳልነበረው የሌለው፣
ወይም ትዝታው ብቻ የቀረው

አይ ስደተኛ!

ወይ ዘመድ አልረዳ
ወይ ስራው አልሆነ፣
አገር አልጠቀመ፣
ወገን አልደገፈ፣
ሳይወድ በብስጭት ጠጭ፣
ሳይፈልግ በንዴት አጫሽ፣
ሲያገኝ የሚበላ
ሲያጣ ጦም የሚያድር፣

ባገኘው አጋጣሚ ራሱን
ለማዝናናት ቢሞክርም፣
በድን አካሉ እንጂ ሕሊናው የማይጨፍር፣

ቲቪው እጅ እጅ፣
ሙዚቃው ቃር ቃር ያለው፣
ቀኑ ጨልሞ ሌሊቱ የነጋበት፣
የወደፊት ተስፋው የተሟጠጠበት፣
ኸረ አንድ በሉት!

አማራ ነሽ ትግሬ ቤት እንዳትገቢ ሲሏት፣
ትግሬ ነሽ አማርኛ እንዳትናገሪ ስትባል፣
አማራ ነህ ከኛ ቡድን አትገባም ሲሉት፣
ትግሬ ነህ አብረኸን አትሠለፍም ሲባል፣
በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አይሆንም?

ሰው የማይሠራው የማያስበው ያጣ ይመስል፣
ከሰላም ይልቅ ለጥቅም ከተጋበዘ፣
ከአንድነት ይልቅ ለመከፋፈል ከቃጣ፣
ከወዳጅነት ይልቅ ለዘረኝነት ከተነሳ

አዝማሚያው ወደየት ነው?
"እኔ አላማረኝም"

# « እውነት ከልብዎ ነው ? »

## ለዶቢሳው "ከስደተኛው ማህደር" መልስ ብጤ

ከአቦ ዮናስ አሸኔ (ናዝሬት)

"ያሳዋቂ ሳሚ . . . ይለቀልቃል" ይባል የለ! እኔም እንደተረቱ ከመሆኔ በፊት አስተያየቴ ሁሉ ለናንተው እንዲሆንልኝና እናንተ ብትታዘቡኝ ይሻላል ብዬ ልኬዋለሁ። ስለዚህ ላንዳፍታ ቅፅ "1" ቁጥር "3"ትን ያየኋት በባህር ማዶ የህይወት መነፅር ሣይሆን በሃገሬ ባህልና ወግ መነፅር ስለሆነ ሃሣቤ ይህን ይመስላል።

. ላንዳፍታ እያያዝዋም ሆነ ድምርዋ ጥሩ ነው። ያዘጋጁ ክፍልም ቢሆን። የሚደነቅ እንቅስቃሴ አለው ብል ማጋነን አይሆንብኝም። ይህ ክፍል ለሚደርሱት ደብዳቤዎች የሚሰጠው መልስ ከልብ የሚያስደስትና የአርቆ አስተዋይነት ምልክት እንዳለው እንዲሁም ገራምነት፣ ትህትና፣ ታዛዥነት፣ ሁሉን እሺ ባይነት፣ የትዕግስተኛነትና የአፍቃሪነት ፀባይ በውስጡ እንዳለ ከሚሰጠው መልስ ለመረዳት ይቻላል። በዚህ መልኩም ላንዳፍታ ብዙ አዲስ ደንበኞችንና ተሳታፊዎችን እንደምታፈራ ዕምነት አለኝ። በተረፈ የመጀመሪያውን አስተያየቴን ለአቶ ዶቢሳው እንዲሆንልኝ ልኬላችዋለሁ።

ይድረስ ለዶቢሳው፤– ከስደተኛው ማህደር የሚለው መጣጥፍዋን አነበብኩት። ለኔ ግን ይህ መጣጥፍዎ ከራስዎ ሃሣብ ጋር የሚቃረን ይመስለኛል። አዩት ልብወለድም ቢሆን እኮ የእውነተኛ መስመር መከተልና የተደራሲውን ስሜት መኮርኮር ማሳመንም አለበት።

ዶቢሳው በትረካዎ አጀማመር በቤተሰብዎ ላይ የደረሰውን የግፍ ሁኔታ አጣፍጠውና አሳዝነው ሲያቀርቡት የእርሶን የስደትና የመከራ ገጠመኝዎን ግን አበላሹት። በዚህም ሣቢያ ከአንደበትዎ አፍልቀው የጻፉት ድርሰትዎ ኮፍያ ሲሆን የስደትዎ ሁኔታ ደግሞ ጫማ ይሆናል ማለት ይቻላል። ባጠቃላይ መጣጥፍዎ ከእርሶ ስሜትና ባህርይ ጋር የጫማና የኮፍያ ያህል ልዩነት አላቸው። እስቲ ለማንኛውም የድርሰትዎን ሁኔታ እናስተውለው። እርሶም ከልብ ሆነው አስተውሉ። "ከመናገርህ በፊት አስብ አስተውል" ተብሏልና!!

ዶቢሳው ድርሰትዎ የእርስዎን የትውልድ ስፍራ ባይጠቅስም መከራ ያዩባት ታናሽ እህትዎ ግን ሸገር እንደተወለደች፤ እናትዎም በደረሰባቸው መከራ እድለ ቢስ እጣ እንዳለችውና የቀን ጨለማ ሲውጣቸው ኑሮ እሬት ሆኖ ሲመራቸው ቀንም የማይገፋ ሆኖ ሲመስላቸው እርሶን ተከትለው ስለመሸሻቸው በውብ ቃል አትተውታል።

እንግዲህ የእርሶ እናት ከሌሎች እናቶች ሁሉ በመታየታቸው ሳቢያ የከፋ መከራ የደረሰባቸው በመሆኑ ለእርስዎም እናትዎ እጅግ እሩህሩህና እርስዎን ብለው አብረው ስለመሰደዳቸው "ጉሽ ለልጅዋ ስትል ተወጋች" የተባለውን ተረት በተግባር በመፈፀማቸው እናትዎን የሚያስመሰግናቸው ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ የተቀሩት የኢትዮጲያ ልጆች እናቶች ደግሞ እንደናትዎ ሩህሩህና አዛኝ ቢሆኑ ኖሮ በመጀመሪያው ዙር የብሄራዊ ውትድርና ምልመላ ጊዜ እንደናትዎ መሰደድ ቢያቅታቸውም ልጃቸውን ተከትለው አብረው ስልጠና በገቡ ኖሮ ዳሩ ሁሉም ጨካኝ ነበሩ እያሰኝም። ዶቢሳው! ዳሩ ግን ሁሉም እናት እንደርስዎ እናት አልነበሩም። ቢሆኑማ ኢትዮጲያችን ወንድ ልጅ ባጣች መሃን በሆነች ነበር። ገጣሚም እኮ፤–

"የወንድ ልጅ እናት ታጠቂ በገመድ
ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ"
ብሎ ጨርሶታል...

ዶቢሳው እንደአባባልዎ ከሆነ ለስደትና ለመከራ ያበቃዎት የብሄራዊ ውትድርና ምልመላ ምጣት መሆኑን ከገለፁ በኋላ ፈረሶትን ቼ! ብለው ወደ ሱዳን ያስፈረጠጡትን ሲተርኩ ደግሞ "ጎረቤቴ የነበሩ ወጣቶች በግድ እየተያዙ፣ እናቶች እያለቀሱ ሲወሰዱ ሳይ "ነግ በኔ" ነው ብዬ የቤተሰብ፣ የወገን፣ የአገር ፍቅር ስሜት እያንገበገበኝ ጠፍቼ ሱዳን የገባሁት ለሱዳን ሀብታም አሽከርና ገረድ የሆንኩት፤ . ." ብለዋል። እዚህ ላይ ነው ዶቢሳው! ድርሳንዎ ጫማና ኮፍያ የሆነው አዩ!! "የወገን፣ የአገር ፍቅር ስሜት እያንገበገበኝ..." በማለት ያስፈሩት ቃል ትርጉሙ ምን እንደሆነ በውል የተገነዘቡትና ያጤኑት አይመስለኝም። የቃሉን ትርጉም አስቀድመው ቢያውቁና ስሜቱም የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል በውስጠ ቢኖር እንደአባባልዎ "ነግ በኔ" ብለው ባልኮበለሉ ነበር። ይህ "ነግ በኔ" የሚለው ቃልዎና ስሜትዎ በጉልህ የራስዎን ማንነት ማለትም ራስ ወዳድ ሰው መሆንዎን ይገልፃል። ስለሆነም እርስዎ አስቀድመው አላወቋትም እንጂ ራስዎን ወዳድ ሆነው ጥለዋት የሸሸዋት ኢትዮጲያ እኮ ሃገርዎ ነበረች። ሊያውም እድነኝ፣ ድረስልኝ፣ ተሰዋልኝ እያለች የምትጠራዎና የምትማጸንዎ እናትዎ ነበረች። ታድያ ጥለዋት ከተሰደዱ በኋላ ነው "የወገን የአገር ፍቅር ስሜት እያንገበገበኝ"...የሚሉት። ታድያ የአገር ፍቅር ስሜት አለኝ ካሉ ኢትዮጵያ ደግሞ ከእናትዎ በላይ የሆነች ሃገርዎ መሆኗንስ ለምን ዘነጉ? ለምንስ ይሄን በመሰለ ቃላት ጽሁፍዎን ይከሽናሉ?

ሃገር ወዳድ መሆንዎ እኮ የሚታወቅሎት ከተግባር እንጂ ከአፍዎ አይደለም። እንዳው ዶቢሳው ይህን ቃላት በእርሶ አንደበት ደፍረው ሲናገሩት ጉሮሮዎን እንኳን አላነቆትም? ስሜቶንስ አልሸነቆጠትም? መቼም አይፈረድቦትም፤ ዳሩ ዘመኑ የሸፍጥ ሆኖ ነው እንጂ እውነት እንዲህ የሚፈነጩበት የቃላት ጋጋታ ባልነበረ። እረ ለመሆኑ እርስዎ ይኼን ያሉ ሌላው ለሃገሩ ድንበር ሲል የደማውና የቆሰለው ኢትዮጵያዊ ምን ይበል? ዶቢሳው "አሁን እነሱስ እንደርስዎ በአፍ ሳይሆን በልባቸው ከራሳቸው በፊት የወገንና የሃገር ፍቅር ስሜት አንገብግቦአቸው ነው። የእርስዎ ግን የተገላቢጦሽ "ይህንን ሲጽፉ ባለማፈርወዎ ገርሞኛል። ደፋር ነዎት ጃል፤" እንዳው ዶቢሳው ይህን የጻፉት ግን ከልብዎ ነው ወይስ ሀገር ወዳድነትዎን በይምሰል ድርሰትዎ መግለፅዎ ነው? የሆነስ ሆነና ይህን ስሜት ያለው ሰው ይኮበልላል? ይሰደዳል ዶቢሳው?

ባይሆን ከጻፉ አይቀር ኢህአፓ ሆኜ ደርግ ሊረሽነኝ ሲል ጠፋሁ ብትሉ ድርሰቱ ምን ያህል በተዋጠሎት ነበር። ዳሩ ይህን የጻፉት የድርሰትዎ ቃል ሁሉ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ባዶ በርሜል ሆኗል ማለት ይቻላል።

አሁንም ዶቢሳው በጹሁፍዎ "...በዕውነቱ ከድንጋይ እንደተፈጠርንና ሀገር እንደሌለን መሆናችን፣ ወኔ ሳያንሰን ወኔ እንደሌለን መሆናችን በጣም አሳዘነኝ።..."የሚል ቃል አስፍረዋል። "አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል፤"አለ ያገሬ ሰው። ለመሆኑ ዶቢሳው ይህ የጻፉት ድርሳን ከተግባሮ ጋር አይቃረንም? አይጋጭም? ነው ወይስ ድርሰት ማሣመሪያ ነው "ሀገር እንደሌለኝ" የሚለው አማርኛዎ ሱዳን ነው ትዝ ያልዎት ወይስ ስደትዎ ነው ይህን ቃል ያስተማርዎት? አዩ "አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል" ያልኮት ለዚሁ ነው። ይህችን አገር የገደላት አንዱ አፍ ነው ማለት ይቻላል። በላይ ዘለቀም፤-

"ሀገሬ ኢትዮጲያ ሞኝ ነሽ ተላላ
የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ"

ያለው ወዶ አይደለም።

ታድያ እርሶም ሱዳን ትዝ ያለችዎን ሀገርዎን በመከራዋ ግዜ ጥለዋት ከተሰደዱ በኋላ ዛሬ ትዝ ብላዎት ሃገሬ ሃገሬ ቢሏት ምን ይፈይዱላታል? በመሆኑም ዛሬ በአፍዎ ሀገሬ፣ ሀገሬ ያሏትን አስቀድመው ሀገርዎ መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ የሚመጣብዎን መከራ ሁሉ ያውም ለማንኛውም የሀገሩ ዜጋ የመጣውን ፅዋ በፀጋ በተቀበሉት ነበር። ሌላው "ወኔ ሳያንሰው ወኔ እንደሌለው "የሚሉትስ ለመሆኑ ይህ አባባልዎ የተሰደዱትና ደረሰብኝ የሚለው መጣጥፍዎ የሚያወራው ስለእርስዎና ስለቤተሰብዎ ብቻ ነው።

ታድያ ለምን ድፍን ኢትዮጲያ እንደተሰደደ አድርገው በጥቅሉ ጻፉ። "ወኔ ሳያንሰኝ" ቢሉት አይሻልም ነበር። ድሮም እኮ ዶቢሳው "ወኔ ባያንሶት ኖሮ አይሰደዱም ነበር።" አይደለም እንዴ? በተለይ እንደ ሁፍዎና እንደ አንደበትዎ አባባልማ ቢሆን ኖሮ ኤርትራም ባልተገነጠለች ነበር አይመስሎትም?

ዶቢሳው ከመጣጥፍዎ ጋርም ይህችን ግጥም:-

"ሰው በሃገሩ፣ ሰው በወንዙ፤
ቢበላ ሳር ፣ቢበላ መቅመቆ፣
ይታወቅ የለም ወይ ሰውነቱ ታውቆ።"

በማለት አስረድተዋል። ትክክለኛ አባባልን የያዘች ግጥም በመሆኗ እኔም እመሰክርላታለሁ። ታድያ ይህ አባባል ማለት ያለባቸው እርስዎ ሳይሆኑ በግል ከሃገሪቱ መንግስት ጋር በፖለቲካ፣ በተፅዕኖ ወይም ለመማር፤ ለማግኘት በመሣሰሉት ችግሮች ሣቢያ ከሃገራቸው በወጡ ዜጐቿ አፍ ቢነገር ያምራል። እርስዎም እንዳው ድርሣኔ ይመር ብለው ጻፉ እንጂ ይህ የጻፉትን ግጥም እንኳን ለምሳሌ የመጀመሪያዋን ስንኝ ሃሣብ በውል ቢያውቁና ቢገነዘቡ ኖሮ በብሄራዊ ውትድርና ምክንያት ተሰደድሁ ባላሉ ነበር። "በገደል በዱር ሙጫ ፍራፍሬ እየበላሁ ከጋራ ጋራ ስንከራተት እነሆ ዛሬ ነፃነቴን ተቀዳጀሁ እድሜ ለኢህአዴግ" ከሚሉት ጋር በደመርኖት ነበር። ስለዚህ ይህ ግጥምዎ እንደርስዎ "ነግ በኔ" ብለውና ራስ ወዳድ ሆነው ለተሰደዱት ሳይሆን ለእውነተኛ ኢትዮጲያዊ ልጆችዋ ነው። ፊትም አሁንም ለእውነተኛ ፍትህና ነፃነት ሲታገሉና በመታገል ላይ ላሉት በውጪ ላሉ ወገኖቻችን ነው። እርስዎማ ለአገርዎ መሞትና መድማት ሊያውም ይኼ እድል ሳይገጥሞት ይችላል። እንዳው ሞትን ፈርተው ብቻ ሌላው በተሰዋላት መሬት ተመልሰው ለመኖር ሲሉ ስደትዎን ተያያዙት። ለመሆኑ ሞትስ ሱዳን የለም እንዴ ዶቢሳው?

ዶቢሳው እንዳው በፈጠረዎ የመጣጥፍዎን አጀማመር ጥሩ ሆኖ ሳለ አጨራረሱን ግን ምነው አበላሹት? ባይሆን ስደትዎን በፀረ ህዝብነት ተጠርጥሬ...ቅብርጥሴ...ምንትሴ...ብለው ቢጽፉ ኖሮ ውነቴን ነው ድርሰትዎ ምንኛ ባማረ ነበር። አዩት የብሄራዊ ውትድርና ምጣት እኮ ለእርስዎ ብቻ አይደለም። ለሁላችንም ኢትዮጵያውያን ሁሉ እኮ ነው። አዩት ዶቢሳው እርስዎም ሆኑ እርሶን መሰል ሰዎች የሆንን ሁሉ ከራስ ወዳድነታችን የተነሣ አንድ ያልተገነዘብነው ሃቅ አለ። መጽሐፍ ቅዱስ "በአንተነትህ ዓይን ላይ ያለውን ትልቁን ጉድፍ ሳታጠራ የሌላውን ትንሽ ጉድፍ አታጥራ" ብሏል። የኛም ትልቁ ችግራችን ይሄ ይመስለኛል። ያኔ ኃይለ ሥላሴን "ሌባው ጨቋኙ አድሃሪው ንጉስ" ብለን እንዳልጮህን ሁሉ ዛሬም ደርግ 17ዓመት ጨቋኖን

አፍኖን ብሄራዊ ውትድርና መልምሎን...ገርፎን ...ሰቅሎን...መልሳችን ይሄው ብቻ ነው። እኛ ግን የበኩላችንን ሁሉ በቅንነትና በእውነት ፍቅር ስሜት ሆነን ለሃገራችን አልሰራንላትም ብል አላፍርበትም። ይህ ብሄራዊ ውትድርናም ቢሆን በሃገራችን ብቻ አይደለም የተጀመረው በሰለጠኑ ሃገሮችም ቢሆን የዚሁ ዓይነቱ ምልመላ እንደሚፈፀም አያውቁም ዶቢሳው። ስለዚህም እኛ ለሃገራችን ምን ሠራንላትን ትተን እርስ በእርሳችን የምንወነጃጀል፣ የተንኮል፣ የምቀኝነት የመሣሰሉት ተፈጥሮ የኖረንና አብሮን ያለ ነው። ስለሆነም ሃገራችን ጀግንነትን መስዋዕትነትን ብትጠይቀን ፊት አዞርንባት፣ ሸሸናት፣ መሞቱን መድማቱን ጠላንላት፤ ልንሸሻት ልንርቃት ዘወትር ተመኘን፤ የቻለ ሸሻት፤ እርሶም ሱዳን ገቡ፤ ይህ ነው ሃቁ ዶቢሳው። ለዚሁም ነው በላይ ዘለቀ "የገደለሽ በላ"ያለው "እውነት ትመነምናለች እንጂ አትጠፋም።" እና ዶቢሳው ሃሣቤን ከመቋጨቴ በፊት አንድ እንዲታወቅልኝ የምፈልገው እኔ ይህን እንድጽፍሎት ያነሣሣኝ የእርስዎ "የወገንና የሃገር ፍቅር ስሜት እያንገበገበኝ" የሚለው አቋሞን ጠንካራ የሆነውን የሃገር ወዳድ መንፈስዎን በምን አይነት በ"ነግ በኔ" ሳብያ የብሄራዊ ውትድርና መምጣት ለስደት አያበቃም ለማለት እንጂ እኔ ያለፈውን ስርዓት አራማጅ ወይም አቀንቃኝ ሆኜ እንዳልሆነ አስቀድመው ይወቁልኝ። ተግባባን? አመሰግናለሁ!! ቸር ይግጠመን።

********************************
**

## ? ? ምን ትመክሩኛላችሁ ? ?

(ከአዛለች)

ከአገሬ ከወጣሁ ሁለት ዓመት ገደማ ነው። ብዙ ዓላማ ነበረኝ። በርግጥ በወቅቱ በወጣቶች ይደርስ የነበረው ችግር አገሬን ለቅቄ እንድወጣ ግፊት እንደነበረው አልክድም። አወጣጤ ሽሽት ብቻ እንዳልነበረና ከዚህ ታላቅነቱ ከሚወራለት አገር ላገኝ የምችለው ብዙ ጠቃሚ ነገር እንዳለ እያወቅሁም ነበር። አገሬ እያለሁ አሜሪካንን በጣም ከሚያመልኳት ወገን እንኳ ባልሆንም በቴክኖሎጂ ዕድገት ያላትን የበላይነት በመረዳት ከሚያደንቋት አንዷ ነበርኩ ብል ከልቤ ነው። ያም ሆነ ይህ ያለ የሌለውን መንገድ ሁሉ ተጠቅሜ፣ ዘመድ አዝማድ መውጫ መግቢያ አሳጥቼ፣ እናቴም በሌላት ገንዘብ "ልጄ ሰው ሆና ትረዳኛለች፤" በማለት ተበድራ ተበዳድራ መሳፈሪያዬን ሰጥታኝ ነበር የመጣሁት። ለሕይወቴ፣ ለወደፊት ኑሮዬ ያለው መንገድ የኔ ወደ አሜሪካ መምጣት እንጂ ሌላ ምንም አማራጭ እንደሌለ አድርጌ ነበር ዘመድ አዝማድን ያሳመንኩት። ትዝ ይለኛል አጐቴን ለማሳመን የአሜሪካ ፊልም

ከሚታይበት ሲኒማ ቤት እዘውትረ ይዤው እሄድ የነበረው። እናቴን ለማሳመን አጐቴ ያደረገውን ጥረት መቼም አልረሳውም። ሁሉም ነገር ተሳካና አሜሪካም መጣሁ። የመጣሁትም ከኔ በጣም ቀደም ብላ ከመጣች አንዷ የአክስቴ ልጅ ጋ ነው። መቼም ስለሷ አገር ቤት የሚወራው ሌላ ነበር። በየጊዜው ከምትልካቸው ፎቶ እንደተረዳነው የሰውነቷ ማማር፤ የምትኖርበት ቤት ውበት፣ የምትለብሰው ፋሺን፣ ለጉድ ነበር። ለኔ ወደ አሜሪካ መምጣት አንዱ ግፊት የእሷም ሁኔታ ነበር ብል አልሳሳትም። የአክስቴ ልጅ በደስታ ተቀበለችኝ። እንደመጣሁ ትምህርት ቤት የምገባ መስሎኝ ነበር። ግን አልሆነም። አገር እስክላመድ ድረስ ተብሎ ቤት ተዘግቶብኝ አንድ ሁለት ወር ያህል ቆየሁ። አቤት ታዲያ ያ አገር ቤት ያጓጓኝ የነበረው ፊልም ወጣልኝ። ጣቢያ እየቀያየርኩ አንዴ ዘፈኑን፣ አንዴ ፊልሙን ሳይ የመጀመሪያው ወር እምብዛም አልተሰማኝም። የአክስቴም ልጅ ከሥራ አምሽታ ስትመጣ በመኪና እያዞረች ከተማውን ታሳየኝ ስለነበር ዓለም የገባሁ መሰለኝ።

በመጣሁ ሁለተኛው ወር አጋማሽ ላይ ቤት መዋሉም እየሰለቸኝ ሲመጣ የትምህርት መጀመሩ ጉዳይ ይታየኝ ጀመር። ከመምጣቴ በፊት ዓላማዬ ብዬ ወስኛለሁና የአክስቴን ልጅ አነሳሁባት። ትምህርት ለመቀጠል ያለውን ችግር ነገረችኝ። እሷ ከመጣች አምስት ዓመት አልፏት ትምህርት እንዳልጀመረች ያወቅሁት ያኔ ነበር። አገር ቤት የሚወራውማ ሌላ ነበር። ዲግሪዋን አግኝታ ትልቅ ኩባኒያ ውስጥ ተቀጥራ ቢሮ እንደምትሠራ ነበር የሰማሁት። ይህን ስነግራት "ትንሽ ስትቆዪ ሁሉን ታይዋለሽ፣" አለችኝ። ትምህርት ቤት ለመሄድ ያለውን ክፍያ ብዙም አላውቀውም ነበር። "ሥራ ሠርቶ ገንዘብ አጠራቅሞ ያንን እየከፈሉ መማር ነው ያለው መንገድ።" ብላ ስትነግረኝ እሷ ታዲያ ለምን አጠራቅማ ገብታ መማር እንዳልቻለች አልጠየቅኋትም የዛን ጊዜ። ባልጠይቃትም መልሱን ከከራረምኩ በኋላ አገኘሁት። የቤት መዋሉ መሰልቸት ብቻ ሳይሆን እኔም እንደ አክስቴ ልጅ ሥራ ይዤ ገንዘብ በማምጣት የቤቱን ወጪ ለመሸፈን መርዳት እንዳለብኝ በቀጥታም ባትነግረኝ ከሁኔታዋ ልረዳ ቻልኩ። የትምህርት መቀጠል ዓላማዬ ጋብ አለና ስለ ሥራ ማግኘት ማሰብ ጀመርኩ።

ሥራ ለማግኘት የሥራ ፈቃድ ያስፈልጋል። የመጣሁት በተማሪ ቪዛ በመሆኑ ያ ሥራ ለመያዝ የማያስችል ስለሆነ ሌላ ዘዴ መጠቀም እንዳለብኝ ተረዳሁ። በስደተኝነት መመዝገብና ለዚህም ጥሩ ጠበቃ ይዤ ማመልከት እንዳለብኝ ተመከርኩ። ከአገር ቤት አዲስ (fresh) ሴት ልጅ መጥታለች ከተባለበት ቤት የሚግተለተለው ብዙ ነውና ሁሉ ሀሳቢ በመምሰል የሚሰጠው ምክር ሌላ ነው።

(ወደ ገጽ 31 ይዞራል)

# ሁሉም . . ሲርቁ ነው

እያሌው ታደሰ (ሚኒያፖሊስ)

ከተራራው ከወንዙ ማዶ፣
ሸንተረር ሸለቆው ከለያየኝ ጋርዶ፣
ከንፋሱ ሽውሽውታ ከወጀቡ ተዋህዶ፣
ትዝታ ከነጓዙ ናፍቆትን አዛምዶ፣
ሀገራዊ ውበትን ከወገኔ ለዛ አጣምዶ፣
ዕረፍት ነሣኝ እየመጣ፤
ያ ፍቅር ያ ተለምዶ።

ነግቶ ወገግ ሲል አዕዋፍ ሲንጫጫ፣
ድው ድው በያአቅጣጫው የቡናው ሙቀጫ፣
እማማ እከሊ ቡና ጠጡ እያልኩ
ያለብኝ ሩጫ፣
የቡና ቁርስ አቀብል፤
እደጅ ተጫወት፤ ተብሎ ቁንጥጫ።

ረፈድ አድርገን ጨርቅ ኳሷን ይዘን፣
በኪስ በኪሳችን ኅብስት አሹቅ ሞልተን፣
መንደር ካለችው መስክ ተሯሩጠን ደርሰን፣
በሁለት ተከፍለን በቡድን ተጋጥመን፣
ግራ ቀኝ፣ ፊት ኋላ ኳሲቱ ተባርራ፣
ማኖ የቅጣት ምት ብላ ተመትራ፣
በድንጋዮች መሐል ኳሲቱ አምልጣው፣
ጐል ትባልና አንድ ወገን
ሲኰራ ተኰርፎ ሊላው።

እንዲያም ይሆንና ድሌ ማታ ነው ድሌ፣
እኔ ወንዱ ልጅ ይኼው ነው አመሌ።

ብዬ ተወጥሬ በትንሽ ደረቴ፣
ብልጭልጯን ዋንጫ ስወስድ ለጥረቴ፣
ከቶ አይረሳኝም የልብ ኩራቴ።

ያ የልጅነት ወቅት ለዛ የነበረው፣
ያ የሀገር ውበት በዙሪያ ገብ ያለው፣
በዓይነ ሕሊናዬ አርቄ የማየው፣
ለካ ሁሉም ነገር ሲርቁ ነው የሚያምረው፣
በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ነው የሚቆጠረው፣
ሲባል አልመስል አለኝ መቼ ተረድቼው፣
በርቀት መስተዋት ጎልቶ መቼ አይቼው።

በትሬን ድው ድው በሱ ሆያ ሆዬ፣
ሣንቲም በሚስጥር ኪስ ሸልጦ አዝዬ፣
ኩስ ኩስ እያልኩኝ በዙርያ በገባው፣
ወዳጄን ዘመዴን ሳሞግስ ስከበው።

"ይሔ የማነው ቤት የኰራ የደራ፣
የጋሽዬ ነወይ የዚያ የቀብራራ፣
እዚችም እዛችም ትዘላለች ጠጣ፣
እኔ አልለቅም ዛሬ ነፍሴ ብትወጣ።"

እያልኩ የዞርኩበት የትውልድ መንደሬ፣
ዕንቁጣጣሽ መጥቶ አበባ አዙሬ፣
ሣንቲሜን ስለቅም ለብይ ለደብተሬ።

ድፎ ዳቦው ቀርቦ በጉ ጠዋት ታርዶ፣
ጠላው በሽክና የቅርጫው ብርንዶ፣
ገናን አሣልፈን አምሮብን በጥምቀት፣
አጅበን በሆታ የመንደሩን ታቦት።

"ፀሐይ፣ ፀሐይ፣
ፀሐይ ሰረቀ ፀሐይ፣ ፀሐይ ሰረቀ
ፀሐይ ሰረቀ ክርስቶስ ተጠመቀ"
ያ አኩሪ ባህል የጥንቱ የጠዋቱ፣
ዘመናት ያልሻሩት በፁብ ድንቅነቱ።

ዛሬ ተደማምሮ አንድ ሆኖ መጥቶ፣
በዓይነ ሕሊናዬ ቁልጭ ብሎ ገብቶ፣
ቀስቅሶ ገደለኝ አለሁ አለሁ ብሎ።

ኩሉ የምንጭ ውሃ የወፉ ዝማሬ፣
የመስኩ የአበባው የዛፎቹ ፍሬ።

ጋራው ሸንተረሩ ደን የተላበሰው፣
ፏፏቴው ከገደል የሚወረወረው፣
የወንዙ ሸለቆ እጅግ የጠለቀው፣
ያኔ እዚያ ሣለሁ ልብም የማልለው፣
ለካ ሁሉም ነገር ሲርቁ ነው የሚያምረው።


የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ለመሆን ወይም በስጦታ ለመላክ

[illegible]

U.S.A $12.00
Canada U.S.$15.00
Europe U.S.$18.00

የላንዳፍታ መጽሔት ግዢና ትእዛዝ

NAME
ADDRESS
CITY/STATE/ZIP
PHONE
BACK ISSUE ORDERS

ላንዳፍታ መጽሔትን ለጓደኛ፣ ለዘመድ ይላኩ፤ የቤተሰብ መጽሔት ናትና፤

NAME
ADDRESS
CITY/STATE/ZIP
PHONE
BACK ISSUE ORDERS

[illegible] Payable to LANDAFTA [illegible] Money Order [illegible]

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
Atlanta, GA 30359

# አዳም ና ሔዋን

## « የመጀመሪያው አቀራረብ »

ከእንዱዓለም (ቺካጎ)

በሁለት ተቃራኒ ጾታዎች መሐል የሚደረግ ከፍተኛ ግንኙነት ጋብቻ ነው። አንድ ወንድና አንድ ሴት በፍቅር ተግባብተው አንድ ሆነው አብረው በመኖር ከአብራካቸው ልጆች ወስደው የሚኖሩበት የማህበራዊ ግኑኝነት መሠረቱ ጋብቻ ነው። እንግዲህ ጋብቻ ክቡር የሆነ ግኑኝነት ነው ካልን ይህን የምንፈፅምበት ጊዜና ሁኔታ በሕይወት ውስጥ አንዳንድ ታላቅ ጊዜ ከሚታዩት አንዱ መሆኑን መረዳት አለብን። ስለጋብቻ ብዙ ተብሏል፣ ብዙ ተፅፏል፣ ብዙም አከራካሪ ነገሮች ተነስተዋል። ይህ ጽሑፍ በነኚህ የተለያዩ አመለካከቶች መሐል ያለውን ክርክር ለማንሳት ሳይሆን በተለያዩ ባህሎች ጋብቻን ለመፈፀም የሚደረጉትን ቅድመ ዝግጅቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል።

ከአያት ከቅድመ አያት ሲያያዝ የመጣ የጋብቻ አፈጻጸም ልምድ እንደባህል ይቆጠራል። ለምሳሌ በአገራችን በተለያዩ ብሔረሰቦች ያለው የጋብቻ አፈጻጸም በመጠኑ የተለያየ ይምሰል እንጂ መሠረቱና አፈጻጸሙ በአብዛኛው ተመሳሳይነት አለው። የተጋቢዎቹ ማለትም የባልና የሚስቱ አባቶችና እናቶች ጋብቻውን በማጽደቅ በኩል የሚጫወቱት ሚና ተመሳሳይ ነው። ሥልጣኔ ከተስፋፋ በኋላ የመጣውን የዛሬው ሁኔታ ስናይ ጥንት ወሳኞቹ፣ ለጋብቻው መፈፀም የሚስማሙት የሁለቱ አባቶችና እናቶች ናቸው። ይህ በሁሉም ብሔረሰብ ዘንድ የነበረ ነው። የአፈፃፀሙ በተለይ የሠርጉ ሁኔታ፣ የጫጉላው አከባበር፣ የመልሱ ወዘተ... እንደ አካባቢው ሁኔታ በመጠኑ የተለያየ ቅርፅ የያዘ ይምሰል እንጅ ተመሳሳይነት አለው። ይህን በሚመለከት ሰፋ ያለ ጥናት ኖሮኝ አይደለም ካነሳነው አይቀር ጠቀስ አድርገን እንለፍ ለማለት ነው። ወደ ዋናው ነጥቤ ልምጣና አሁን ባለንበት የስልጣኔ ደረጃ ጋብቻውን ለመፈጸም የሚያስችለንን ሁኔታ እንዴት ማመቻቸት እንዳለብን በመጠኑ እንወያይ። ደረጃ በደረጃ እናያለን። ይህን በመጀመሪያ የመተዋወቁ ጉዳይ ነው። ሁለቱ ማለትም ወንድና ሴቱ በአንድ አጋጣሚ ይተዋወቃሉ። በግብዣ ላይ፣ በቤተክርስቲያን፣ ሥራ ቦታ፣ ትምህርት ቤት፣ ወዘተ... ወይም በጓደኛ አማካይነትም ሊተዋወቁ ይችላሉ።

እንግዲህ መጀመሪያ በዓይን ተያይቶ መፈቃቀድ ማለት ነው። "ሳያት ድንግጥ አልኩ" ወይም "ሳየው የልቤ ምት ጨመረ" የሚባለው የመጀመሪያው የመፈቃቀድ ምልክት ነው። ከዚያ በኋላ መቼም ያለ ነውና ወንዱ ደፈር ብሎ ቀረብ ይልና ራሱን ያስተዋውቃል። ይህ የመጀመሪያ አቀራረብ ሁኔታ ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳለው ብዙ ሴቶች ይናገራሉ። በባህላችንም ይሁን ሰለጠነ በሚባለው አካባቢ ሴቶች እራሳቸው ደፍረው ወንዱን ቀርበው አይጠይቁትም። መፍቀዳቸውን የሚያሳዩበት ግን ብዙ ምልክቶች አሏቸው። ታድያ ይሄን ቀልጣፋ ወንድ ቶሎ መረዳት መቻል አለበት። ለምሳሌ ፓርቲ ላይ፣ ግብዣ ላይ ከርቀት አንዷን ያያል። ታየዋለች። ደንገጥ ይልና ደጋግሞ ያያታል። እሷም ሰረቅ እያደረገች ማየት ካበዛች ነገር አለ ማለት ነው። እንዲያው አየዋት ደስ አለችኝ ብሎ ዘሎ ጉብ ማለት መሞከርም ተገቢ አይደለም። ያለችው ከማን ጋር ነው? ይህን ማጤን መቻል አለበት። ከባሏ ወይም ከእጮኛዋ ወይ ከምታከብራቸው ቤተዘመዶቿ ጋር ልትሆን ትችላለች። በመጀመሪያ ከርቀት ፈገግታ ማሳየቱ ጥሩ ነው። ለፈገግታው አፀፋውን ከመለሰችና ከፈገግታው በኋላ ሰረቅ እያደረገች ማየት ካበዛች አንዳንዴ ለመናገር ሁኔታውን ራሷ ልታመቻች ትችላለች። ተነስታ ብቻዋን የምትሆንበት ቦታ ትመርጥና ወደዚያ ትሄዳለች። ያኔ እንግዲህ ከተል ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ መጠንቀቅ የሚያስፈልግበት ሁኔታ አለ። አንዳንድ ሴቶች አብሯቸው ግብዣው ቦታ የመጣውን ወንድ እየተንቀዠቀዠ ካስቸገራቸው እሱን ለማስቀናት ሲሉ የፈቀዱ ለመምሰል ይሞክራሉ። ለእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ደግሞ መሣሪያ ለመሆን መሞከር ሞኝነት ነው።

ቀደም ሲል በወጡ የላንዳፍታ እትሞች "እሱና እሷ" በተሰኘው ርዕስ በጭውውት መልክ የተለያዩ አቀራረቦችን በኮመዲ ዓይነት ለማሳየት ተሞክሯል። "እሱና እሷ" መሃል የተደረጉት ጭውውቶች በኮመዲ መልክ ቀርበው አስቂኝ ይምሰሉ እንጂ በውን የተፈፀሙ ድርጊቶችን ለማመልከት የተቀረፀ መሆናቸውን ማወቅ አያዳግተንም። "ላንዳፍታ" በጭውውቶች መጨረሻ ልይ ስለ "እሱ" አቀራረብ፣ ስለ "እሷ" አቀባበል እንድንተችበት ጋብዛን ነበር። እንግዲህ እነኚህን የተለያዩ አቀራረቦችን ስንመለከት የአንዳንዱ ወድድ አቀራረብ ድርቅ ያለ፣ ያንዳንዱ ሙዝዝ ያለ፣ ያንዳንዱ ደግሞ ከልጅቷ ግምት ውጪ የመጠቀ (አራዳነት የበዛበት

ብንለው)ሆኖ በመጨረሻ ባለመግባባት ሲለያዩ እናያለን። አንድ መታወቅ ያለበት ቁምነገር አለ። ልጅቷ ገና ስታየው በጣም የፈቀደችው ከሆነ ምንም ዓይነት አቀራረብ ይኑረው አትሸሸውም። መፈለጓንም ወዲያው ግልፅ ማድረግም አትፈልግም። የትውውቅ ጨዋታው እንዲራዘም መንገድ ከፈለገች ሰውዬውንበቁመናው ፈቅዳዋለች ማለት ሊሆን ይችላል። ቢሆንም የሰውዬው የመጀመሪያ አቀራረብ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው። ፈረንጆችም (First Impression) የሚሉት ነው። እንዳው የተለያዩ ሴቶች በወንዶች የመጀመሪያ አቀራረብ ላይ ያላቸውን አስተያየት እንመልከት። ይህን ከተለያዩ ሴቶች ያገኘሁት ነው።በሙሉ ያገኘሁዋቸው አስተያየቶች ትክክል ባልሆነ አቀራረብ ላይ የተመሠረቱትን ነው።

1. አንዳንድ ወንዶች አንዲት ሴት ከመግባባት ባህርይዋ የተነሳ ፈገግ ያለች ወይም ተጫዋች ከሆነች ፈቅዳኛለች በሚል ግምት ግትር ያለ አቀራረብ አላቸው።
2. በአንድ ጊዜ ትውውቅ ስለራሳቸው በብዛት ያወራሉ። አንዳንዴም ይዋሻሉ።
3. እኔ እንደዚህ ነኝ፣ አንቺስ በማለት በአንድ ጊዜ ትውውቅ ብዙ ለማወቅ ይሻሉ።
4. አንዳንዶቹ የሚያወሩትን አያውቁም። የባጡን የቆጡን ሲያወሩ ዝግት ያደርጋል።
5. አንድ ወንድ ቀርቦ ሲያናግረኝ ካልፈለግሁት በቀጥታ መንገድ "አልፈልግም" ማለቱ ስሜቱን ይነካል በሚል በተዘዋዋሪ መንገድ አለመፈለጌን ስገልፅ የማይገባው ሰው ምን ትሉታላችሁ?
6. አንዳንዶቹ አለመፈለጋቸው ሲገለፅላቸው እልህ ይይዛቸዋል መሰለኝ ድርቅ ይላሉ። ያልሆነ ያልሆነ ነገር መናገር ይጀምሩና ጠብ ለመጫርም የሚከጅላቸው አጋጥመውኛል።
7. አንዳንዶች ጉረኞች ናቸው። ራሳቸውን ከበው ነው የሚወሩት።
8. በተለይ በምሽት ዝግጅት ቦታ፤ ከማን ጋር ልሁን ማረጋገጥ እኮ የለም። ዘሎ መጥቶ ብቻ "ተነሺ እንጫወት" ይልና ተነስቼ ስለተጫወትኩ ብቻ የፈቀድኩት መስሎት የባጡን የቆጡን ስለራሱ የሚያወራ ያናድደኛል።

ይህ ብቻ አይደለም። ብዙ የሚያስገርሙ ሁኔታዎች አሉ። ሴቶቸች ብዙ ገጠመኞቻቸውን ቢነግሩን ልንማማር እንችላለን። ብዙውን ጊዜ 'ይኸ መንገድ ጥሩ ነው' 'ይኸ አይሠራም' ብሎ ለመወሰን ያስቸግራል። እንደሰው ባህሪ የተለያየ አቀራረብ አለ። አንዷን ደስ የሚላት ሌላዋን ዝግት ሊያደርጋት ይችላል። ይህ ነው ችግሩ። ታዲያ ሴቶች እህቶቸቻችን ምን ትመክራላችሁ?

በሚቀጥለው ጊዜ በሰፊው ይዤ እቀርባለሁ።

---

### · · · ምን ትመክሩኛላችሁ ?

(ከገጽ 28 የዞረ)

እንደ አማራጭ የቀረበልኝ ደግሞ እዚህ አገር ለረዥም ጊዜ ቆይቶ ከተቻለ ዜጋ የሆነ ካልሆነም የመኖሪያ ፈቃድ (Green Card) ያለው ሰው ማግባት ነው። ይኼኛው ትንሽ ከበደኝ። ከአክስቴ ልጅ ጋር የሚወጣ አንዱ ነበር ይህን የመከረኝ። ዝግጁ የሆነ ሰው (ጓደኛው) እንዳለ ደግሞ የአክስቴ ልጅ ነገረችኝ።

"አላውቀው፣ አያውቀኝ፣ እንዴት ብዬ አገባዋለሁ?" አልኳት የአክስቴን ልጅ።

"የግድ አብረሽው ትኖሪያለሽ ማለት እኮ አይደለም።" አለችኝ።

"ምን ዓይነት ጋብቻ ነውሱ? ባሌ ከሆነ አብሬው መኖር ያለብኝ መሰለኝ?" ብዬ ጠየቅኋት። ከልቤ ነበር።


"አየሽ፤ እሱ ሚስቴ ናት ብሎ ይፈርምልሽና ከፈለግሽ ቤቱ፣ ካልፈለግሽም እዚሁ እኔ ጋ ልትኖሪ ትችያለሽ፤ ብታገቢውና ቤቱ ብትኖሪስ ምን ወጣው ሸበላ ልጅ ነው። ጥሩ ገንዘብ አለው።"

ግራ ገባኝ። "የሚፈለገው ባል ነው ወይስ የሥራ ፈቃድ?" አልኩኝ በሆዴ። "ባል ለማግባት እንኳ አሁን አልፈልግም ይልቅስ ለስደተኝነት ባመለከት አይሻልም?" አልኳት እያስተዛዘንኩ።

"ምርጫው የራስሽ ነው። በስደተኝነት አመልክተሽ ላይቀበሉሽ ይችላሉ። ካልተቀበሉሽ ደግሞ ወዲያው አገር እንድትለቂ ይወስኑብሻል። የሚፈቅዱልሽም ከሆነ ቆይተው ነው፤ ጊዜ ይፈጃል። በባል ከሆነ ጊዜ አይፈጅም። በተለይ ደግሞ እሱ የአሜሪካን ዜጋ ስለሆነ ቶሎ ነው የሚያልቅለት። ለዚህ ብዬ ነው እንጂ የማትፈልጊውን ጋብቻ እንድትፈጽሚ ፈልጌ አይደለም።" አለችኝ።

ሥራውም የመያዝ ሆነ ባል የማግባት ጉዳይ፤ የአክስቴ ልጅ የሠጠችን ምክር አለመቀበሌም ይሁን ብቻ ሌላም ሌላም ተጨምሮ የአክስቴ ልጅ ትንሽ ከበፊቱ መለወጧ ይሰማኝ ጀመር። ወድጄ አይደለም? ምንም ውሳኔ መውሰድ አልቻልኩም። እስቤ ከአገሬ የመጣሁት ሌላ፣ የገጠመኝ ሌላ። ምን ተሻለኝ? ያለሁበትን ችግር እንዴት ልወጣው? ምን ትመክሩኛላቸችሁ? ካለኝ ምርጫዎች የቱን ላድርግ?

? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ?




# ጓደኛ ለሚፈልጉ

ጓደኛ ፈላጊዎች ራሳቸውን አስተዋውቀው፣ ሊተዋወቁ የሚፈልጉትን ሰው ዓይነት የሚጠቁሙበት አምድ ነው። ስምና ትክክለኛ አድራሻ በመጽሔቱ ላይ አይወጣም። በስምና አድራሻ ፋንታ የኮድ ቁጥር ይወጣል። የኮዱን ቁጥር የምንሰጠው እኛ ነን። በስምና አድራሻ ምትክ የኮዱ ቁጥር ይወጣል። ስምና አድራሻ እኛ ጋ በምስጢር ይቆያል። ትክክለኛ ስምና አድራሻ ግን እኛ ጋ መድረስ አለበት።በጣም አጠር ተደርጐ ቢጻፍ ዕድሉን ለብዙ ሰው ማዳረስ ይቻላል።

ለመተዋወቅ የምትፈልጉት ሰው ዓይነት ወጥቶ ካገኛችሁ ቁጥሩን በመጥቀስ ደብዳቤ ጽፋችሁለት/ጽፋችሁላት አነስ ያለ ኤንቨሎፕ ውስጥ አሽጋችሁ ኤንቨሎፑ ላይ የናንተን ሙሉ አድራሻ በቀለም፣ የሚላክለትን/የሚላክላትን ሰው ኮድ ቁጥር በእርሳስ ጥጉ ላይ ጽፋችሁ በሌላ ከፍ ባለ ኤንቨሎፕ ውስጥ ከታችሁ አሽጋችሁ በአድራሻችን ትልካላችሁ። እኛም የኛን ፖስታ በመክፈት ከውስጥ ያለውን ኤንቨሎፕ እውጥተን የኮድ ቁጥር የተጠቀሰውን ግለሰብ ትክክለኛ አድራሻ ከመዝገባችን ኤንቬሎፑ ላይ በመሙላት እንልካለን። ከዚያ በኋላ እንደፍጥርጥራችሁ።

## የሚከተሉትን መመሪያዎች በደምብ አጢኑ።

1ኛ. ለፖስታና ለአገልግሎት አከፋፈሉ በሚቀጥለው ዓይነት ይሆናል፤
ከአሜሪካ - $5.00 (በmoney order)
ከካናዳና አውሮፓ - $6.00 (በአሜሪካ ገንዘብ፣ money order)
ከኢትዮጵያ - ምንም አይከፈልም።
ለ"ላንዳፍታ ቋሚ ደምበኞች (subscribers)
(ላንዳፍታ ማዘዣ ቅጽ ሞልታችሁ ከፍያ የላካችሁ) $4.00 ብቻ ነው።
2ኛ. ዕድሜአቸው ከ18 በታች ለሆኑ ይህ አገልግሎት አይሰጥም።
3ኛ. ይህ አምድ ዓላማው መተዋወቂያ መድረክ ለመፍጠር ብቻ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።
4ኛ. እባካችሁ እንዲጻፍላችሁ የምትፈልጉትን ነገር አሳጥሩት።
5ኛ. በመጀመሪያ የብዕር ጓደኝነትን በማጠንከር የበለጠ መተዋወቅን እንመክራለን።

## አዲሱ አድራሻችን፤

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

---

## ከአንድ አንባቢ የተሰጠ አስተያየት፤

የቀድሞው አኩሪ ባህላችን ወጣት ወንዶችና ሴቶች ተገናኝተው የሚተዋወቁበት መድረክ በየብሔረሰቡ ባህል አዘጋጅቷል። የአሁኑ የተበረዘ ባህላችን ደግሞ በዘመናዊነት (ምዕራባዊ)ና በኢትዮጵያዊ ይሉኝታና ዓይን አፋርነት መሐል ተንጠልጥሎ ከሁለት የወደቀ ዛፍ ሁነናል። እንደ ነጮቹ በየመዝናኛው ሥፍራ መገናኘትና መተዋወቅ ያስቸግራል። በጉዞ ላይ፣ በመሥሪያ ቤት፤ በት. ቤትና በሰፈር አካባቢ ባጋጣሚ ከመገናኘት ውጪ ሌላ አማራጭ የለንም። "ላንዳፍታ" ጥንቃቄ በተመላበት ዘዴ (አድራሻችንና ስማችንን ሳያጋልጣ) ጓደኞቻችን እንዲገናኙ መድረክ በመክፈቱ ከማድነቄም ሌላ አመሰግናለሁ። ታዲያ በዚህ በኩል ግኑኝነት በማድረግ የሰመረላችሁ (እኔም ልሆን እችላለሁ) "ላንዳፍታ"ችንን ለማሳደግ ምን አሰበናል ወይስ ጓደኛችንን እንዳገኘን ዝም እንላለን?

---

# ጓደኛ የሚፈልጉ ሴቶች

---

ስም 1043፤ ዕድሜ 23፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ ሃይማኖት ፕሮቴስታንት፤ ሥራ ሴክሪተሪ፤ መጽሐፍ ማንበብ፣ መዝሙር መስማት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት፣ እግዚአብሔርን ማገልገል እወዳለሁ። አልጠጣም አላጨስም። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፤– አማኝ የሆነ፤ የማይጠጣ፤ የማያጨስ፤ ሚስቱን ቤቱን ልጆቹን የሚወድ። ባሌ ሆኖልኝ እስከሞት የማልለየው። (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

---

ስም 1044፤ ዕድሜ 20፤ መኖርያ ጅማ፤ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቅሁ ወደፊት መማር የምፈልግ፤ መጽሐፍ ማንበብ፣ አገር መጐብኘት፣ ሙዚቃና ቲያትር እወዳለሁ። በብዕር ጓደኝነት ከእኔ ጋር መተዋወቅ የሚፈልግ ወንድ ወይም ሴት እፈልጋለሁ። (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

---

ስም 1045፤ ዕድሜ 20፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ ሙዚቃ ቲያትርና እስፖርት እወዳለሁ። የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታዬን በማሻሻል ላይ ነኝ። ቁመቱ ረዘም ያለ፣ እምነቱ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን፣ ዕድሜው ከ22 እስከ 30 የሆነ፣ በሃብት የማያምን ወንድ መተዋወቅ እፈልጋለሁ።(በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

---

# ጓደኛ የሚፈልጉ ወንዶች

---

ስም 1046፤ ዕድሜ 34፤ መኖርያ ዩናይትድ ስቴትስ፤ ዩኒቨርስቲ ጨርሻለሁ። እሰራለሁ አላገባሁም። ከሰዎች ጋር መወያየትና አንዳንዴ ሙዚቃ ማዳመጥን እወዳለሁ። መተዋወቅ የምፈልጋት ሴት የማታጨስ፣ ልጅ የሌላት፣ ትምህርት በመጠኑም ቢሆን ያላት፣ ዕድሜዋ ከ24 እስከ 32፣ አሜሪካ፣ አውሮፓ ወይም ኢትዮጲያ የምትኖር፤ ጥሩ ጠባይ ያላት፤ ሲያይዋት የማታስከፋ፤ ለዘላቂ ትዳር።(በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ።)

---

ስም 1047፤ ዕድሜ 24፤ መኖርያ ዩናይትድ ስቴትስ፤ የኢትዮጲያዊና የመናዊ ድብልቅ፤ 12ኛን ኩዌት አጠናቅቄአለሁ። አልጠጣም አላጨስም። ሙዚቃና እስፖርት እወዳለሁ። እስልምና ሃይማኖት አጠብቃለሁ።ጥሩ ትዳር መመስረት እፈልጋለሁ። መተዋወቅ የምፈልጋት ሴት ዕድሜ ከ26 ያልበለጠች፣ የዘር በሽታ ያልተጸናወታት፣ በኢትዮጲያዊነትዋ የምትኮርና የሃገር ፍቅር ስሜት ያላት፤ ለዘላቂ ጓደኝነት።(በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ።)

---

ስም 1048፤ ዕድሜ 27፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ የመንግሥት ሰራተኛ፣ ፎተግራፍ ማንሳት፣ ኪነ ጥበብ እወዳለሁ። ግልጽና ተጫዋች ነኝ። በብዕር ጓደኝነት ወንድም ሆነ ሴት ለመተዋወቅ እፈልጋለሁ።(በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ።)

---

ስም 1049፤ ዕድሜ 28፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ ለሥራ ወደ ጅማ ተመላላሽ፤ የመንግሥት ሠራተኛ፤ ማንበብ፣ ፊልም ማየት፣ ሙዚቃ፣ ጠረጴዛ ኳስ እወዳለሁ። ልጅ የለኝም። መተዋወቅ የምፈልጋት ሴት ዕድሜ እስከ 25፣ ግልጽና ረጋ ያለች፣ የፍቅር ስሜትዋን የማትደብቅ፣ ጠይም፣ አጭር ያልሆነ ጸጉር፣ ከጥሩ ቁመና ጋር፣ ሥራ ያላት፣ ወጣ ብላ መዝናናት የምትወድ፣ ልጅ የሌላት ቋሚ ፍቅረኛ እፈልጋለሁ።(በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ።)

---

ስም 1050፤ ዕድሜ 22፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ 2ኛ ዓመት ዩኒቨርሲቲ፤ መጽሐፍ ማንበብ፣ ሙዚቃና ቲያትር ወዳለሁ። ማንኛውንም ሱስ የሚያስይዝ ነገር እጠላለሁ። በብዕር ጓደኝነት ዕድሜዋ ከ35 ያልበለጠ ክርስትያን የሆነች ሴት መተዋወቅ እፈልጋለሁ። (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ።)

---



# የአበው ቅርስ



ይህ አምድ በአማርኛ የተደረሱ ቅኔዎችን፣ ተረትና ምሳሌዎችን፤ ፈሊጦችን፤ የዘፈን ግጥሞችን፤ እንቆቅልሾችን፤ እንካ ሰላንቲያዎችንና የመሳሰሉትን፤ በተለይም ከአባቶቻችንና ከእናቶቻችን የወረስናቸውን፣ እንዳይረሱ የምንዘጋብበት፣ የተረሱንን እንድናስታውሳቸው የሚረዳን መድረክ ነው። አንባብያን በየመዘክሮቻችሁ ያከማቻችሁዋቸውን ቅርሶች በመላክ እንድትተባበሩን እንጠይቃለን። ከአገር ርቀን ላለን ባህላችንን ጠብቀን የምናስከብርበት፣ አባት እናቶቻችንን የምናስታውስበት፣ የቋንቋቸችንን ምጥቀት እየተረዳን የምንኮራበት ነውና። ቀደም ላሉት እትሞች፤ ለዚህኛውም አስተዋጽዖ ላደረጋችሁ ሁሉ በአንባብያን ስም ምስጋናችንን እናቀርባለን።

---

ይድረስ ተወዳጅ ለሆናችሁት ለላንዳፍታ መጽሔት አዘጋጆች፤ የሀገር ሰላም የሕይወት ጤና እንዲያድላችሁ ጥልቅ የሆነ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ። ፪ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ጥር ላይ የወጣውን ላንዳፍታ መጽሔት አግኝቼ ጠለቅ ብዬ ተመልክቼ ሳነብ በገጽ 7 እመጨረሻው መስመር ላይ የተፃፈውን ስለአየሁ መለስ ብዬ ሽፋኑ ጀርባ ፎቶ ላይ አይኔን ጣል አድርጌ ሳተኩር ትዝ ያለኝ ፈጣሪአችን እየሱስ ክርስቶስ አላዛርን ከመቃብር ያስነሳውን በማስታወስ ወደመጽሔቱ ጉዳይ ተመልሼ ውስጠ ወይራ የሆኑ ከታላቁ አያቴ የሰማሁዋቸውን ተረቶች ከዚህ ጋር ስለላኩላችሁ በድርጅታችሁ በላንዳፍታ መጽሔት ላይ እንድታሰፍሩልኝ በትሕትና እያአቀረብኩላችሁ በላንዳፍታ መጽሔት ላይ ያለኝ ፍቅር የማያቋርጥ ነው።

## ው ስ ጠ ወ ይ ራ

፩. ሰውዬው ወደለቅሶ ቤት ሲሄድ አንድ ሰው እመንገድ ላይ አገኘውና "ወዴት ትሄዳለህ?" ብሎ ቢጠይቀው "አቶ እገሌ በእሳት ተቃጥሎ ሞተ ብለውኝ ወደለቅሶ እሄዳለሁ፤" ቢለው ጠያቂው የሞተውን ሰው ያውቀው ኖሮ "እዩ ጉድ ክፉ ሕልም አይቼበት ነበር እንኳን በዚህ አለፈለት፤" አለ ይባላል።

፪. አንድ ገበሬ ስንዴ ዘርቶ ከበቀለለትና እሸት ከሆነ በኋላ አንበጣ ስለበላበት ኡኡኡ ብሎ ሲጮህ ጩኸቱን የሰሙ ጎረቤቶች ደርሰው "ምን ሆነህ ነው የምትጮኸው?" ቢሉት "የዘራሁትን ስንዴዬን አንበጣ መጥቶ በላብኝ፤" ቢል ታድያ "ምን ያስጮህሃል፣ የአንበጣ አፍ ለምለም ነው ይተካል፤" ቢሉት "እኔ ስንዴዬ የተበላብኝ ተጎዳሁ እንጂ የኔን ስንዴ የበላው አንበጣ አፍማ ምነው አይለምልም፤" አለ ይባላል።

፫. አይጥ እናት አባቷ ተከዘው ስላየች "እናቴ ዛሬ አንድ የሚያስደስት ወሬ ሰምቼ መጣሁ" ብትል "ምን የሚያስደስት ወሬ ሰማሽ?" ብትላት "በድመት አፍንጫ ላይ ተጉዞ የሚሸመትበት አገር አለ አሉ" ብትላት እናቷ "ቀድሞ ቤት ታልፎ ነው እዚያ የሚደረሰው" አለች ይባላል።

ከሻለቃ ጌታነህ ደምሴ (ናዝሬት)

********

## ከአማርኛ ቅኔዎች

የሚከተሉትን ቅኔዎች የላኩልን አቶ ኃይለማርያም ከበደ (ከጂማ) ናቸው።

፩ኛ.
እንጨቱን ለቃቅን ታላቀረብንላት፣
ቤቱን አፈራርሳ የምታነደው ናት።

፪ኛ.
ሱሪዬን አንጥፌ ልተኛ ደጅሽ፣
ቤትእንዳልገባ አንቺምንት የለሽ።

፫ኛ.
ሴቲቱ ትግያ ምንኛ ለመደች፤
ይሳቅበት ብላ ወንዱን ጥላኝ ሄደች።

■ ■ ■ ■

## ተረትና ምሳሌዎች

(የሠራህወርቅ ናችው የላኩልን)

1. ለብልህ አይነግሩም ለአንበሣ አይመትሩም።
2. ሥጋ ቁጠር ቢሉት ጣፍያ አንድ አለ።
3. ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ።
4. በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ።
5. እንኳንስ ዘንባብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ።
6. አካሄዱን አይተው ጭብጦውን ቀሙት።
7. ትለብሰው የላት ትከናነበው አማራት።
8. ባለቤቱን ካልናቁ ውሻውን አይመቱ።
9. ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው።
10.አላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል።

■ ■ ■ ■

## ሦስት ነገሮች፤

ከኃይለማርያም ከበደ (ጂማ)

ሦስት ነገሮችን ውደድ፤
እምነት፣ ግልፅነትና እውነት

ሦስት ነገሮችን ጠብቅ፤ አክብር፤
ቃልኪዳንን፣ ጓደኝነትንና ፍቅርን

ሦስት ነገሮችን ተቆጣጠር፤
ቃላቶችህን፣ ጸባይህንና አመልህን

ሦስት ነገሮችን ለአዕምሮ አስገዛ፤
ምላስህን፣ ቁጡነትህንና ድርጊትህን

ሦስት ነገሮችን ጠብቅ፤
ሀገርን፣ ቤተሰብህንና ዓይንህን

ሦስት ነገሮችን አድንቅ፤
ፍላጐትን፣ ውበትንና ሙዚቃን

ለሦስት ነገሮች ተዘጋጅ፤
ለሃላፊነት፣ ለዕውቀትና ለትዳር

ከሦስት ነገሮች ለመቆጠብ ሞክር፤
ከሌብነት፣ ከሥራ ፈትነትና ገንዘብ ከማባከን

ሦስትን ለማግኘት ታገል፤
ጤንነት፣ ዕውቀትንና መወደድን

በመጨረሻም ሦስቱን በሥራ ተርጉማቸው፤
ዕውቀትህን፣ ጉልበትህንና ገንዘብህን።

## "የ ዘ ፈ ን ግ ጥ ም"

ከጉበዜ ረታ (ዳላስ–ቴክሳስ)

አብረዋት ሲተኙ ስንዝር የምትርቀው፣
ጡቷ እንደጐጥ መሪ ዞሮ የሚጨበጠው፣

አይኗ ቃታ ገብቶ ጀግና አባራሪ ነው፣
ጥርሷ ፋና ሆኖ ግብር አስገቢ ነው።

ከናድና እጅጌ እንዝርትና ጣት፣
ቀጭን ትፈትላለች እንደሸረሪት፣

ቀጭን መፍተያዋ እንዝርቷ ሰባት፣
ሲያጉረመርም ያድራል ደጋንዋ ለሊት፣

ነጭ ትጋግራለች ለጌቶች እራት፣
ነጭ መጋገሪዋ ምጣድዋ ሙኒት፣

የፊቷ ፀደላ በወርቅ የቀቡት፣
የሴት ወርቀባሽ ተኩላ የማትሰት።

እንበሳውን ገድላ ፀጉሩን ጉዝጉዛለች፣
የእባብ ገመድ ታጥቃ ዘንዶ አገልድማለች፣
ደጅ አጋፋሪዋን ነብር አቁማለች።

ምንም ጀግና ቢባል ወይም አስማተኛ፣
በሞቱ ቆርጦ ነው ከእርሷ የሚተኛ።

## ታ ላ ላ ቅ ጥ ቅ ሶ ች

ከመጽሐፈ ምሳሌ የተወሰዱ

"እናንት ልጆች፣ የአባትን ተግሣጽ ስሙ፤ ማስተዋልንም ታውቁ ዘንድ አድምጡ።"

"ተግሣጽን የሚወድ ዕውቀትን ይወዳል፤ ዘለፋን የሚጠላ ግን ደንቆሮ ነው።"

"የለዘበች መልስ ቁጣን ታበርዳለች፤ ሸካራ ቃል ግን ቁጣን ታስነሳለች።"

# « ግ ጥ ም ከ ተ ባ ለ »

ከግርማ ዘገየ ይግለጡ (ቺካጐ)

ባለፈው የ"ላንዳፍታ" አንደኛ ዓመት ቁጥር 3 ሐምሌ 1984 ዕትም ላይ "ግጥም ከተባለ" በሚል ርዕስ ያቀረብኩትን ጽሁፍ አለማጠቃለሌና ግዜ ሲፈቅድ እንደምመለስበት በገለፅኩት መሠረት እነሆ በዚሁ ርዕስ ላይ አጠር ያለ ማሠሪያ ማቅረብ እፈልጋለሁ።

ግጥም መቼና እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ የሚገልፁ የታሪክ መጻሕፍት ባይገኙም የሰው ልጅ እንደወፍ በጩኸት፣ እንደዱዳ በምልክት ከመግባባት አልፎ ለሚጠቀምባቸው ቁሳቁሶችና ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች ስያሜ መስጠት ሲጀምርና ይህም የቋንቋ ፈጠራ የመጀመሪያ ረድፍ ሲጠቃለልለ በቋንቋ ዕድገት ውስጥ መራቀቅና መግባቢያ ሲዳብር የተፈጠረ የብስለት መለኪያና የቋንቋ ውበት መፈጠሪያ ይመስለኛል።

እንግዲህ ግጥም በቋንቋ ውስጥ ለዜማ፣ ለፍቅር፣ ለዓላማ፣ ለምኞትና ፍላጐት ለመግለጫ የሰው ልጅ መጠቀም እንደጀመረ ብንረዳም በቅድሚያ ግን በአብዛኛው የእምነት መፈፀሚያ ሥፍራዎች ፈጣሪን ለማመስገን መዘምራን ከጥንት ጀምሮ ይጠቀሙበት እንደነበር ብዙ የታሪክ መፃህፍት ይጠቁማሉ።

ግጥም መፃፍ እንዳሁኑ ባልደረጀበት፣ የተለያየ ቅርፅና "የቤት አመታት" ስልት ከመያዙ በፊት በአብዛኛው ግጥም የሚፃፈው ቤት ባይመታም መልዕክትን ብቻ አስመስሎ ለማስተላለፍ ነበር።

ሸራ ጫማ ያረገ አይባልም ደሃ፣
እንግዲህ ጀመረች እግር እግሬን ልታይ፣
የእህያ ውርንጫ ተረከዘ ሎሚ፣
እሾህ እንዳይወጋሽ ቀስ ብለሽ ሂጂ።

ይሄ እንግዲህ ቤት የማይመታ ግጥም ሲሆን ገጣሚዎቹ እንደሚመስላቸውና ሌላውን እያሣሣቀ በሚገባው መንገድ ያቀረቡት ነው። ቀስ በቀስ ቋንቋ እየዳበረ ሲሄድ ብዙ ጸሐፍት ጽሁፋቸውን በግጥም ማቅረብ እያዳበሩ መምጣትና እንዲያውም "ከዝርዝር ንባብ" ይልቅ በግጥም መልክ ማቅረቡ አድማጭ እያገኘ በመሄዱ ግጥም ከፍተኛ ዕድገት በማግኘት በቋንቋ ሕይወት ውስጥ "ሰምና ወርቅ" የተባለውን ባለሁለት ገፅታ ትርጉም እየያዘ መምጣት ከመጀመር አልፎ በሁሉም ሥፍራ ራዋቂ ሆነ። ለምሳሌ:-

ለዳኛ ሣይነግሩ ምስክር ሣይቆጥሩ፣
ሠሜንተኞች ከብቴን ቀምተውኝ ቀሩ።
ይሄ ደረትሽ ነው ያጣላኝ እኔኔ፣
እስቲ ሸፈን አርጊው ያጡት እንደሆን።

እንግዲህ በአጭሩ ከላይ ለማሣየት የሞከርኩት በግጥም ሕይወት ውስጥ "ሰምና ወርቅ" የተባለው የአፃፃፍና የአተረጓጐም ስልት ሁለት ነገሮችን በአንድ ግዜ እንዴት ማስተላለፍ እንደምንችል ለመግለጽ ነው። "ሰምና ወርቅ" በአብዛኛው ጥቅም ላይ ሲውል የምናየው የውስጥ ብሶትን ፊት ለፊት መናገር ከሚያመጣው ጥቃት ለመዳን ሲባልና አለመናገር ደግሞ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም በመገመት "ውስጠ ወይራ" አድርጐ ማቅረቡ ሲታመንበት ነው። እስቲ ከዚሁ ሳልርቅ በደል የበዛበትን የጥንት ጭሰኛ በደሉን በአደባባይ ለመግለፅ የተጠቀመበትን የግጥም ስልት ለእማኝነት ልጥቀስ።

እህሉን ወሰዱት ሁሉንም አፍሠው፣
ሙክቴንም ሳቡት ዘበኛ አቁመው፣
ንጉሥ የተረፈኝ ጥቂት አማርኛ፣
ሆዴንም ውሰዱት አርፌ እንደተኛ።

ከሰምና ወርቅ የግጥም ሥልት ቀጥሎ ግጥም በዕድገት ደረጃው በአነጋገር ብቻ ሳይሆን በአፃፃፍም ዘመናዊ ስልት እየያዘ በመምጣት ያለንበት ዘመን ፀሃፍት ግጥምን በአፃፃፍና በገላጭነቱ ጥልቅ እንዲሆን አድርገውታል።

በሃገራችን ካሉት እውቅ ፀሃፍት አንዱ አበራ ለማ ዓመታት ካስቆጠረ ግጥማቸው ውስጥ አንዱን እንደምሳሌ ላቅርብ።

ያ መረቡ ልቤ
    ረገበ እንቢ አለ
አንድ ራሱን ማስገር
    አቃተው ዋለለ።
ፍርሃቴ ስጋቴ
    በላዬ ነገሠ
ውስጥ አንጀቴን ምሶ
    ቤቴን አጣረሠ።
ግና ምነው ፈራሁ
    ወኔዬ ባዘቀ
በፍርሃት ነቅዤ
    ነፍሴ ተጨነቀ።
እድሜ እንደብል ሆኖ
    ሕይወት ካነተበ
ፍርሃት ንጉሥ ሆኖ
   አገር ካስደመመ
እናንተም እንደኔው
    ፍርሃት ካበጃችሁ
ጠበንጃው ሣንጥለው
    ውሻው ለምናችሁ።

በዚህ የአበራ ለማ ግጥም ውስጥ ብዙ ነገር ታያላችሁ። ውስጠ ወይራነት ያላቸው መልዕክቶች፣ የዘርፍ አቀማመጥና ጥልቅ የሆኑ ገላጭ ቃላቶችን ትመለከታላችሁ። ለምሣሌ ያሀል ዋለለ፣ ማስገር፣ አጣረሠ፣ ባዘቀ፣ ካነተበ፣ ካስደመመ፣ ካባጃቸው የሚሉት ቃላቶችና አገላለጦች አንድ ፊደል ይሆኑ እንጂ በውስጣቸው ሰፊና ጥልቅ የሆኑ ወጊ ትርጉሞች ይዘዋል። የግጥም ነገር ከተነሣ አንድ ነገር ትዝ አለኝ። ወደ አዝማሪዎች ግጥም ተራ የገባችሁ እንደሆነ ለመግጠም ሲባል ብቻ የሚገርም የዘፈን ግጥም ትሰማላችሁ። እኔን ከሚገርሙኝ የአዝማሪዎች ግጥም ውስጥ ጥቂቱን ላቅርብ።

ከመንደር አዝማሪው ጀምሮ እስከመድረክ ድምፃዊ ዘፋኝ ድረስ በብዙ መረዎ ድምፃዊያን ተደጋግሞ የተገጠመ ከሠርግ ቤት አንስቶ እስከ አደባባይ የእስክስታ ወራጆች ትክሻ ያንዘፈዘፈ "አሞራ በሠማይ ሲያይሽ ዋለ" የሚለው ዘፈን የማያውቅ እንደሌለ እርግጠኛ ነኝ። እንኳን በዕድሜ ገፋ ያሉት አፋቸውን በደንብ ያልፈቱ ሕፃናት ሲያዜሙት ትሰማላችሁ።

እስቲ ግጥሙን መርምሩ:-

አሞራ በሠማይ ሲያይሽ ዋለ፣
የገሌ ነሽ እያለ፣
አሞራ በሠማይ ሲያይሽ ዋለ
አሽ... ሲያይሽ ዋለ አሽ...

እንግዲህ ይሄ "ቢስ" ወይም "ይደገምልን" እየተባለ የሚዘፈን ዘፈን ነው። ዜማና ግጥሙ የሁሉንም የመወዛወዝ ፍላጐት በመሣቡ ረገድ ድንቅ ነው። እኔም አንድ ሁለቴ ትከሻዬን ፈትቼበታለሁ። ግን የግጥሙን ቁምነገር የመረመራችሁ እንደሆነ በመሠረቱ አሞራ ከሠማይ ላይ ሆኖ ቁልቁል ወደታች የሚያየው የወደቀ ጥንብ ወይም በአቅም ከእሱ የሚያንስ ትንሽ ፍጡር ሲሆን እሱንም ጠልፎ ለመሄድ ሲል ነው።

ግጥሙ በውስጠ ወይራነቱ ደግሞ አንዱ የከጀላትን ሲያንጃብብባት እንደሚውልና ሲያመቸው ለመጥለፍ ወደኋላ እንደማይል ያመለክታል። ግን ካልጠፉ ቃል አፍቃሪና ተፋቃሪን ከአሞራና ከጥንብ ጋር ማመሣሠል ትንሽ የከበደ መሠለኝ። ለግዜው ግን "አሞራ" በሚለው ፋንታ "አሞራው" የሚለውን ቢጠቀሙ ትንሽ የሚሻል መሰለኝ። ከጆፌው ይልቅ ድርጊቱን ያመለክታልና። በመሠረቱ ዘፈንም ሆነ ግጥም የሠሚውን ስሜት የሚኮረኩር ሃዘንና ደስታውን የሚዳስስለት፣ የውስጥ ብሶቱን የሚነግርለት፣ ለማለት የሚፈልገውን ዐቅም የሚፈጥርለትና ስለሱ የሚሠማውን የሚያንፀባርቅለት መሆን ያለበት ይመስለኛል። ታዲያ ይሄንን ሣስብ ዓላማ የሌለው፣ ለማን እንደቆመና ምን እንደሚያሰብ በውል የማታውቁት በጥሩ ዜማ የታጀበ ግጥም ስትሰሙ አይደንቃችሁም።

በቅርቡ ከመሸታ ቤት ወደአደባባይ ማሲንቆውን ይዞ ብቅ ያለ ጉብል ነው የሚጫወተው። እስቲ ግጥሙን ተመልከታችሁ ወይ እኔን ወይ እሱን ታዘቡ።

ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ ጠጪ፣
ሠክሮ ተወላግዶ በጣም ወልገድ ብሎ፣
ዓይኑን ፈጠጥ አርጐ እጁን ሰብሰብ አርጐ፣
ደረት ነፋ አድርጐ አድሮ ጠዋት ገብቶ።
ሚስቱንም ጨቅጭቆ፣
ደሞዟን ሳይከፍል ሠራተኛ አባሮ፣
ማረጋጋት /ማዘንጋት/ ይዞት ካላደረ ውጭ፣
መወለድ አይበለው ተጨነገፈ እንጂ።

ከዚህ ዘፈን የምንረዳው ነገር ቢኖር የስካርን ጻዲቅነት፣ የጨዋነትን ኩነኔነት ሲሆን የአዝማሪውን መመዘኛ የማያሟላ ወንድ ሁሉ ከጀግኖች እንደማይደመር አበክሮ ይመክራል። ለዚያውም በዚህ ብቻ አያባራም። ከመከርኩ አይቀር ሁለቱንም ፆታዎች መሆን አለበት በሚል ዓይነት ሴቶችንም ሲያነሣሣ:-

ሴቷም በበኩሏ ካልተባለች ሂያጅ፣
አምስቱን ስድስቱን ካላጋደመቺ፣
እንዲህ ባሏት ግዜ እንዲያ ካላለች፣
በጠሯትም ግዜ ከተፍ ካላለች፣
የሴቶች ስም አጥፊ መሆኗ ታውቆላት
ዳኛው ባስተያየት
መነጥር ዝቅ አርገው አዳር ፈረዱባት።

ምን የሚሉት ዘፈን ነው። አስተማሪ አይሉት አዝናኝ። ምናልባት ይህ አዝማሪ የዘወትር ስካር ሱስ የሆነባቸው ጠጪዎች መሃል ይህንን ገጥሞ ተጨብጭቦለት "ጉሽ እንዲህ ነው እንጂ" አሰኝቶ ከሆነ እዛው የዘነበበት መሸታ ቤት ማባራት ሲገባው ይህንን ይዞ አደባባይ መውጣት ምን ይሉታል? የሚገርመው ደግሞ በዘፈኑ በስተመጨረሻው የተናገረው መሻርያ ያደርግበት ይሆናል የሚል ግምት ነበረኝ። እንዲያውም ቃሉን እረገጥ እያረገ ሲጫወተው እሱን ብቻ ሳይሆን የራሴን ጆሮና የሣቅሁበትን ጥርሴን ታዘብኩት። እስቲ እኔው የገጠመኝን ላውራላችሁ። እምና የዘመን መለወጫ በዓል ለማክበር ኢትዮጲያውያን እንደተለመደው ከያሉበት በመጠራራት ምሽቱን በአንድ አዳራሽ ተሰባስቦ "ኢዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ" ለማለት ታድመዋል። እኔም አንዱ በመሆኔ ከበዓሉ ቦታ የደረስኩት ረፈድፈድ አድርጌ ወደእኩለ ለሊት ላይ ነው። ብዙም ጨዋታ አላመለጠኝ። እንዲያውም ደመቅመቅ ካለ በኋላ በመድረሴ ወድጄዋለሁ። ሴቶች የባህል ልብስና ጌጣቸውን አድርገው ሲወዛወዙ፤ አዛውንት በልጃቸው ታጅበው መድረኩ ላይ ሲውረገረጉ ማየቱ ራሱ በጣም ደስ ይላል። የተመቻቸ ወንበር ባላገኝም አንድ ጥግ ፈልጌ ቆም አልኩ። እኔ እስክሟሟቅ ሌላውን ማድነቅ ስላለብኝ በጭብጨባም በሆታም ለእስክስታ ወራጆች ድጋፌን መለገስ ጀመርኩ።

የዕለቱ ተጋባዥ አዝማሪ በግል ልጅነቱ ጀምሮ ባካበተው የማሲንቆ አመታት እጅግ ተከኖበታል። ለማሲንቆው ማዳመቂያ ከጐኑ በአነስተኛ ጠረቤዛ ላይ ያስቀመጠውን "ዘመናዊ የከበሮ ምት ቅንብር" ማጫወቻ መሣሪያ በፈለገው ዓይነት በሌባ ጣቱ ደንቆል እያረገ በማያልቅበት የግጥም ናዳ ይህንን ባህሉን የሚወድ ህዝብ ላብ በላብ አርጐታል። መቼም ድምፁ፣ እንጉርጉሮ፣ ቅለቱ፣ የግጥም አደራደር ለጉድ የሚያሠኝ ነው። ሙያ ብለው ከያዙት እንዲህ ነው እንጂ ያሠኛል። ታዲያ አንዳንዴ ግዜው ያለፈበትን ግጥም በዘፈኑ መሃል አስገብቶ ድንቅር ያደርገዋል። እንግዲህ የኔ ትዝብት የጀመረው ከዚህ ነው። ተከተሉኝ፤

ሣላወጣሽ ካልጋ
ንገሪኝ ዋጋ።

በአዳራሹ ውስጥ ያለው በሙሉ መቀበል ጀመረ ወንዱም ሴቱም "ንገሪኝ ዋጋ" እያለ። በዚህ ግዜ ለኔ የሚታየኝ አመንዝራና ዝሙተኛ ወይም "ሴተኛ አዳሪና "የወንድ ሿሪ" አልጋ አጠገብ ቆመው በአካል ሽያጭ ዋጋ ባለመስማማት ሲሟገቱ ታየኝና ፈገግ አሠኘኝ። ለነገሩ ጨዋታው እጅግ የቆየ በባህላችን በሠርግ፣ በበዓልና አልፎ አልፎም ቢሆን በአዘቦት የሚንጐረጐር ዘፈን ነው። ግን የሰው ልጅ በሥልጣኔ እያደገ ሲሄድና የግል ሚስጥሩንና አደባባይ የሚወጣውን ለይቶ ሲረዳ ማብቃት ያለበት መሠለኝ። "ሌላው ስለውጭው ሌላ ዓለም ሲመራመር እኛ በአንድ ፊት እርስ በእርስ ስንተላለቅ በሌላው ጐኑ "ንገሪኝ ዋጋ" ስንባባል አስተሣሠባችን ከጦር እድማውና ከአልጋ ያልራቀ እየመሠለኝ ያሣስበኛል። አሁንም ከአዳራሹ ስላልወጣሁ የምለውን አልጨረስኩም።

ጭብጨባውም ማድመቁም ቢሰለቸኝ ወንበር ፍለጋ ወደ መሃል አመራሁ። በአብዛኛው ሰው ለጨዋታው ስለተነሣ ብዙ መቀመጫዎች ባዶ ናቸው። ቀረብ ወዳለኝ አመራሁና አንድ በዕድሜ ገፋ ያሉ አዛውንት አጠገብ ተቀመጥኩ። "እንኳን አብሮ አደረሰን" አሉኝና ጨዋታ ጀመርን። ስም መለዋወጥ ወይም ትውውቅ አላስፈለገም። የሳቸው ጆሮ ግን አዝማሪው የሚያፈነቅላቸውን ግጥሞች ያደንቃሉ።

እስክስታ አወራረድ እኔ መች አውቅና፣
እንዘፈዘፈችኝ ሽንጧን ያዘችና።

አዳራሹ በሙሉ በጩኸትና በጭብጨባ ተደባለቀ። አዛውንቱም ድምፃቸውን ሁለቴ ላግ ላግ አረጉና ፍንትው ባለች ፈገግታቸው ወደኔ ዞረው ፍልቅልቅ ብለው ሳቁ። "ምን ጉደኛ ዘፋኝ ነው ጃል?" አሉኝ። ግጥሙ ከልብ እንዳስደሰታቸው ከሁኔታቸው ያስታውቃል። አቋማቸውን ከላይ እስከታች ተመለከትኩ። ተንዘፍዝፈው ለማንዘፍዘፍ ምንም የሚያንሳቸው ነገር የለም። በወጣትነት ዘመናቸው ደህና ጠላፊ መሆናቸው ዓይነ ግቡ መልካቸው ይመሠክራል።

ደህና ሲዝናኑ የነበሩት አዛውንት ድንገት ፈገግታቸው ጠፋና "ትሰማለህ ልጄ ደሞ ይሄ ምን የሚሉት ዘፈን ነው?" አሉኝ ተቆጥተው እኔ አልዘፈንኩ ታድያ ምን አስቆጣዎት ብዬ ልቀልድ ፈለኩና ቢያጮሉኝስ ብዬ "ምኑ?" አልኳቸው። "ያሁኑን ግጥም ሰማኸው አይደል?" ከማለታቸው ግጥሙ ተደገመ።

ማራዶናም ቢሆን ቁርበት አንጣፊ ነው፣
ሬገንም ቢሆን የፊልም ተዋናይ ነው፣
ክሊንተንም ቢሆን ሣክስፎን ነፊ ነው።
ግዜውም እንዳያልፍ በዋዛ ፈዛዛ፣
ሠላም እንዲመጣ እባካችሁ ሰዎች
ዘፋኞች እንግዛ።
ራሽያ ሣለሁ ... ተብያለሁ፣
ካናዳ ስዘፍን ... ተሹሜአለሁ፣
መንግሥቱ ሲጠፋ ጀኔራል ሆኛለሁ፣
መለሠ ሲደገም አገር እገዛለሁ።

"ቀጣፊ፣" አሉ አዛውንቱ ለኔ እንደሚሠማ አድርገው። "ምነው?" አልኳቸው። "አሁን ማን ይሙት ለቀጣፊና ለአዝማሪ እንደመንግሥቱና መለሠ የሚያከል መሪ ይገኛል። የጨዋ ልጅና አገሩን የሚወድ ሰው ፈጁ እንጂ፤ "አሉ በቁጭት ላቋርጣቸው አልፈለኩም። መስማት የምፈልገው ስላለ ብዙ እንዲያወሩልኝ ገፋፋኋቸው።

ዘፈኑን ትተን ብዙ አወጋን። በስተመጨረሻ ምን አሉኝ መሰላችሁ። " እኔ ይህንን አዝማሪ ብሆን በየወሩ ዚምባቡዌ እየሄድኩ መንግሥቱን አዝናና ነበር። ደግሞስ የሰው መሪ መዝለፍ ምን ይባላል?" አሉኝ በመገረም። ምን እያሉ ነበር መንግሥቱን የሚያዝናኑት?" አልኳቸው።ሣቅ አሉና

አይዞህ መንግዬ አይበልህ ከፋ፣
ሁሉም ወራጅ ነው በየወረፋ።

እያልኩ ነበራ የማጽናናው "የበሉበትን ወጭት መስበር፤" አሉና ፈገግ አሰኙኝ። የአዛውንቱን ማንነት በደንብ የተረዳሁት በሌላ ግዜ ተገናኝተን ባደረግነው ጭውውት ነበር። ተገፍተውና ተገፈው ካገራቸው ከወጡ 14 ዓመት ሆኗቸዋል። ስመጥር የቀድሞ ከፍተኛ የጦር መኮንን ናቸው። እሳቸው ገልፀው ባይነግሩኝም ታሪካቸውን በደንብ ከሚያውቅ ከተረዳሁ በኋላ ከልቤ አዘንኩ። እንደዚህ ባለው ጉዳይ ላይ ወደፊት አንድ ዝግጅት ስለሚኖረኝ አርዕስቴን ሣለቅ ወደተነሣሁበት ልቤን ልመልሣችሁ። የዜና ማሠራጫ ተቋም በመንግሥት ቁጥጥር ስር በሆነበት ዓለም ጋዜጠኞችና የኪነት ባለሙያዎች ያለውን የመንግሥት ፍላጐት ከማንፀባረቅና ከማወደስ ባሻገር አድርጉ የተባሉትን ወይም ይህን አዘጋጁ ሲባሉ ትዕዛዝን አክብረው ከመፈፀም ሌላ ብዙ አማራጭ የላቸውም። ለምን ቢባል ለመኖር ሲሉ መብላት ለመብላት ደግሞ መሥራት ስላለባቸው ሥራቸውን ላለማጣት በአድርባይነት ለመኖር ይገደዳሉ።

ታድያ ይህም ሆኖ ለቆሙበት ዓላማና የህዝብ ፍቅር አድልቶባቸው የሚያዩትን እኩይ ተግባር ባደባባይ አግልጠው ከሥራቸው የተፈናቀሉና ካገር የተሰደዱ ጋዜጠኞች ታይተዋል። ከኪነት ባለሙያዎችም ውስጥ ይህ ዕጣ የደረሳቸውና ከከባድ ማስጠንቀቂያ እስከቅጣት የደረሰባቸውም አሉ።

ለምሣሌ ያህል " አልቻልኩም፤ ችግርሽ በኔ አልፏል፣ ያ ጥቁር ግሥላ፣ ከእሣት ወደረመጥ፣ ሎሚ ተራ ተራ፣ አገሯ ዋርሣ መገና፣ እንቆቅልሽ፣ ወዘተ... የተሠኙት ዘፈኖች የተዘፈኑት ከገዢው መደብ ፍላጐት ውጭ በመሆኑ ዘፋኞቹ የሚመጣባቸውን ጥቃት ሁሉ ለመቋቋም ወስነው ነው ለህዝብ ያቀረቡት። ከእነዚህ ውስጥ ግማሾቹ ግልፅና ከፊሎቹ ደግሞ ውስጠ ወይራ ሆነው የህብረተሰቡን ስሜት የቀሰቀሱ ስለነበሩ አቅራቢዎቹ ምንግዜም አይረሱም። ታድያ ይህን ስንመለከት አንዳንድ አልኩ ባይና እበላ ባይ አዝማሪዎች ይደንቁኛል። ለዚህ ነው ዘፋኞችን በሁለት ከፍዬ እንድመለከት የምገደደው።

በኔ የግል ደረጃ ምደባ አዝማሪ የምላቸው ብዙም ከቀለሙ ሳይቀርቡ በገጠሬ ድምፃቸው ጭራ ወጥረው፣ ጅማት ገዝግዘው ከአፍ አይሉት ከአፍንጫ በሚወጣ ድምፃቸው ግጥም ይሁን እንጂ ለትርጉሙ ግድ የማይሰጣቸው፣ የአድማጭን ኪስ በዓይናቸው እየቃኙና ለሽልማት በመማፀን ዓይነት የአንገታቸው ደም ስር እስኪገታተር ድረስ ከጣራ በላይ እየጮሁ የሚዘፍኑና ለመኖርያ የምትሆን የዕለት ገቢ የሚሰበስቡበትናንና በመጠኑም ቢሆን መድረክ ላይ ለመውጣት የበቁትን ሲሆን ድምፃውያን /ከያኒ/ የምላቸው ደግሞ ከቀለሙ ዘረፍ፣ ከአቋቋማቸው ቀልጠፍ፣ በእንቅስቂሴአቸው ሸንቀጥ የሚሉትን ሙያው የጠራቸውና ለሙያው ተፈጥረው በሙያቸው የሚያድሩትን ነው። እንግዲህ ይህ የማንንም አስተያየት የማይጨምር የግል አስተያየቴ ነው። አይሆንም ሁለቱም አንድ ናቸው የምን መከፋፈል ነው የሚል ካለ "እሰጥ አገባ" ይሞግተኝ። በቂ ማስረጃ እያቀረብኩ ለመሟገት ዝግጁ ነኝ።

ስለግጥምና ገጣሚዎች፤ አዝማሪና ድምፃዊያን ብዙ የምለው ነበረኝ። እስቲ በቅርቡ አዝማሪና ድምፃዊያን መናኸሪያቸው ወዳደረጉት ወደ ዲሲ ብቅ ስለምል በጥቂት ቀኒት ቆይታዬ የታዘብኩትንና ያየሁትን ይዤ ሌላ ግዜ በሌላ ዝግጅት ልመለስበት እሞክራለሁ። እስከዚያ በቸር ያቆየን።

---

# የ ት ኛ ው ነ ው ጀ ግ ና

ከግርማ ዘገየ ይግለጡ

ሞፈር ቀንበር ጠምዶ...
ጅራፍ እርፍ አዋዶ፤
ድንግል መሬት ገምሶ
አፈር አለስልሶ፤
ዘር በትኖ አብቅሎ
አረም ሙጃ ነቅሎ፤
ደቦ ተጠራርቶ፣ አጭዶና ከምሮ
አንጡራ ጉልበቱን አንጠፍጥፎ ለፍቶ
ለራሱ ቆጥቦ
ለገበያ አቅርቦ
ህዝብን የመገበ ወገን የደጎመ
በውጭ ምንዛሪ አገር የጠቀመ፤
ይህን ጀግና ይሉታል?
ያሞጋግሱታል?
ይሸላልሙታል?
ወይስ ገፋ ገለል ሂድ ጥፋ ይሉታል?
ቀለም ውጦ ተፍቶ
ዕውቀት ጨምቆ በልቶ
በጥናት ሕንገቱን አቀርቅሮ ደፍቶ፤

እርሱና አገሩን በጋራ ሊጠቅም
ህዝብ ወገን ሊደጉም፤
ዕውቀቱን አደብሮ
ቁጥርን በቁጥር አጣፍቶ ደምሮ፤
የተማረን ወገን
    የነገ አገር ተገን
ጀግና ነው ይሉታል?
ያበረታቱታል?
    ወይስ እንዲጠፋ
ከዕውቀት ገበታ ያፈናቅሉታል?

ደዌ ያደረበትን
በሽታ ሠፍሮበት የሚጨነቀውን
አደጋ ደርሶበት እጅ እግሩን ያጣውን
የሚፈውስ ሃኪም የሚጠግን ዶክተር
ሌት ተቀን የሚጥር የሚቆም ለወገን
የሚሠራ ሳገር
ጀግና ነው ይሉታል?
ያመሠግኑታል?
ወይስ አስበርግገው ካገር ያጠፉታል?
    ወይስ እንደአውሬ
ከሠው እንዲወገድ
ድንበር ጥሶ እንዲሄድ መድረሻ ያሳጡታል?

ለሰው መብት የሚቆም
ሠላም እንዲሰፍን
ሞት ይብቃ ሞት ይሙት
ብሎ የሚጮኸውን
ሠላም ባገር ወርዶ

ሠቆቃና ጥፋት ፍርክስክሱ ወጥቶ
ከሥሩ ተንዶ
ወንድም እማችነት
ያገር ህዝብ አንድነት
አንድ የብረት አጥር
እንዲሆን የሚጥር
ለሚመጣው ጥቃት እንገቱን የሰጠ
ሠላም እንዲሰፍን ታጥቆ የሚታገል
በነፍሱ የቆረጠ
ጀግና ነው ይሉታል?
ያገር አድባር አውጋር
ትባርክህ ይሉታል?
ከጎኑ በመቆም ያበረታቱታል?
ወይስ በግልብጡ
የሱን ትግል ንቀው
ሠላም አጨልመው
ተግባረ ሠናዩን
ግብረ ቅዱስ ውኑን
እኩይ ነህ ይሉታል?
ኮንነው አዋርደው
ክብሩን ይገፉታል?

ያረሰ ገበሬ ወገን የመገበ
ዘር በትኖ ለቅሞ አገር ያጠገበ
የታመመ አድኖ
ለታመመ ታሞ ለቆሰለ ቆስሎ
ደዌ ላደረበት ለደረሰ ፈጥኖ
የቀለም ዘር ቆጥሮ
ከዕውቀት አብሮ
ነገ የዕውቀት ዛፍ
የቀለም ቅርንጫፍ
የሚሆን ተማሪ
አገር ወገን እኩሪ
ድምፁ ሠላም ጠሪ
ለሃቅ መስካሪ
ለመብት ተቆርቋሪ
የሰው መብት አክባሪ
ለአንድነት የሚቆም
ለፍቅር የሚታገል
የእውነት ምስክር
የሠብዓዊነት ሉል
እኒህ ሁሉ እንድላይ ጀግና ካልተሰኙ
በተገቢው መንገድ በህግ ካልተዳኙ
ስደት ከዘመቱ
ብኩን መና ሆነው ከተባሉ ከንቱ
የትኛው ነው ጀግና የትኛው ነው ጥኑ
የወገን ማዕዘን ያገር አድባር ዘንጉ
ዘመን ዘመን ሽሮት
እውነት ተገልብጦ
የሃቅ ቀለም ደርቆ
ከቦታው ተፍቆ
ጀግንነት ከሆነ አገር ማሸበር
ወገንን ማስጨነቅ
ወገን ማስቸገር
በህዝብ ጉሮሮ ላይ አፈሙዝ ደግኖ
አንድነት የሚል ቃል የሚያጠፋ አድኖ
ዘር ከዘር የሚያፋጭ
ሃይማኖት የሚያጋጭ

አሠሪና ሥራን በአዋጅ የሚለያይ
በሽምቅ ተዋግቶ በሽምቅ የሚያጋይ
ጦርነት ስደትን
ሠቆቃና ሞትን
በክብር የጋበዘ
የሚቃረነውን በእስራት ያጋዘ
ሽምቅ ዲሞክራሲን
ለይስሙላ ሰጥቶ
ሃቅ እውነትን ገድሎ
ያገር ታሪክ ወግቶ
ወግ ባህልን ነድሎ
ወገን ህዝብ በድሎ
በጠበንጃ ሥልጣን በጦርነት ምሎ
የተማረን ወገን በሳንጃ ዘልዝሎ
ባደባባይ ገድሎ
ይሄን ምን ይሉታል?
ከበሮ ደልቀው
ጀግንዬ አበባዬ
ጉሮ ወሸባዬ
ወየነ ጀግንዬ ይሉታል ሆ ብለው
እኔ በዚህ ዘመን የጀግና ትርጉሙ
ያገር አድባር ዘንጉ
የወንድ ልጅ ስሙ
መልስ እፈልጋለሁ ጠፍቶኛል የምለው
ወገኔ ንገረኝ ጀግናው የትኛው ነው?

??????????????????????????????


==============================


"ላንዳፍታ"ን

ማከፋፈል ለምትፈልጉ፤

የ"ላንዳፍታ"ን መጽሔት በየአካባቢያችሁ
በማከፋፈል ለመጽሔቷ ዕድገት አስተዋጽዖ ማድረግ
የምትፈልጉ በስልክ ቁጥር
(404) 728-9122 እነጋግሩን።
ለአከፋፋዮች ከ20 እስከ 25 በመቶ ኮሚሽን
እንከፍላለን።

==============================





# እ ስ ፓ ር ት




**ይህ አምድ የተከፈተው በኢትዮጲያውያን የሚካሄደውን የስፖርት እንቅስቃሴ ለማስተዋወቅና ለማበረታታት ነው። በየአካባቢያችሁ ስላለው እንቅስቃሴ፤ የውድድሮችን ውጤት ዘግባችሁ ላኩልን።**


ዘንድሮም እንዳለፈው ዓመት ዓመታዊው የሰሜን አሜሪካ የእግር ኳስ ጨዋታ ክብረ በዓል በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጲያውያን በተገኙበት በሳንፍራንሲስኮ ተካሂዷል። 15,000 ያህል ኢትዮጲያኖች ከዩናይትድ እስቴትና ከካናዳ ያሰባሰበው ይህ ታላቅ የእስፖርት ክብረ በዓል የተካሄደው ከJune 28 እስከ July 4 ድረስ ነበር። በዚህ ውድድር የሰንፍራንሲስኮው ዋሊያ ቡድን የአትላናታውን ቡድን በማሸነፍ የዓመቱ ሻምፒዮን ሆኗል። ብዙ ጊዜ አስተናጋጅ ሆኖ ለራስ መሆን ባይበጅም ችሎታችሁ ነውና ዋልያዎች እንኳን ደስ አላችሁ እንላችሁዋለን። በጣም ጥሩ ጨዋታና የቲም ሥራ ያለው የአትላንታው ቡድን በሁለተኛ ደረጃ ሲወጣ አሁን ስምንተኛው ጊዜ ነው። ጥሩ የእስፖርት አቋም፣ ፍቅርና ጠባይ የተካኑ የአትላንታ ቡድን አባላት ልምምድ በሚያደርጉበት በአትላንታ ፒድሞንት ፓርክ አንድ ሁለቴ በመገኘት ከግጥሚያው በፊት ለማየት ችለናል። የቡድኑ አቋምና ዲስፕሊን ለአሸናፊነት እንደሚያበቃው ገምግመን ነበር። በእስፖርት ዓለም መሸነፍም ማሸነፍም ያለ ነውና ሻምፒዮን ባለመሆናቸው ቅር ቢላቸውም በፀጋ የመቀበል የእስፖርት ባህርያቸው ደስ ያሰኛል።

ቡድኑ ሲጫወት ያየ ስለሱ ከማውራት አይመለስም። በዚህ ላይ ለስምንት ጊዜ የሁለተኛነት ማዕረግ የያዘ ቡድን አንዴ ብቻ አንደኛ ከወጣው ሳይሻል ይቀራል ብላችሁ? (ዋሊያዎች እንዳትቆጡ)። ስለሻምፒዮናው ብዙ ይወራል፤ ብዙም ተጽፏል፤ እኛ ደግሞ ስለሁለተኛው እናውራ። ከእስፖርተ ክለቡ ባገኘነው መረጃ መሠረት የአትላንታን ቡድን እናስተዋውቃችዋለን።የአትላንታ ስፖርት ክለብ በጥቂት ከፍተኛ የእስፖርት ፍቅር ባላቸው ግለሰቦች አነሳሽነት የሚገኙትን ወጣቶች ለማሰባሰብ በሚል አላማ በ1978ዓ.ም ተቋቋመ። ክለቡ እራሱን በማጠናከርና በአካባቢው የሚገኙትን ወጣቶች በማሰባሰብ ለአራት ዓመት ከቆየ በኋላ በ1982ዓ.ም በGeorgia Soccer Association ስር በአባልነት ተመዝግቦ በተለያዩ ውድድሮች እየተሳተፈ የክለቡን አቋም በበለጠ ማጠናከርና የአባላቶቹን ቁጥር ማብዛት ጀመረ። በአባላቶች መዋጮና በተጫዋችዎች ትብብር የአጭርና የረጅም ጉዞ በማድረግ እያሌ የወዳጅነት ጨዋታውችን ተካፍሎአል። በመጨረሻም የዚህ አገር አቀፍ የሆነውን የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጲያኖች ስፖርት ፌዴሬሽን መሠረት ለመጣል ጽንስ ሀሳቡን



የአትላንታው የእግር ኳስ ቡድን

ካቀረቡት ቡድን አንዱ እእንደነበረ ለማወቅ ተችሏል።የአትላንታ የኢትዮጲያኖች ስፖርት ክለብ እስከዛሬ ድረስ በተካፈላቸው ውድድሮች ከፍተኛ አጥጋቢና አስደሳች ውጤቶችን ተጐናፅፏል። ከነዚህም ለመጥቀስ ያህል ከሃያ እስከ ሃያ አራት የሰሜን አሜሪካ ቡድኖች ጋር አመታዊ ውድድሮችን በመካፈል ከ1985 እስከ 1993 2ኛ ደረጃን የያዘ ሲሆን ቡድኑ በጨዋታ ብቻ ምስጉን ሳይሆን የስፖርትን ጨዋነት ጠንቅቀው በሚያውቁ ተጫዋችዎች እና አባላቶች የተገነባ ነው። ይህ አቋመሙም ለክለቡ መልካም ስም ማግኘት ምክንያት ሆኖታል። በተመልካችም ዘንድ አድናቆትን ያገኘ ቡድን ነው። አሁንም ይህ ቡድን አትላንታ በሚገኙ ኢትዮጲያዊያኖች ሞራልና ድጋፍ የበለጠ ውጤት እንደሚጐናፀፍ ክለቡ ሙሉ ተስፋ አለው። የአትላንታ ስፖርት ክለብ እስካሁን ድረስ ባደረገው ዕድገት ተወስኖ ሳይቀር በበለጠ ተጠናክሮ ለተተኪው ወጣቶች የሚያኮራ ቅርስ ማውረስን እንደሚመኝ የእስፖርቱ ክለብ አባላት ገልጸውልናል።



የአትላንታው ቡድን በልምምድ ወቅት

# ከሳንፍራንሲስኮው ውድድር የምንማረው፤

ከአበራ ሲሳይ (ቺካጐ)

የሳንፍራንሲስኮው ዋሊያ እግር ኳስ ቡድን የአስረኛውን የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጲያውያን ውድድር የአትላንታውን ቡድን አሸንፎ የዋንጫው ባለቤት ሆኗል። በዋንጫው ጊዜ ከአስራ አምስት ሺ በላይ የሚቆጠሩ ኢትዮጲያውያን ነበሩበት። ባልሳሳትም ከመቼውም የበለጠ የተመልካች ቁጥር ነበር። በዚች ጽሑፍ ላይ ማተኮር የምፈልገው የጨዋታዎችን ጥራትና ድምቀት ሳይሆን አጠቃላይ ዝግጅቱ ይሆናል። የሳንፍራንሲስኮን ዥግጅት ከዚህ በፊት ከተዘጋጁባቸው ከተማዎች ጋር በማወዳደር፣ ለወደፊት ለፌዴሬሽኑና ለኢትዮጲያውያን ጥቅም የሚውሉበትን አስተያየቶች ለመስጠትና በፌዴሬሽኑ መካከል እየጎላ በመምጣት ላይ ስለአሉት ችግሮች ለመጠቆም ይሆናል። የፌዴሬሽኑ የመጀመሪያዎቹን አራት ዝግጅቶች ባለመስማቴና ባለማወቄ ስለአላየሁ እንዲሁም በሲያትል ላይ የተደረገውን ዝግጅት ባለማየቴ የምሰጠው አስተያየት አይኖርም።ለመጀመሪያ ግዜ በ1989 ዓ/ም (እ. ኤ. አ.)በቨርጂኒያ ከተማ ውስጥ የተካሄደውን ቀጥሎም በዳላስ፣ በቦስተን፣ በቶሮንቶና በሳንፍራንሲስኮ የተካሄዱትን በሚገባ በማየቴ አስተያየቴን ለአንባቢያን አቅርቤዋለሁ።ከምሰራበት ኩባንያ የዓመት እረፍቴን ስወስድ ብዙውን ጊዜ ከምኖርበት አካባቢ ሳልወጣ እንዲሁ በሆነው ባልሆነው አሳልፍ ነበር።

በቨርጂኒያ የተካሄደውን የእግር ኳስ ውድድር ስሰማ ማየት አለብኝ በሚል ከቺካጎ ቡድን ጋር ለማየት ሄድኩ። የቨርጂኒያ ዝግጅት ጣፍጦኝ ሳይሆን ለዘመናት ያላየኋቸው ጓደኞቼንና ዘመዶቼን በሕይወት በማግኘቴ፣ አዳዲስ ጓደኞችን ለማፍራት እንደምችል በማየቴ፣ በተለያየ ምክንያት ዳሽቆ የነበረውን የኢትዮጲያዊነት ስሜቴን እንደገና ማንሳት እንደምችል ተረዳሁ። ኢትዮጲያውያኖች ሙያተኛነታቸውን በማስመስከር ለገበያ ምግቡን፣ መጠጡን፣ ጨርቃጨርቁን ቡናውን ወዘተ ኳስ ሜዳው ውስጥ ዘርግተው ሲጠቀሙ በማየቴ እንዲያው በደፈናው ግርግሩና ግንኙነቱ ስለማረከኝ በየዓመቱ የእረፍት ጊዜዬን ለዚህ ዝግጅት ወሰንኩ። በየጊዜዉ የሰዉ ብዛት እየጨመረ በማየቴ ብዙ ኢትዮጲያዊያን እንደኔዉ የወሰኑ ይመስለኛል። ይህን አስደሳች ዝግጅት ያላያቸሁና ያልሰማቸሁ ለአንድ ሳምንት ኢትዮጲያ ደርሳችሁ እንደምትመጡ አድርጋችሁ በመቁጠር የዕረፍት ጊዜአችሁን እዚህ ብታሳልፉ የማይርሳና ልዩ ልምድ እንደምታገኙ አልጠራጠርም። ፌዴሬሽኑም ከተለያዩ አሉባልታዎች ወቀሳዎችና ፍጥቻዎች አልፎ ባአስራ አንደኛ ዓመት በመብቃቱም በጣም ያስመሰግነዋል። ለወደፊቱም ከማሻሻል ጋር እንዲጠነክሩ እመኝላቸዋለሁ። ምንም እንኳን ፌዴሬሽኑ እንዴት እንደተመሠረተ፣ በማን እንደተመሰረተ ባላውቅም ከዓመት ዓመት የተሳታፊው



የዓመቱ ሻምፒዮና የሳንፍራንሲስኮው ዋሊያ ቡድን

ብዛት እየጨመረ በመሄዱ እንደ እድገቱ የፌዴሬሽኑ አላማ እየሰፋና እያደገ ሄዶአል የሚል ግምት አለኝ። በአሁኑ ሰዓት ፌዴሬሽኑ በ24 ቡድኖች የተመሠረተ ነው። ከእያንዳንዱ ቡድን ጋር ወደዝግጅቱ የሚሄዱት ኢትዮጲያውያኖች ብዙ ናቸው። ከዚህም ከዚያም ተብሎ የሚሰባሰበውና ከአዘጋጅ ከተማ አካባቢው የሚኖረው ቢደማመር ከአስር እስከ ሃያ ሺ ኢትዮጲያውያን በዓመት ለአንድ ሳምንት ጊዜአቸውን በአንድነት ያሳልፉሉ ልንል እንችላለን። ይህ ዝግጅት ከአራትና አምስት ዓመት በኋላ ቁጥሩን በእጥፍ እየጨመረ እንደሚሄድ አልጠራጠርም።

እድገቱና ውበቱ ከላይ የተጠቀሰውን ሲመስል ችግሮቹ ምንድን ናቸው የሚለውን ማየቱ የሚያስከፋ ነገር የለውም። የፌዴሬሽኑ አላማና ግብ ለኢትዮጲያውያኖች ግልፅ እንዲሆን ያስፈልጋል። አሁን እንዳለው ሁኔታ የኢትዮጲያውያንን ማገናኘት፤ ቡድኖችን ማስፋፋት እንዲሁም እንግዶችንና ሙዚቀኞች በማስመጣት ጥሩና የማይረሱ ቀናቶችን በአንድነት ለማሳለፍ እንደሆነ ይመስለኛል እንደማስበው። የብዙ ኢትዮጲያውያኖችም ፍላጐት በኳስ ጨዋታው በማሳበብ ከወገኖቻቸው ጋር ለማሳለፍ እንደሚሄዱ ሆኖ ይታየኛል። ፌዴሬሽኑም ዓላማው ይህ ከሆነ ጥሩ አላማ አለው። በፖለቲካና በሌላ መስኮች አስፈላጊውን አንድነት መመስረት ለጊዜው ባይቻልም በስፖርትና በተለያዩ መዝናኛዎች በአንድነት ማሳለፍ ባህላችንን እንዳንረሳ ያደርገናል። ይህ ከሆነ እንግዲህ ፌዴሬሽኑ እንደስፋቱና እድገቱ ብዙ ነገሮችን የማቀናበር ችሎታ ይጠበቅበታል የሚል ዕምነት አለኝ። ኢትዮጲያውያን አገር አቋርጠው ኳስ ጨዋታ ብቻ ለማየት አይደለም የሚመጡት። ዘመድ ለመጠየቅ፣ የጥንት ጓደኛን ለማየት፣ በስደት አብረው የነበሩትን በመከራ ጊዜም አብረው የተጐሳቆሉትን በጦርነቶች አብሮ የታገለውን ወዘተ ለማየት፣ ለመጠየቅና ትዝታውን ለመወጣት ብሎ ከየአቅጣጫው ከገንዘቡ ጋር የሚመጣው እጅግ ብዙ ነው። አዘጋጅ ከተማም በተቻለው መጠን ከየአቅጣጫው ከገንዘቡ ጋር የመጣውን በደንብ ማስተናገድ ይኖርበታል። ሆኖም በሳንፍራንሲስኮና በቨርጂኒያ ያየሁት ችግሮች ብዙውን የሚያስደስቱ አልነበሩም። የሳንፍራንሲስኮ ዝግጅት በብዙ ነገር ጥሩ እያለ የኢትዮጲያውያኖች ምግብ ቤቶች ከሆቴሉ የራቁ ስለነበሩ የመጣው እንግዳ 70 በመቶው ኢትዮጲያዊ ላልሆኑ ምግብ ቤቶች በመሄድ ገንዘቡን አጥፍቷል የሚል ጥብቅ እምነት አለኝ። ይህ ዋናው የዚህ ዓመት ፌዴሬሽን መወቀስ ያለበት ነጥብ ነው ብዬ እጠቁማለሁ። ቀጥሎ በኳስ ሜዳ ውስጥ ሶዳ ማንም እንዳይሸጥ መከልከሉ አግባብ አልነበረም። አዘጋጅ ቡድኑና ፌዴሬሽኑ በቂ የሆነ የተለያዩ ገቢዎች ስለነበሯቸው ሶዳዎችን ለምግብ ሻጮች መልቀቅ ነበረባቸው። መስካሪ አልሆንም እንጂ ውሃ እንኳን እንዳይሰጡ የተከለከሉ እንደነበሩ ጆሮዬን ነካ አድርጐታል። ሆኖም ተጨባጭ ነገር ስላላየሁ ማግረር አልፈልግም። ቀጥሎም ከጨዋታዎች በኋላ የተለያዩ ድግሶች ነበሩ። ምንም እንኳን ፌዴሬሽኑ ከሜዳ ውጭ ባያገባውም የተለያዩ ድግሶችን ለሚያዘጋጁ እንዳይከስሩ በምክር መርዳት ይኖርበታል። ድግሶቹ አይኑሩ ለማለትም ሳይሆን ሕዝብ ይመጣል በሚል ብዙ ወጪዎችን በማውጣት ከአሥር እስከአምሳ ሰው ያልገባበት ዝግጅቶችን በማየቴ በጣም አዝናለሁ። አንድ ድግስ አቅራቢ አንድ ቀን ያለምንም ተወዳዳሪ ቢያዘጋጅ ትርፍ አትርፎ ችግሩን ሊያቃልል ይችላል። ከሁለት እስከሥስት ዝግጅቶችን በመመካከር በአንድ ምሽት ቢዘጋጅ አንዳቸውም አይከስሩም። ተጋባዡም አምሽቶና ተዝናንቶ ይሄዳል የሚል ዕምነት አለኝ። በሳንፍራንሲስኮ ውስጥ ከስምንት ዝግጅት በላይ በአንድ ምሽት ነበረ። ስለዚህ አዘጋጆችና ፌዴሬሽኑ በመመካከር ቢሠሩ ለአዘጋጆች የበለጠ አትራፊና፣ ለእንግዶችም የበለጠ ዝግጅትና ደስታ

የሚሰጡ ሁኔታዎችን መፍጠር ይችላል። ኳስ ሜዳ ውስጥ የነበሩት ዝግጅቶች በሙሉ (ያለሶዳው) ጥሩ ነበሩ። ምግብ በመጠነኛ ዋጋ ተሸጧል። ጨርቃ ጨርቆቹም ሁሉም ማራኪዎችና ልበሱኝ ባዮች ነበሩ። ለወደፊትም አንድም ነገር አትለውጡ እላለሁ።

በቨርጂኒያ ከተዘጋጀው ዝግጅት ጋር አላውዳድረውም። ቪርጂኒያ በአጭሩ ዝርፊያ ነበር። ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው የተበላሸ ነበር። ለዚህም ችግር ፌዴሬሽኑ መለስተኛ የሆነ ወቀሳ ይገባዋል። ለማንኛውም ዝግጅቶች ፌዴሬሽኑ ተገቢ ቁጥጥር ማድርግ ሲገባው ያደረገ አልመሰለኝም። ግለሰቦች ከመጠን በላይ ኢትዮጲያውያኖችን ዘርፈዋል። ምግብ ቤቶችም የትም ቦታ ያላየሁትን ክፍያ አስከፍለዋል። ባይደንቃችሁ የተወሰነ ምግብ ቤቶች ከሃያ እስከ ሃያአምስት በመቶ የሰርቪስ (Service Charge) ብለው ከጠቅላላ የምግብና የመጠጥ ክፍያ ጋር ጨምረው ይሰጡና እንደገና ቲፕም የጠበቁ አይቻለሁ። ሦስት ሆነን ምግብ ቤት ሄድንና ሦስት የኢትዮጲያ ምግብ ፣ሥስት ቢራና ሁለት ቡና አዘን ከአገልግሎት ክፍያ 25% ተጨምሮበት $95 ከፍለን ወጥተናል። ተመልሰን አካባቢው አልሄድንም። ይህ አይነቱ ችግር ከጠቅላላው ሁኔታ ጋር ሲያያዝ በጣም የተበላሸ ዝግጅት አድርጉታል። ሆኖም የሰው ብዛት፣ ዘመድና የጥንት ጓደኞችን የማግኘቱ ጉዳይ ስለማይቀር ችግሩን አላጉላውም።

ከዚህ ቀጥሎ እስከአሁን ካየኋቸው ዝግጅቶች የትኛው ይበልጣል? ለምን? የሚሉትን በመመርኮዝ በሰንጠረዥ አውጥቻለሁ። ግምቱ ከእራሴና በአቅራቢያዬ ያሉትን ጠይቄ ባገኘሁት ላይ ተመስርቼ ከታች ያለውን ሰንጠረዥ አውጥቻለሁ።

| | | ጨዋታ የተካሄደባቸው ከተሞች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቪርጂኒያ | ዳላስ | ቦስተን | ቶርንቶ | ሳንፍራን |
| 1 | ኢትዮጵያዊነትና ሰንደቅ ዓላማ አሰቃቀል | 4 | 4 | 4 | 10 | 7 |
| 2 | ሆቴል አመራረጥ | 5 | 6 | 1 | 10 | 10 |
| 3 | ኳስ ሜዳ አመራረጥ | 3 | 10 | 1 | 10 | 10 |
| 4 | ሜዳው ከኢትዮጵያውያኖች ንግድ ቦታ ርቀት | 7 | 8 | 8 | 5 | 4 |
| 5 | ሜዳው ከሆቴሉ ያለው ርቀት | 7 | 9 | 8 | 10 | 1 |
| 6 | ኢትዮጵያውያን ንግድ ድርጅቶች ተጠቅመዋል | 10 | 9 | 8 | 8 | 3 |
| 7 | ፌዴሬሽን፡ በዝግጅቱ፡ ላይ፡ የነበረው፡ ቁጥጥር | 1 | 8 | 4 | 10 | 10 |
| 8 | ለዝግጅት ጥሩ ምላሴነት | 0 | 10 | 2 | 10 | 8 |
| 9 | በኳስ ሜዳ የምግብ ዋጋዎች ርካሽነት | 1 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 10 | የምግብ ቤቶች ዋጋ መቀየር | 1 | 7 | 3 | 9 | 8 |
| 11 | የሙዚቀኞች ጥራት | 2 | 6 | 10 | 7 | 4 |
| 12 | ሜዳ ውስጥ የነበረው አጠቃላይ ሁኔታ | 8 | 6 | 5 | 10 | 8 |
| 13 | የመጨረሻው ፓርቲ ሕዝብ ብዛት | 6 | 3 | 4 | 10 | 10 |
| 14 | የመጨረሻው ፓርቲ አርኪነት | 0 | 6 | 7 | 10 | 10 |
| 15 | የአዘጋጅ ከተማ የሥራ ጥራት | 0 | 7 | 2 | 10 | 8 |
| 16 | የሕዝብ ብዛት | 8 | 5 | 6 | 9 | 10 |
| 17 | አጠቃላይ ዝግጅት | 3 | 7 | 4 | 10 | 9 |
| | ጠቅላላ ነጥብ | 66 | 121 | 87 | 158 | 130 |
| | ከ | 170 | 170 | 170 | 170 | 170 |

አሸናፊው ቶሮንቶ ነው እላለሁ። በቨርጂኒያ ውስጥ የተካሄደው ምንም እንኳ በርካታ ኢትዮጲያውያኖች ቢሳተፉበትም አዘገጃጀቱ ያማረ አልነበረም። ኳሱ ሜዳ የነበሩ ምግብ ሻጮች ሆኑ 18th St.ያሉት ምግብ ቤቶች ከመጠን በላይ ተካፋይ ቡድኖችንና ደጋፊዎቻቸውን ያለአግባብ እንዲከፍሉ አድርገዋል። ሲፈልጉ ዋጋ ይጨምራሉ። ሲፈልጉም ውሃ ይሸጡ ነበር። የመጨረሻው ዝግጅት ሆቴሉ ውስጥ በመደረጉ ቦታው ከሚችለው በላይ ስለያዘ ትርምስምሱ የወጣ ነበር። የሲጋራ ጢሱም አካባቢውን አፍኖት ነበር። እንደተለመደው ሰው $20.00ብር እየከፈለ ገብቶ ወዲያውኑ ህዝብ በዝቷልና ልቀቁ ይባላል። ትንሽ ያየውም፣ ዘግጅት ብሎ የመጣውም በማዘን ወደ 18th st. መጓዝ ጀመረ። በአጠቃላይ የቨርጂኒያ ዝግጅት ብዙ ኢትዮጲያኖችን ያስቆጣ ይመስለኛል። የቶሮንቶ ዝግጅት በእኔ እምነት በጣም ያማረና የማይረሳ ነበር። ሰንደቅ አላማችን ከሆቴሉ ጀምሮ እስከ ኳስ ሜዳው ድረስ በአግባቡም ሲውለበለብ ማየቱ ብቻ በቂ ነው። በሌላ ከተማዎችም ባንዲራችን ተውለብልቧል። ሆነም የቦታ አመራረጡ በግድ የለሽነት የተደረገ ይመስላል። ሰንደቅ አላማ የአገር ልዩ ምልክት ነውና በክብር መውለብለብ አለበት። ይህን በሚገባ ያደረገው የቶሮንቶው አዘጋጅ ቡድን ብቻ ነው። የሚቀጥለው ዓመት ዝግጅት በሜሪላንድ ከተማ እንደሚሆን ፌዴሬሽኑ ወስኗል። መጀመሪያ እንኳ አትላንታ ያዘጋጃል የሚል እምነት ነበረኝ። የሚገባቸው ነበር። የ18th St.ዋጋ መናርና በሜዳው ውስጥ የዋጋ መቀያየር፣ የውሃ ሽያጭ እየታየኝ፤ ያለፈውን የቪርጂኒያ ልምድ በማስታወስ የሜሪላንዱ ዝግጅት ቅዠት ቅዠት ይለኛል። በሌላው በኩል ደግሞ የፌዴሬሽኑን እድገትና ስፋት ስመለከት ቁጥጥሮችና እድገቶች ይኖራሉ ብዬ አምናለሁና የሜሪላንዱ ዝግጅት ከሁሉም ዝግጅት የበለጠ ይሆናል የሚል ሕልም እየመጣ ያፅናናኛል። ሌሎቻችሁም እንደእኔው ከዛሬው ብታስቡበት በምትሄዱበት ጊዜ ይቀላችኋል። በዝግጅቶቹም ተደስታችሁ እንደምትሄዱ እርግጠኛ ነኝ። በእንደዚህ ዓይነቱ ስብስብ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ይገኛሉ። ኳስ ጨዋታው የውበት፣ የቁንጅናው፣ የጭፈራውና የፖለቲካ ስብሰባዎች ሲሆኑ ከውበት ውድድር በስተቀር ሁሉም ዘንድ ሄጃለሁ። ከሁሉም ነገር ብዙ ነገር አውቄአለሁ።ለመደምደም ያህል ፌዴሬሽኑ በማንኛውም ኢትዮጲያውያን ሁሉ መመስገን ይገባዋል። ስህተቶችም ቢኖረውው ከሰውና ከጊዜ እጥረት የተነሳ ስለሆነ ጊዜ ያላቸው ሁሉ ፌዴሬሽኑን በመገናኘት ልትረዱ የምትችሉበትን ብታሳውቁ ብዙዎቹ ችግሮች እየተሻሻሉ እንደሚመጡ አልጠራጠርም። ፌዴሬሽኑ የሚከተሉትን አራት ነገሮች በጽሞና እንዲመለከት እጠቁማለሁ:-

1) በተቻለ መጠን ሆቴሎችና ስታዲዮሞች ከኢትዮጵያውያን የንግድ ቦታ ባይርቁ። አንድ አካባቢ ከሆኑ ብዙ ኢትዮጲያውያኖች ሊጠቀሙ ይችላሉና።ለእንግዳውም ሕዝብ መንከራተት ይቀራል።

2) ከአዘጋጅ ከተማዎች ጋር በመተባበርና ቁጥጥሮች በማድረግ ዝግጅቶች ቅንጅት እንዲኖራቸው ማድረግ፤ ፕሮግራሞች እንዳይደራረቡ ማዕከላዊ አሠራርን በተግባር ማዋል፤

3) ፌዴሬሽኑ ከሚያገኘው ገንዘብ አስፈላጊውን ወጪ ካወጣ በኋላ ለተለያዩ የኢትዮጲያ የችግር መፍቻዎች መለገስ። ወይንም አሜሪካ ውስጥ የኢትዮጲያ ቤተክርስቲያኖችና መስጊዶች፣ የኢትዮጲያ የሕፃናት መዋያዎችና Community ማህበራትንመርዳት፣ አቅም የሌላቸውን ቡድኖች መርዳት፤

4) ሶዳ መሸጥ ክልክል ነው የሚለውን ሕግ ብታነሱት መልካም ነው።

ከዚህ በላይ ሌላው ከእድገት ጋር እያማረ ስለሚመጣ እድገቱን ለማየት ከሚጓጉት አንዱ ነኝ።
ለመጪው መልካም ዝግጅት ይሁንላችሁ



የቺካጉው ቡድን በዘንድሮው ውድድር ለምን እንዳልተሳተፈ መግለጫ የሚሰጠን ብናገኝ ደስ ይለናል። ፎቶውን የላኩልን አበራ ሲሳይ ናቸው።



# ቢስቁም ባይስቁም



## « ማሙሽ »

አንድ ጣቱን እየጠባ ያስቸገራት እናት ከዕለታት አንድ ቀን ጣቱን እንዲያወጣ ካደረገችው በኋላ "ማሙሽ ከዛሬ ወዲያ እንደዚህ ካደረክ ሆድህ ይቆዘራል" ትለዋለች። ልጅም ፈርቶ ይተዋል። ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ዘመዳቸው እቤት ትመጣለች። እርሷም እርጉዝ ነበረች። ልጅም አይቶ ሲያበቃ "ሆድሽ ለምን እንደተቆዘረ አውቃለሁ፣" አላት ይባላል።

■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■

## « እዛ ማዶ »

ሰካራም – "የዚህ መንገድ ማዶ የትኛው ነው?"
መንገደኛው – አሻግሮ እያመለከተ "ያ ነዋ! እዚያ ማዶ።"
ሰካራም – "ይገርማል እኮ! አሁን ከእዚያ ማዶ አንድ ሰው እዚህ ነው ብሎ ላከኝ።"

■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■

## « ጥርሴን »

አበበ – "ጥርሴን በጣም አሞኛል፤ ልነቀለው ነው።"
በላይ – "አብደሃል እንዴ? እኔን ትላንት እንዲሁ አሞኝ ስጨነቅ ሚስቴ ዳበስ ዳበስ አድርጋ ብትስመኝ ሕመሙ ጠፍቶ ይኸው ድኛለሁ። ለምን አንተም አትሞክርም?"

አበበ – " በጣም ጥሩ! አሁን ቤት ካለች እንሂዳ።

■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■

## « ቤቱ እንዳይዞር»

የቤቱን ቁልፍ ቀዳዳ ማግኘት ተስኖት ይታገል የነበረው ሰካራም ጐረቤቱ አየውና ጠጋ ብሎ፤ "ቁልፉን ማስገባት አቅቶህ እንደሆን ልርዳህ መሰለኝ?" ይለዋል።

ሰካራሙም " አይ ስለሱ አትቸገር፤ ይልቅስ እንዳይዞር ቤቱን ያዝልኝ፤" ብሎት አረፈ።

■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■

# ? ጨዋታና ስንጠረዥ ?

## አዕምሮ ፈታኝ ጥያቄዎች

1ኛ. አበበ፣ ተስፋዬ፣ በለጠና ከበደ አራት ወንድማማቾች ናቸው። አበበ ከተስፋዬ ቀደም ብሎ ይወለዳል፤ ግን በለጠ ይቀድማል። ከበደ ከአበበ ቀድሞ ተወለደ። እንደ አወላለዳቸው ቅደም ተከተላቸውን ጻፉ።

■ ■ ■ ■

2ኛ. ጣሰው ከዓለሙ ረዘም ቢልም ከአሰፋ ያጥራል። ፋሲል ግን ከአሰፋ አይረዝምም። በዚህ አባባል ከእነኛህ የትኞቹ ናቸው ትክክል?

ሀ. አሰፋ ከዓለሙ ይረዝማል።
ለ. አሰፋ ከፋሲል ይረዝማል።
ሐ. አሰፋ ከፋሲል ያጥራል።
መ. ጣሰውና ፋሲል ቁመታቸው እኩል ነው።
ሠ. ፋሲል ከዓለሙ ቢረዝምም ከጣሰው ያጥራል።

■ ■ ■ ■

3ኛ. አንድ ጠበቃ ስድስት ምስክሮችን ዳኛ ፊት ሊያቀርብ ያቅዳል። ዓለሙ፣ ተሰማ፣ አስቴር፣ ላቀች፣ ቆንጂትና መገርሳን። እያንዳንዱ ምስክር የሚቀርበው አንዴ ብቻ ነው። ለጉዳዩ ጥራት አቀራረባቸው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት እንዳለበት ይወስናል።

1. አራተኛ የሚቀርበው ምስክር ዓለሙ መሆን አለበት።
2. አስቴርና ቆንጂት መቅረብ ያለባቸው ከተሰማ በፊት ነው።
3. ላቀች ከአስቴር በፊት መቅረብ አለባት።

በዚህ መመሪያ መሠረት ስድስቱ ምስክሮች ዳኛ ፊት የሚቀርቡበትን ቅደም ተከተል አውጡ።

(መልሶቻችሁን ላኩልን)

■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■ ■

## ያለፈው ስንጠረዥ መልስ

በትክክል የመለሱና የላኩልን፤

ሳምሶን አንዳርጌ
(ከዎርቼስተር ማሳቹሴትስ)

ተሻገር ከልካይ
(ላስ ቬጋስ)

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጉ 1 | ፓ 2 | ጠ 3 | ሳ 4 | ■ | ካ 6 | ኣ 7 | ሰ 8 | ሬ 9 | ው 10 |
| ዱ 11 | ባ 12 | ■ | ን 14 | ቆ 15 | ሀ 16 | ች 17 | ■ | ል 19 | ፕ 20 |
| ካ 21 | ■ | ኸ 23 | ጻ 24 | ጓ 25 | ■ | ስ 27 | ጓ 28 | ዓ 29 | ■ |
| ሀ 31 | ታ 32 | ር 33 | ሬ 34 | ■ | ■ | ሬ 37 | ■ | ኸ 39 | ማ 40 |
| ■ | ን 42 | ■ | ታ 44 | ካ 45 | ካ 46 | ቆ 47 | ■ | ሰ 49 | ማ 50 |
| ከ 51 | ቆ 52 | የ 53 | ■ | ም 55 | ን 56 | ■ | ኸ 58 | ው 59 | ር 60 |
| ሆ 61 | ሞ 62 | ች 63 | ■ | ኸ 65 | ቃ 66 | ጠ 67 | ሪ 68 | ■ | ■ |
| ■ | ቲ 72 | ቆ 73 | ሰ 74 | ሰ 75 | ■ | ል 77 | በ 78 | ቢ 79 | ሰ 80 |
| ኸ 81 | ■ | የ 83 | ም 84 | ጃ 85 | ■ | ዩ 87 | ል 88 | ፋ 89 | ል 90 |
| ሰ 91 | ና 92 | ን 93 | ቲ 94 | ■ | 96 | ን 97 | ■ | ጀ 99 | ል 100 |

እንዳለፈው ቃላት በሰንጠረዥ ጨዋታ ነው የሚጫወቱት። በእንግሊዝኛ ለተጻፈው የአማርኛ ትርጉሙን በመስጠት፤ በአማርኛ ተጽፎ ባዶ ቦታ ለተተወው ስሜት በሚሰጥ የአማርኛ ቃል ሰንጠረዡን ይሞላሉ። መልሱን በሚቀጥለው እትም እናወጣለን። በትክክለ ሠርተናል የምትሉ ስምና አድራሻ ላኩልንና እናወጣዋለን።

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | | 15 | 16 | 17 | 18 | | 20 |
| 21 | | 23 | 24 | 25 | 26 | | 28 | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | | 35 | | 37 | 38 | 39 | 40 |
| 41 | 42 | | 44 | | 46 | 47 | 48 | 49 | |
| | 52 | 53 | 54 | 55 | 56 | 57 | | 59 | 60 |
| 61 | | 63 | | 65 | 66 | 67 | 68 | | 70 |
| 71 | 72 | 73 | 74 | 75 | | 77 | 78 | 79 | 80 |
| 81 | 82 | | 84 | 85 | | 87 | 88 | 89 | |
| 91 | 92 | 93 | 94 | | 96 | 97 | 98 | 99 | 100 |

## ወደጎን

1. *Philosopher*
5. *Liar*
11. *He cursed.*
15. *to sleep*
23. *in fault*
28. የበሬ ሥጋ ብልት
31. *rural*
37. *deceive*
41. *rust*
46. *I won't say.*
52. *Bekele told a story.*
59. *bee*
65. *He got sick.*
71. *Don't curse.*
77. ዘነጋ
81. *say*
84. *edge*
87. *North of U.S.A.*
91. *What you have to tell her*

## ወደታች

1. *He bought a horse.*
2. ሳንቃውን ____ ____።
3. *well known*
6. የሚበላ
7. *for us*
8. *Don't kill.*
10. *He will come.*
15. *to leave*
29. *if I beg,*
32. *satisfied*
37. *handsome*
44. *he said,*
53. *noon*
55. *miracle*
60. *If I come*
61. *flowery*
68. *she is beautiful.*
72. *huge*
74. *monastery*
79. *He became partial.*

መልስ ሰጪ ስም ______________________ አድራሻ ______________________

# CP TRAVEL ሲፒ የጉዞ ወኪል

RAUL CHIPOCO
President

***WISHES YOU***
***A HAPPY ETHIOPIAN NEW YEAR !!***

## እንኳን ለአዲሱ ዓመት

## በሰላምና በጤና አደረሳችሁ።

## በአዲስ ዓመት
## ልዩ ቅናሽ


## ከአትላንታ -- አዲስ አበባ *$1,515.00*

ለማንኛውም የጉዞ አገልግሎት
በርካሽ ዋጋ

Special to
AFRICA

## ATLANTA TO ADDIS ABABA
## ***$1,515.00 Only***

** Some restrictions apply*



## ሲፒ የጉዞ ወኪል

AT LINDBERGH PLAZA
2851 PIEDMONT ROAD, N.E. SUITE B-1000
Phone: (404) 233 - 2511 - Fax: (404)231-9557

# Live Reggae

# THE WILD HARE

## & SINGING ARMADILLO FROG SANCTUARY




IICAGO

**(312) 327 - Hare**